በፍቅር፥በሰላም፥በአንድነት
ተከባብሮ ለመኖር
መደማመጥ፥
መቻቻል


ጥር/የካቲት ፲፱፻፹፯
፫ኛ ዓመት ቁጥር ፭
$2.75
ኢትዮጵያዊ የቤተሰብና የመዝናኛ መጽሔት በአማርኛ
በየሁለት ወር የሚታተም

# ላንዳፍታ



## የፊተኛው ለኋለኛው ማስጠንቀቂያ ነበር





የተቃዋሚ ኃይሎችን ከኢህአዴግ ጋር ለማደራደር የተደረገው የአሜሪካ ምክር ቤት ሙከራ

❖

አዲሱ ህገመንግሥት ከውጫሌ ውል ጋር ሲተያይ

❖

ከአቡነ ዜና ማርቆስ ጋር ውይይት

❖

“የኮለምበስ ጉዞ” ልብ ወለድ

❖

❖ በቅርብ ከኢትዮጵያ የደረሱን ዜናዎች

# LANDAFTA

An Ethiopian Cultural Bi-monthly Amharic Magazine
(Amharic is the official language of Ethiopia)
January/February 1995 Vol. 3. No.5

ኑሮ በአሜሪካ

አዳምና ሔዋን

ልብ ወለድ የደብራ ጣሰ ዕጣዬ

# የኢትዮጵያ መንደር





## ETHIO VILLAGE

### CAFE & RESTAURANT

**3462 N. Clark St.**
**Chicago, IL 60657**
**(312) 929-8300**

CATERING AND CARRY OUT AVAILABLE

ቀይ ወጥና ዝግኑ ዶሮ ወጥ አልጫው፤
አትክልት ከሥጋ ጋር ምንቸት አብሽ ክትፎው።
የአበሻ ዳቦና ቆንጆ የማር ጠጅ፤
ሽታው ግቡ ይላል ሳይገቡ ከደጅ።
ቆርጠው በሩን ከፍተው ገባ ሲሉ ገና፤
አገር ቤት የገቡ ያስመስላልና።
የሰኞ ዕለት ዱለት የበግ ወጥ ፍትፍቱ፤
ረቡና ዓርብ ዕለት የጾም በያይነቱ።
በስምንት ዓመት ልምድ የሙያ ክምችት፤
ፍጹም ኢትዮጵያዊ በሆነ ዝግጅት፤
ኢትዮ ቪሌጅ ይምጡ ሲያሻዎት መደሰት።



# ማ ው ጫ

# CONTENTS


2 ከአዘጋጁ

3 ሰላምታ ከወደ አገር ቤት (ወርቃየሁ)

6 እንዲህ ሆነ
ዜናዎች ከኢትዮጵያ (ከኢትዮጵያ ወኪል)

13 አንድ ጥያቄ አለኝ!

15 “ሁለተኛው የውጫሌ ውል ዶ/ር ሥዩም ገላዬ

19 ልብወለድ
የዴብራ ጠስ (ገረሱ)
ዕጣዬ (አብረኸት)

25 ኑሮ በአሜሪካ
የማታ የማታ እውነት ትረታ
ከአቡነ ዜና ማርቆስ ጋር ቃለ መጠይቅ
ታደሰ አስራትን እናስተዋውቃችሁ

30 አዳምና ሔዋን
አላለልኝ ይሆን (ትዝታ አለብኝ)
የኮለምበስ ጉዞ (ልብወለድ)

40 ባላገርና ፖለቲካ (ከአለፈው የቀጠለ)

47 ጨዋታና ሰንጠረዥ


## የህገ መንግሥቱ ጉባኤ ገጽታዎች





ሽፋን -- ግርማዊ ቀ ኃ ሥ -- የደርግ አባላት -- የኢህአዴግ መሪዎች


“ላንዳፍታ” የግል መጽሄት ናት። የሚወጡ ጽሁፎች በሙሉ የአዘጋጆቹን አመለካከት ወይም እምነት ያንጸባርቃሉ ማለት አይደለም። ጽሁፎቹን በሬዲዮ፣ በቴሌቪዥን ሆነ በተመሳሳይ መንገድ በከፊልም ሆነ በሙሉ አባዝቶ ለማሰራጨት የጸሃፊውንና የአዘጋጁን ፈቃድ ማግኘት ያስፈልጋል። በተለይ የገጠመኝና የፈጠራ ድርሰት ጽሁፎች ህጋዊ መብታቸው የተጠበቀ መሆኑን እንገልጻለን።

© COPYRIGHT LANDAFTA 1995

ላንዳፍታ
፲፱፻፹፯
፫ኛ ዓመት ቁጥር ፭
LANDAFTA
January/February 1995 V. III - No.5

አዘጋጅና አሳታሚ
መኮንን ገሠሠ

**Publisher/Editor**
*Mekonnen Gessesse*

**Editorial Advisors**
*Dr. Abera Molla*
*Abera Sisay*
*Solomon Melesse*
*Dawit Deres*
*Zelleke Nigatu*
*Girma Zegeye*

**Editorial Assistant**
*Aster Mekonnen*

**Distribution**

Atlanta, GA
California Mart
Sweet Auburn Grocery
H & B Tailoring

Chicago, IL
Ethio-Village Rest.

Daton, OH
Rainbow Cafe

Dallas, TX
Maru Grocery
ET. Beauty Supply

Huston, TX
Rendevous Coffee

L.A., CA
Merkato
Damera

Oak Land, CA
Albo-African Shop

San Jose, CA
St. Claire News Stand

Seatle, WA
Addis Cafe

St. Louis, MO
A & Z Liquor

St. Paul, MN
Merkato

Tampa, FL
Ibex Ethiopian Restaurant

Washington D.C.
Addisu Gebeya
Family Food Market
Merkato Market
Nini Market (Alex.)
Tana (Silver Spring)

Windsor, Ontario
Tewodros Zewdu

Landafta
P.O.Box49301
Atlanta, GA 30359
Phone/Fax (404)728-9122

# ከአዘጋጁ

## እ ን ን ቃ !!

ዛሬ በስደት በምንኖርበት አገር ብዙ ችግሮች ሲገጥሙን ይታየናል። የሰው አገር የሰው ነውና እንደራስ አገር ሙሉ መብትን እንደአገሩ ዜጋ አስጠብቆ ለመኖር ብዙ ደንቃራዎች ይገጥሙናል። ኑሮን ለመግፋት፣ በትምህርት ለመበልፀግ፣ ቅርስ ለማበጀት ወዲህ ወዲያ እንሯሯጣለን። የተሳካልን አለን፤ ጠብ ያላለልንም አለን። የተሳካልንም ሆነ ያልተሳካልን ሁላችንም አገራችን ይናፍቀናል። አገራችን ሰላም ሰፍኖ የዜጎች መብት ተጠብቆ እኛም ሄደን አገራችንና ወገናችንን ለማበልፀግ የበኩላችንን የምንፈልገው ጉዳይ ነው። አገራችን አልደላትምና ከፊቱ የኋላው ሁኔታ እየባሰ ለበለጠ ችግር እየተጋበዘች እኛም ከዛሬ ነገ ይሻላል በሚል ተስፋ ስንጠባበቅ ቀናት በወራት፣ ወራት በዓመታት እየተተኩ እዚሁ ያረጀን አለን።

በዚህ አገር ኑሮዋችን በጋራ ተሰባሳበን የምንመካከርባቸው የምንማማርባቸውና የምንረዳዳባችወ ሁኔታዎችን ለመፍጠር ስንጥር፤ በአንፃሩም በአገራችን የሚደርሰውን እየደረሰ ያለውን ችግር ለዓለም ሕዝብ ለማሰማት የምንችልባቸውን የጋራ መድረኮችን ለመፍጠር ስንጥር፣ በወገናችን ላይ የደረሰውን እየደረሰ ያለውን ረሃብ፣ እርዛት ሰቆቃ በመጠኑም ቢሆን ለማጥፋት ተረዳድተን በጋራ ሆነን አስተዋጽዖ እናበረክታለን ብለን ለመሰባሰብ ስንጥር፤ የጋራ አንድነት ለመፍጠር የምንችልባቸውን ሁኔታዎች ለማመቻቸት ስንጥር እንዳንሰባሰብ፣ የጋራ አንድነት እንዳንፈጥር የሚበታትኑን የሚለያዩን በመካከላችን መተማመን እንዲጠፋ የሚያደርጉ ሁኔታዎች እየተፈጠሩ ያሉ መሆናቸውን በየቦታው በቅርብ ጊዜ እየታዩ የመጡ ክስተቶች ምስክሮች ናቸው። አገር ቤት ሕዝብን ለመከፋፈል ከሚደረገው ጥረት ለይተን የማናየው ጉዳይ ነው።

እንዳንሰባሰብ አንድነታችንን እንዳናጠናክር በመጀመሪያ በመካከላችን መተማመን እንዲጠፋ ማድረግ የነዚህ ከፋፋይ ግለሰቦችና ኃይሎች የመጀመሪያ ሙከራቸው ነው። አሉባልታዎችን መንዛት፣ ተራ ወሬዎችን ማሰራጨት ዓይነተኛ መሣሪያቸው ነው። ወገኖች በጋራ በተሰባሰቡበት ቦታ የሚያገናኙና የሚያግባቡ ጉዳዮች በማንሳት ፈንታ የሚያጨቃጭቁ የሚያነታርኩ ጉዳዮች ላይ ትኩረት እንዲሰጥባቸው ማድረግ ሌላው ዘዴያቸው ነው። በአስተሳሰብ፣ በአመለካከት የዋህ የሆኑትን ግለሰቦችን ውሸት የሆነ ነገር እውነት እንደሆነ አድርጎ መጀመሪያ በማሳመን እነኚህ የዋህ ግለሰቦች በሌሎች ላይ እምነት እንዳይኖራቸው ያደርጋሉ። ከዚያም እነሱን ከለዩ በኋላ ለፈለጉት ዓላማቸው ይጠቀሙባቸዋል። ይህን ሁኔታ ሁላችንም እንድንነቃበት ያስፈልጋል።

የመጽሔት ዝግጅት ክፍላችን በስደት ያለውን ወገን ለማገልገል ባለው ጽኑ ዓላማ ይህን ጉዳይ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት በየቦታው እየተካሄዱ ያሉትን በታታኝ መሰሪ ድርጊቶች በመከታተል እያጋለጠ ይፋ እንደሚያደርግ ሲገልጽ በደስታ ነው። "በፍቅር፣ በሰላምና በአንድነት ተከባብሮ ለመኖር መደማመጥንና መቻቻልን" አለብን።

የላንዳፍታ መጽሄት ዝግጅት ክፍል
LANDAFTA
P.O.Box 49301
Atlanta, GA 30359
(404) 728-9122

*Landafta is an independent magazine published bi-monthly in Amharic.*
*Views expressed do not necessarily represent that of its editors and advisors.*

# ሰላምታ ከወደ አገር ቤት

## እንደምን አላችሁ?

እንደምን ከርማችኋል? እንኳን ለአዲሱ ዓመትና ለብርሃነ ልደቱ አደረሳችሁ!! ለመሆኑ እንዴት ናችሁ? ኑሮና ብልሃቱ እንዴት ይዞአችኋል? ይሂ አሜሪካ የምትሉት የፈረንጅ አገር እንዴት ያደርጋችኋል?

እኛ ደህና ነን። እግዚአብሔር ይመስገን። ገናን፣ ጥምቀትን አክብረናል። ምንም የለብን ደህና ነን። ዳሩ እናንተስ ምን አለባችሁ? – በሚያንጠባርቅ ፎቅ ላይ መምነሽነሽ ነው። ከእርሱ ሲወረድ ጭቃ አያገኛችሁ፣ አቧራ አይቦን፣ የሠፈር ቆሻሻ፣ የመንገድ ላይ ግማት አይሰነፍጥ! . . . በዶጅ በሙስታንግ በሼፍሮሌት ሸው ዕልም ነው። የከሣ የጠቆረ ፊት አይታይ። ተራብኩ ተጠማሁ የሚል ለማኝ ቡትቷም አያስቸግር። ማክዶናልድ እየተገመጠ፣ ሆት ዶግ፣ ስቴክ ጥብስ እየተደረገ፣ ብርቱካን ከሚመስልበት አሜሪካ ምቾትና ጌትነት ይቀልድባችኋል። ሰርክ የምትበሉት የላመ የጣፈጠ ቆሎና ንፍሮ፣ ዶኬና ሽልጦ፣ አሸር በአሸር ካላችሁበት አይደርስ። ቁንጫ አይበላችሁ። ትኋን አይልሳችሁ። ቀበሌ ስብሰባ ውጡ አትባሉ፣ ሕገመንግሥት ተወያዩ፣ ድጋፍ ሠልፍ ውጡ የለባችሁ፤ ባለጊዜ አማርኛ አይለምድባችሁ። – ገና ቢደርስ፣ ዓመት በዓል ቢመጣ ሙክት አትጎትቱ፣ የቅርጫ አታስቡ። የዳቦ እህል፣ የጠላ እህል፣ የአሻሮ፣ ብቅል፣ ጌሾ፣ በርበሬ፣ መከለሻ፣ የቅመማ ቅመም የጤፍ ሸመታ ኪሳችሁን አይገለብጥ!

እኛስ የበጋውን ፀሐይና ሐሩር ተያይዘነዋል። አሁን ከረር ገንተር ያለው የበጋው ሐሩርና ፖለቲካው ይመስላል። አዝመራ ተሰብስቦ ከጎተራ ገብቷል። አልሰበሰብልህ ብሎት ኳንደታካች ገበሬ የሚማስነው ባለአዝመራ የቤተመንግሥት ሹሞቻችን ናቸው። በሚያዝያ አጭደው በግንቦት አጋማሽ "ፈንጥዙ፣ ፌሽታ አድርጉ" የሚሉን ይመስላሉ።

እነሆ አዲስ ሕገመንግስት ተሰጥቶናል። በየአሥር ዓመቱ አዲስ ሕገ መንግሥት የሚረቀቅልን እንደቂጥኝ በሽታ ቁስል እየሆነብን ሳይሆን አይቀርም። – የቂጥኝ በሽታ መንስኤው ቫይረስ ነው። ቫይረሱ ያለው ደም ውስጥ ሆኖ ነገር ግን ቆዳ ላይ የሚወጣ ቁስል ያስከትላል። ክብረ–ሰማይ የሚባል ተክል መድሃኒቱ ነው ይባላል። ወተት የሚመስል ፈሳሽ አለው። ቁስሉ ላይ ፈሳሹን ሲቀቡት ራስን እስከሚያስት ያቃጥላል። ታዲያ የሀገሬ ሰው ቂጥኝ ሲይዘው በደሙ ውስጥ ያለውን ቫይረስ እንደመታከም በቆዳው ላይ የወጣውን ቁስል በክብረ ሰማይ እያቃጠለ ነፍሱ እስክትወጣ ይቃጠላል። ቁስሉ ትንሽ የደረቀ መስሎ እንደገና በሌላ ስፍራ ብቅ ይላል። ደግሞ እንደገና እያቃጠለ ቁም ስቃዩን ያያል። እኛም ይህን የሕገ–መንግሥት ነገር እንደ ቂጥኝ በሽታ ላይ ላዩን በክብረ ሰማይ እያቃጠልነው ይመስለኛል በየአሥር ዓመቱ የሚደጋግመን። ሲሆን ሲሆን መጀመሪያ የየልባችንን በሽታ የቂም በቀል ውጋት ታክመነው ቢሆን ምንኛ ደግ ነበር።

የሕገመንግሥት አጽዳቂ ጉባኤተኛ ገሚሱ አዲስ ታሪክ ሲያስተምር፣ ገሚሱ ሲነታረክ፣ ገሚሱ ሲሳደብ፣ ገሚሱ አዳማቂ፣ አጫፋሪ ሆኖ፣ ገሚሱ እንቅልፉን ሲለጥጥ አንዳንዱም ነጠላውን ሲቋጭ ኮተቤ ላይ ሱባኤ ገብቶ ከረመ።



በመጨረሻም የሰማውም፣ ያልሰማውም፤ የገባውም ያልገባውም "ተስማምቻለሁ" ብሎ እጁን ጣራው እስኪነካ አወጣው፤ ሹማምንቶቹም አዩለት።

ሻለቃ አድማሴ የሚባሉ አዛውንት "ስለ እግዚአብሔር አንዳንዱን እንኳ እውነት ተናገሩ" ሲሏቸው ሰነበቱ። እነዚህ ትናንሽ "ንጉሶች" ልባቸው ያቆበቆበ የዘመኑ ሹማምንት እግዚአብሔርን የሚያውቁት ይመስል! ሻለቃ "ቆማጣን ቆማጣ ካላሉት ገብቶ ይፈተፍታል" ብለው የቆረጡ ይመስል "ክቡራን ጌቶች" እያሉ በነገር እየሸነቆጡ የዘመኑን መኳንንቶች ሲያንጫጩ ሰነበቱ። እርሳቸውም መሳቂያ ሆነው የስድብና የትችት ውርጅብኝ ችለው ከረሙ። አዳራሹን ከሞላው ከዚያ ሁሉ ጉባኤተኛ መካከል ሕገ-መንግሥቱን በክፉ የሚያነሱት ሁለት ሰዎች ብቻ ነበሩ። ሌላው ገና ጉባኤው ተጀምሮ ረቂቁን ሳያየው "በዓይነቱ የመጀመሪያው ዲሞክራሲያዊ ሕገ-መንግሥት" ማለት ጀመረ። እኛም ነቃን እወቅናቸው።



ሻለቃ አድማሱ በጉባኤው ላይ
ተቃውሞአቸውን ሲያሰሙ

በጎጃም የብቸና ሰው በየንግግሩ መካከል "እኔው ሆይ!" የሚለው ዘይቤ አለው። ታዲያ አንድ ስፍራ ሁለት የጎጃም ሰዎች ተገናኝተው ይጠያየቃሉ።

"አንተዬ ወዬት ነው አገርህ? ብሎታል አሉ አንደኛው

"እኔው ሆይ?!" ይላል የብቸናው ሰው

"በል ተወው አግኝቼዋለሁ። እዚያው ብቸና ነህ" አለው አሉ መልሶ። እኛም ገና በጉባኤው መክፈቻ የአንዳንድ "እንደራሴዎቻችንን ንግግር" ስንሰማ አወቅናቸው። የእነማን እንደሆኑ ለየናቸው። መገንጠል ይቻላል የሚለው አንቀጽ ሲፀድቅ ጉባኤተኛውን ሩምባ-ሱምባ-ማሪንጌ ቻቻ-ትዊስት ወደግራ - ትዊስት ወደ ቀኝ አሰኘው። ዳንኪራው ጭፈራው እልልታው ቀለጠ። በደስታ ብዛት መሬት ላይ ወድቀው ይንከባለሉ የነበሩ ጉባኤተኞችም ነበሩ። አገሬን ያለ ደግሞ ሁለት እጆቹን አንጓው ላይ የቆረጡት ያህል በብስጭት ድብን ትክን አለ። ቆሽቱ አረረች። ሕዝብና እንደራሴ ተዛዘቡ። . . . ሰውዬው ከእጮኛው ጋር በመዳራት ላይ እያለ ያመልጠውና "ጡጥ" ያደርጋል አሉ። እጮኚት ሰምታ እንዳልሰማች ዝም ብላለች። አቶ እጮኛ ደግሞ እንደተሰማበት አውቆ እፍረት ይዞታል። ምንተዕፍረቱን "እንዲያው የእኔ ነገር አሁን እኔ ነኝ ባል የምሆንሽ?" አላት አሉ። ሕዝብና እንደራሴ "አሁን አንተ ነህ ምን የምትሆነኝ?" ተባባሉ። ተገማመቱ። ከእንግዲህ የሚቀረው ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደራዊ ደርግ ለኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ "ሥልጣን" እንዳስረከበበት ጊዜ የምትመስል ትንሽዬ ድራማ ብቻ ናት።

ምድረ-ተቃዋሚ ደግሞ "አገር ጠፋ። አገር ፈረሰ።" እያለ ይጮሃል። ለትልቋ አሜሪካ አቤት ይላል። ይወተውታል። ይህን ሁሉ እሜቴ አሜሪካ ትሰማለች። ልቧ ወደ አንዱ አድልቶባት መገላገልም ማስታረቅም ተስኖአታል። እንደባለጌ ገላጋይ እጅ ጠምዝዛ ልታስታርቅ ቢሆንላት እየሞከረች ነው።

የቀድሞ ሹማምንቶቻችን እነዚያ ትልልቆቹ አለቆቻችን ትንንሽ ሆነው፣ ያ የሚያምረው ቁመናቸው ግርማ ሞገሳቸው ጠፍቶ፣ ጭር ኩስምን ብለው ለፍርድ ችሎት ቀርበዋል። "የፍየል ወጠጤ" ባዘፈኑበት ሬዲዮና ቴሌቭዥን አንቱ ተብለው ስንቱን ባላሉበት ምድር "የደርግ-ኢሠፓ ወንጀለኞች" እያለ ባለሟምንት በተራው ይዘፍንባቸዋል። በሠፈሩት ቁና መሰፈር አይቀርምና "እየመጣን ነው ደርሰናል" እያሉ ሮጠው የመጡትን እነልዑል ራስ፣ እነ ደጃዝማች፣ እነ ፀሐፊ ትዕዛዝን ቱባ ቱባውን ሰብስበው ካስገቡበት ጉረኖ ገቡ። "እኔ ሕሊናዬ ንፁሕ ነው።" እያሉ ቅያሪ ልብስ በሻንጣ ይዘው፣ የፂም መላጫና after-shave፣ የሚነበብ fiction ይዘው እየተግተለተሉ እንደዋዛ ገብተው እንደማይወጡ ሆነው ቀሩ። የወንድ ልጅ ሞቱ የሰራውን የረሳ ዕለት ነው ይላሉ አባቶች። የፊተኛው ሰረገላ መገልበጥ ለኋለኛው ሰረገላ ማስጠንቀቂያ ነው ይባላል። - የፀሐዩ ንጉሠ ነገሥት፣ የነልዑላን፣ የነመሣፍንት፣ የነመኳንንት ሰረገላ ዘውድ ጭና በግርማ ሞገስ ተሞልታ እንደአንበሣ ስትንጎማለል የምትገለበጥም አትመስል ነበር። አንድ ቀን ግን መሸባትና ቆመች። አክርካሪዋ ተቆምጦ ተገለበጠች። ተሳፋሪዎቿም ካባቸው ወልቆ ግርማ ሞገሳቸው ተገፎ ከአንድ ጉድጓድ ገቡ።

የደርግ ሰረገላም ግልቢያ ስትጀምር አንድ ቀን የምትገለበጥ ሳትመስል "ኢትዮጵያ ትቅደም" እየዘመረች "የፍየል ወጠጤ" እየፎከረች ተሽከረከረች። አምሮባት እየሰገረች፣ ሽምጥ ጋልባ ጋልባ ከአንዱ ስፍራ ላይ መሸባት። ተፈንችራ በአፍንጫዋ ቆመች። እናም ተገለበጠች። ተሳፋሪዎቿም መለዮአቸው ወልቆ ከአንድ ጉድጓድ ይገቡ እንደሁ እርሱ መድኃኒዓለም ያውቃል። ዛሬ ደግሞ የወያኔ ሰረገላ በዚያው ጎዳና እየሰገረች ነው። ሜዳው አልበቃ ብሎአት እየፈነጨች ትጋልባለች። - ካለፉት ሰረገላዎች መገልበጥ ምን ትማራለች? I doubt ጊዜውም ፋታውም ያላት አትመስልም።

. . . የትውልድ ክፍተት ያለ ይመስላል። ካለፈው ውድቀቱ መማር የማይችል፣ የነገን አርቆ ማሰብ የማይፈልግ ትውልድ! – ከስህተቱ ለመታረም ለመመለስ ፈቃደኛ ያልሆነ፣ እንደቆሰለ ጎልጃ (ከርከሮ) ከፊቱ ያገኘውን ሁሉ እየናደ ወደ መውደቂያው ገደል የሚሮጥ ትውልድ! – የዛሬዎቹ ባለጊዜዎችና አዲሱ ትውልድ ያለፈውን ሊያስተውሉ የሚችሉበት ሕሊና ኖሮአቸው ከዚህም ተምረው ቢሆን ያ ሁሉ የትውልድ ዕልቂት ከጥፋት ባልተቆጠረ ነበር። ሳይሆን ቀረና ስንት የሚሠራ ጎበዝ በግፍ አልቆ በአፅሙ ላይ "ፖሊስና–ሌባ" ድብብቆሽ እንጫወታለን።

ለመሆኑ እናንተስ እንዴት ናችሁ? በዚህ የከሳሽ ተከሳሽ ችሎት ላይ እንዴት ነው የምትደረጉት? ትከሰሳላችሁ? ወይስ ትካሳላችሁ? እንዴት ነው የሚሆነው? አትከሰሱ ነገር ርቃችኋል። ቢንጠራሩ ከማይደረስበት አሜሪካ ተጠግታችኋል። እንዳይቀርባችሁ ነገር ከዩኒቨርስቲ – ኮሌጅ እንቅስቃሴ ጀምሮ ከደርግ – ከኢማሌድህ – ከኢሠፓኮ – ከኢሠፓ – ከመኢሶን – ከኢዲዩ – ከኢሕአፓው ነበራችሁበት። ከቀይ ሽብር፣ ከነጭ ሽብር፣ ከነፃ እርምጃው፣ ከወያኔው፣ ከሻቢያው ከፊተኛው ከአሁኑም አብዮት አላችሁበት። – ቢያንስ ድንጋይ ወርውራችኋል! "ትፀድቅ ወይስ ትኮነን" ቢሉት ቆይ መከራ አስታውቅሃለሁ እንዳለው የአገሬ ሰው እስቲ ምከሩና አስታውቁን። እስከዚያው በቸር–ይግጠመን! የናንተው ወርቃየሁ ከኢትዮጵያ

የፊተኛው ሠረገላ መገልበጥ
ለኋለኛው ማስጠንቀቂያ ነበር !! አዲዮስ!!



የ
ፊ
ተ
ኛ
ው



ለ
ሚ
ቀ
ጥ
ለ
ው



# እንዲህ ሆነ

## በኢትዮጵያ የላንዳፍታ ወኪል የተጠናቀረ

## ተቃዋሚ ኃይሎች በመጪው ምርጫ እንዲሳተፉ ድርድር እየተደረገ ነው።

በመጪው ሚያዝያ ይካሄዳል ተብሎ በሚጠበቀው "የሕዝባዊ መንግሥት ማቋቋሚያ" ምርጫ ላይ ስለሚሳተፉበት ሁኔታ በተቃዋሚ የፖለቲካ ኃይሎችና በኢሕአዴግ መካከል ድርድሮች እየተካሄዱ ነው። በአሜሪካ ኮንግረስ ግብረ-ሃይል አደራዳሪነት በሚደረገው ውይይት ኢሕአዴግ ዋንኛ የተቃዋሚ ኃይሎች ከተባሉት የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር በግንባር ተገናኝቶ ይወያያል ተብሏል።

የውይይቱ ዋና ዓላማ በመጀመሪያ ደረጃ ተቃዋሚ የፖለቲካ ኃይሎች በፖለቲካው ሂደት ውስጥ በሰላማዊ መንገድ የሚሰሩበትን ሁኔታ ለመፍጠር ስምምነት ለማድረግ ሲሆን በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ በዋና ዋና ጉዳዮች ላይ በተከታታይ አዲስ አበባ ላይ ውይይቶችን ለማድረግ የሚያስችል ስምምነት ለማድረግ መሆኑን ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸው ምንጮች ጠቁመዋል።

በዚህ ውይይት ከተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች መካከል ኢዲኃቅ፣ ኢሕአፓ፣ የደቡብ ሕዝቦች ዲሞክራሲያዊ ኅብረት፣ ኦነግ፣ መድኅንና፣ መኢህድ እንደሚገኙ ታውቋል። በሽግግሩ መንግሥት በኩል አቶ ዳዊት ዮሐንስ የሚመሩት ቡድን የፕሬዚዳንት መለስ ልዩ መልዕክተኛ ሳይሆን እንደማይቀር ተገምቷል።

በመጪው ምርጫ ኢሕአዴግ ብቻውን ተወዳድሮ ማሸነፉ የኢትዮጵያን የፖለቲካ ሂደት እንዳያበላሸውና የደጋፊዋንም የአሜሪካንን ፖለቲካ እንዳይጎዳ በአሜሪካ ኮንግረስ ሥር የተዋቀረው ግብረ ኃይል ተቃዋሚ የፖለቲካ ኃይሎች በምርጫው እንዲሳተፉ ጥረትና ግፊት እያደረገ መሆኑም ከድርጅቶቹ አካባቢ ይነገራል። ሁሉም የተቃዋሚ ኃይሎች በመጪው ምርጫ የማይሳተፉ መሆናቸውን ገልፀው የአቋም መግለጫ ያወጡ ቢሆንም ከአሜሪካ መንግሥት በኩል ለሚደረግባቸው ግፊት በመጉበጥ አንዳንድ ተቃዋሚ ኃይሎች በምርጫው መሳተፍ ብልህነት መሆኑን ወደ ማመን ያዘነበሉ መሆናቸው ታውቋል። በተለይም ብዙዎቹ ድርጅቶች በሽብር ፈጻሚነት (Terrorist) ተራ እንዳይመደቡና መድረክ እንዳያጡ በመስጋት ከእምነታቸው ውጭ በምርጫው ሊሳተፉ እንደሚችሉ የፖለቲካ ታዛቢዎች ይገምታሉ።

ይህ ዓይነቱ አዝማሚያ በኦነግና በኢዲኃቅ ላይ መታየታቸውን አንዳንድ ምንጮች ጠቁመው በተለይም ኦነግ የሚያራምደው "የራስን ዕድል በራስ የመወሰን እስከመገንጠል" መርህ በሕገመንግሥቱ ውስጥ ምላሽ የተሰጠው ስለሆነ ያለማቅማማት በምርጫው እንዲሳተፍ ግፊት እየተደረገበት መሆኑ ታውቋል።

የኢትዮጵያ መድኅን ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ ሰሞኑን ባወጣው መግለጫው በአንድ ድርጅት የበላይነት በሚመራው የይስሙላ ምርጫ ውስጥ እንዲሳተፉ የአሜሪካ መንግሥት የሚያደርገው ግፊትና ተጽዕኖ ያሳሰበው መሆኑን ገልጾ ተቃዋሚ ድርጅቶች ለዚህ ስውር ደባ እንዳይንበረከኩ አሳስቧል።

በኮንግረሱ የተሰየመው ግብረ ኃይል ተቃዋሚ ድርጅቶች ምንም ዓይነት ቅድመ ሁኔታ እንዳያቀርቡ አቋም የወሰደ ሲሆን ይህም በፖለቲካ ድርጅቶቹ በኩል ሊቀርቡ የሚችሉትን የታሰሩ የፖለቲካ መሪዎች መፈታት፣ የፀደቀው ሕገ-መንግሥት መታገድ፣ የሽግግር መንግሥቱ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች ተግባራዊነት መቆም፣ ጋዜጠኞችንና የፖለቲካ ፓርቲ አባላትን የማዋከቡ ተግባር እንዲቆም ወዘተ ኢሕአዴግ ጨርሶ የማይቀበላቸው ስለሆነ ነው ተብሎ ይታመናል። በግብረ-ኃይሉ ውስጥ የተሰየሙት የአሜሪካ ባለስልጣኖች ኢሕአዴግንና የሽግግር መንግስቱን ፖሊሲዎች የሚደግፉና ቀናነት የሚጎድላቸው ናቸው ሲሉ የፖለቲካ ድርጅቶቹ ያማርራሉ።

በሌላ በኩል ከደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ዲሞክራሲያዊ ኅብረትና የኢትዮጵያ ብሄራዊ አንድነት ፓርቲ የተውጣጣው የጋራ የፖለቲካ መድረክ በመጪው ምርጫ እንዲሳተፍ ለቀረበለት ምርጫ ስምንት ቅድመ ሁኔታዎችን አቅርቧል። የጋራ የፖለቲካ መድረኩ ያቀረባቸው አብዛኞቹ ነጥቦች በግብረ-ኃይሉ መርህ የተሸፈኑ ስለሆነ በመጪው ምርጫ ለመሳተፍ የሚችልበት ሁኔታ ሰፋ ያለ እንደሚሆን ታዛቢዎች ይገምታሉ። ከዚህም ሌላ እውነተኛ የኢሕአፓ ተወካዮች ነን በሚሉ ወገኖች በምርጫው ውስጥ በተቃዋሚነት ለመሳተፍ በኢሕአፓ ስም እንቅስቃሴዎች በመደረግ ላይ መሆናቸውን የዜና ምንጮች ጠቁመዋል።

## የሊዝ ፖሊሲ ተግባራዊ ሆነ። የችርቻሮ መደብሮችም ለጨረታ ቀረቡ።

ለበርካታ ወራት ሲያወዛግብ የሰነበተው የሊዝ ፖሊሲ በአዲስ አበባ ከተማ ተግባራዊ መሆን ጀምሯል። በዚህም መሰረት በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙ ልዩ ልዩ ቦታዎች ለጨረታ ቀርበው ለሃምሣ ዓመታት በ14 ሚሊዮን ብር ጨረታ ለግል ባለሀብቶች ተከራይተዋል። በዚህ ጨረታ ለአንድ ቦታ 10 ሚሊዮን ብር የጨረታ ዋጋ አቅርበው ግማሹን በመክፈል የመጀመሪያውን ደረጃ የያዙት የበቀለ ሞላ ሆቴሎች አስተዳደር ሲሆን ሌሎች ግለሰቦችም 5 ሚሊዮን ብር በአንዴ በመክፈል ቁልፍ የሆኑ ቦታዎችን ተረክበዋል።

ይህ በዚህ እንዳለ በችርቻሮ ኮርፖሬሽን ሥር የሚተዳደሩ 30 የችርቻሮ መደብሮችና ታላላቅ

የሸቀጣ ሸቀጥ ሱፐር ማርኬቶችን በጨረታ ለመሸጥ መንግሥት ለተጫራቾች በጋዜጣ ጥሪ አድርጓል። በጠቅላይ ሚኒስትሩ ሥር የተቋቋመው የፕራይቬታይዜሼን ኤጀንሲ ይህንኑ እንዲያስፈጽም ኃላፊነት የተሰጠው ሲሆን በእነዚህ ድርጅቶች መሸጥ ምክንያት በድርጅቶቹ ውስጥ የሚሰሩት 3ሺ የሚሆኑ ሰራተኞችና የሚያስተዳድሯቸውም 15,000 ያህል የሚሆኑ ቤተሰቦቻቸው ለከፍተኛ ችግርና ረሃብ ሊጋለጡ እንደሚችሉ ተፈርቷል።

ተያይዞ በተላለፈ ሌላ ዜና በከተማ ቦታና ትርፍ ቤት አዋጅ ተወርሰው በኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት ሥር በመንግሥት ይዞታ የሚገኙትን ቤቶች በጨረታ ለመሸጥ የሚያስችል አዋጅ በተወካዮች ም/ቤት ፀድቋል። እንደምክርቤቱ አገላለጽ ከሆነ ቤቶቹን ለመሸጥ ያስፈለገበት ምክንያት መንግሥት ከቤት አስተዳደር እንዲወጣና በየጊዜው እያደገ የመጣው የቤት ፍላጎትና አቅርቦት ለማቀራረብ ነው ተብሏል። ቤቶቹን በመሸጡ ሂደት ተከራዮች የሽያጭ ቅድሚያና አስፈላጊው ድጋፍ እንደሚደረግላቸው የተጠቀሰ ሲሆን ተከራዮች መግዛት ያልቻሉትን በጨረታ በመሸጥ በካሣ ሕግ መሠረት ትርፍ ቤት ለተወረሰባቸው የቤት ባለቤቶች ሕጋዊ የካሣ ክፍያ እንደሚከፈላቸውም በተጨማሪ ተገልጿል። የቤቶቹን ሽያጭ የሚያስፈጽም የመንግሥት ቤቶች ሽያጭ አስፈጻሚ ጽ/ቤት በአዋጅ የተቋቋመ ሲሆን ተግባሩም በሚቀጥሉት ሶስት ዓመታት እንደሚጠናቀቅ ተገምቷል። ከአዋጅ ውጪ በቀላጤና በትዕዛዝ በመንግሥት ይዞታ ሥር የሚገኙ ቤቶች ለባለቤቶቻቸው የሚመለሱ መሆኑም ተገልጿል።

መንግሥት የሚያካሄደው የሊዝ ፖሊሲና ቤቶችን በጨረታ የመሸጥ ፖሊሲ አዲስ አበባን ጥቂት ባለሀብቶች እንዳይገዟት ስጋት ፈጥሯል። ከዚህም ሌላ አሁን ባለው የእያንዳንዱ ተከራይ የገንዘብ አቅም በበርካታ ነዋሪዎችና በቤተሰቦቻቸው ላይ ማኅበራዊ ቀውስ ሊያስከትል እንደሚችል ጉዳዩ ያሳሰባቸው ወገኖች በምሬት ይናገራሉ። በተለይም ደግሞ ሂደቱ በንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩትን ነጋዴዎች በቀጥታ የሚጎዳ መሆኑን በመጥቀስ ለረጅም ዓመታት የሰሩባቸውን የንግድ ቤቶች መልቀቅ የሚገደዱበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል ተብሏል። በመርካቶ የሚገኙ ታላላቅ የንግድ አውታሮችና መደብሮችን በራሱ ብሄረሰብ አባላት ወይም የንግድ ድርጅቶች እጅ ለማስገባት ኢሕአዴግ የሚያራምደው የዘረኝነት ፖሊሲ አካል ነው ሲሉ አንዳንድ ክፍሎች ኢሕአዴግን ያማርራሉ። ይህ በዚህ እንዳለ ከዋቢ ሸበሌና ከግዮን ሆቴሎች በቀር በመንግሥት ይዞታ ሥር የሚገኙት ሆቴሎችም በቅርቡ ለጨረታ ሳይቀርቡ እንደማይቀር ውስጥ አዋቂ የዜና ምንጮች ይጠቁማሉ።

## ፕሮፌሰር አሥራት ተጨማሪ ሶስት ዓመት ተፈረደባቸው

በዕውቁ የሕክምና ባለሙያና የመአህድ ፕሬዚዳንት በፕሮፌሰር አሥራት ወ/የስ ላይ የከፍተኛው ፍ/ቤት ሌላ ተጨማሪ 3 ዓመት እሥራት ፈረደባቸው። ፕሮፌሰር አሥራት ይህ ውሳኔ የተሰጠባቸው በ1985 ዓ.ም በደብረብርሃን ከተማ ለመአህድ አባላት፣ ለደጋፊዎችና ለአካባቢው ሕዝብ ባደረጉት ንግግር ሕዝብን አነሳስተዋል በማለት አቃቤ ሕግ ባቀረበባቸው ክስ መነሻነት ነው። ፕሮፌሰሩ በቀረበባቸው ክስ ምክንያት ለ84 ጊዜ በችሎት ፊት ቀርበዋል። ይህ ውሳኔ ከመተላለፉ በፊት ፕሮፌሰሩ በቀረበባቸው ክስ አልከራከርም በማለት ጠበቆቻቸውን ስለማሰናበታቸው ያቀረቡት ማመልከቻ የፍ/ቤቱን ክብር የሚዳፈር ነው በማለት የ6 ወራት እስራት የተፈረደባቸው መሆኑ ይታወሳል። የስድሳ ሰባት ዓመቱ አዛውንት ፕሮፌሰር አሥራት ወ/የስ እስካሁን በጠቅላላው የአምስት ዓመት ከስድስት ወራት እሥራት የተፈረደባቸው ሲሆን "የጦር መሣሪያ ይዞ ሽብር በማድረግና ጦርነት በማነሳሳት" ሌላ ክስ ተመስርቶባቸው ክሱ መሰማት የተጀመረ መሆኑም ታውቋል። በሌላ በኩል ፕሮፌሰር አሥራት ወ/የስ ከዓለም ዕውቅ የሰብአዊ መብት ተሟጋቾች አንደኛው ናቸው ሲል የጀርመን ድምፅ ሬዲዮ አወድሶአቸዋል።

## የኢትዮጵያ ሠራተኞች ኮንፌዴሬሽን ፈረሰ።

መንግሥት የወሰዳቸውን የኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራሞችን በመቃወም ለሽግግር መንግሥቱ እስጊ ሆኖ የነበረው የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበር ኮንፌዴሬሽን ሕጋዊ ዕውቅና ያገኘበት ምዝገባ መሰረዙን የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር አስታውቋል። ከዚህ ቀደም ሲል የማዕከላዊ ከፍተኛ ፍ/ቤት በሰጠው ውሳኔ ኮንፌዴሬሽኑም ሆነ ተገንጥለው በመውጣት የነፃ ሠራተኞች ማኅበር በሚል ስያሜ የተደራጁት ወገኖች ምንም ዓይነት እንቅስቃሴ እንዳያደርጉ በማዘዙ ኮንፌዴሬሽኑ የጠራው ጠቅላላ ጉባኤ አልተካሄደም። ይህ ውሳኔ እንደተላለፈ የኮንፌዴሬሽኑ ሊቀመንበር አቶ ዳዊ ኢብራሂም ከግቢው እንዳይደርሱና ጽ/ቤታቸውም በታጣቂዎች ቁጥጥር ሥር እንዲውል ተደርጓል። የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የኮንፌዴሬሽኑ ሕጋዊ ዕውቅና የተሰረዘው የኮንፌዴሬሽኑ ምዝገባ እንዲሰረዝና እንዲፈርስ አምስት ፌዴሬሽኖች ባቀረቡለት አቤቱታ መሆኑን ገልጿል። አምስቱን ፌዴሬሽኖች ይመሩ የነበሩት በአንጃነት የተገነጠሉት ክፍሎች እንደሆኑም ታውቋል። በሌላ በኩል አቶ ዳዊ ኢብራሂም ሰሞኑን ከአንድ ጋዜጣ ጋር ባደረጉት ቃለምልልስ በኮንፌዴሬሽኑ ላይ የደረሰው ተጽዕኖ መንግሥት በኮንፌዴሬሽኑ ውስጥ በሰገሰጋቸው ሰርጎ ገቦች አማካይነት የተፈጠረ ነው ሲሉ የሽግግር መንግሥቱን ኮንነውታል።

## ሕገ-መንግሥቱ ፀደቀ።
## የተቃውሞውና የድጋፍ ሠልፍ ተካሄደበት።

በአቶ ክፍሌ ወዳጆ በሚመራው የሕገ-መንግሥት አርቃቂ ኮሚሽን የተዘጋጀው ረቂቅ ሕገ-መንግሥት በኮተቤ በተካሄደው የሕገ-መንግሥት ጉባኤ ፀድቋል። ኢሕአዴግ 88% መቀመጫዎችን በያዘበት በዚህ ጉባኤ ሕገ መንግሥቱን ለማጽደቅ ይህን ያህል የጎላ ተቃውሞና ክርክር አላጋጠመውም። የመሬት ይዞታን፣ የብሔረሰቦች የራስን ዕድል በራስ መወሰን እስከመገንጠል የሚመለከቱ አንቀጾችና ሌሎች ለአገሪቱ ሕልውና ፈታኝ ይሆናሉ የተባሉት ጉዳዮች ያለአንዳች ችግር በጉባኤው ተቀባይነት አግኝተዋል። በጉባኤው ላይ ዋንኛ ተቃዋሚ ሆነው የቀረቡት በቀ.ኃ.ሥ. ዘመነ መንግሥት የፓርላማ እንደራሴ የነበሩት ሻለቃ አድማሴ ዘለቀና አቶ ዳንኤል የሚባሉ ከአዲስ አበባ የተወከሉ ግለሰብ ብቻ ነበሩ። በተለይም ሻለቃ አድማሴ ሕገመንግሥቱን እንዳለ በመቃወምና የብሄረሰቦች መብት እስከመገንጠል የሚፈቅደውን አንቀጽ በማውገዝ ሽንጣቸውን ገትረው ተሟግተዋል።




የሕገ መንግሥቱ ጉባኤ መሪዎች
አቶ አባተ ኪሻ የደቡብ ክልለ ፕሬዚዳንት
ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ የማስታወቂያ ሚኒስትር
አቶ አዲሱ ለገሠ የአማራው ክለለ ፕሬዚዳንት
(ሁሉም የኢህአዴግ አባላት ናቸው)

በአንፃሩም የሕወሓት (ወያኔ) የጀርባ አጥንት የሚባሉት አቶ አባይ ፀሐይ፣ አቶ ዓለምሰገድና ሌሎች የድርጅቱ ነባር ካድሬዎች ጉባኤውን ኢሕአዴግ በሚፈልገው አቅጣጫ ለማስኬድ አቢይ ሚና ተጫውተዋል። የውጭ ኢኮኖሚ ሚኒስትሩ ዶ/ር አብዱልመጂድ ሁሴንም የብሄረሰቦች መብት እስከመገንጠል የሚለው አንቀጽ እንዲፀድቅ ለማድረግ ዋና ተዋናይ ሆነው ታይተዋል። ይህ አንቀጽ በፀደቀበት ወቅት ጉባኤው ውይይቱን አቋርጦ ለተወሰኑ ደቂቃዎች ጉባኤተኞቹ በጭፈራ በዕልልታና በጭብጨባ ደስታቸውን ሲገልጹ ተስተውለዋል።



አቶ ዳንኤል በላይነህ ተቃውሞአቸውን ሲያሰሙ



ሕገ መንግሥቱን በመደገፍ የወጡ ሰልፈኞች (አንዳንዶቹ ለምን ፊታቸውን ይሸፍናሉ?)

በሌላ በኩል ጉባኤው በመካሄድ ላይ እንዳለ የአማራጭ ኃይሎች የጠራው ታላቅ የተቃውሞ ሠልፍ በመስቀል አደባባይ ተካሂዷል። 300,000 ይሆናል ተብሎ በተገመተው በዚህ የተቃውሞ ሠልፍ "አይሰራም ሕገ መንግሥቱ የደደቢቱ" "መለስን ከመውለድ ይሻል ነበር ማስወረድ፣ አንዲት ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኖራለች፣ ከፋፋዮችና የታሪክ አተላዎች ከምድራችን ይጥፉ" የሚሉ መፈክሮች ተሰምተዋል። በዕለቱ ለተቃውሞ ሠልፉ የወጣውን ሕዝብ የተመለከቱ ታዛቢዎች የኢሕአዴግ መንግሥት በእሣት ረመጥ ላይ እንደተቀመጠ ይቆጠራል ሲሉ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል። ከጉባኤው መጠናነቅ በኋላ ደግሞ በመንግሥት የተዘጋጀ የድጋፍ ሠልፍ ተካሂዷል። በተያያዘ ዜና አሜሪካንን ጨሮ ተቀማጭነታቸው በአዲስ አበባ የሆኑ 18 ኤምባሲዎች ሕገ-መንግሥቱን አጥብቀን እንደግፋለን ሲሉ አቋማቸውን ገልፀዋል።



ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ የጉባኤው ሰብሳቢ የጸደቀውን ሕገመንሥት ለፕሬዚዳንት መለስ ሲያስረክቡ

ከእነዚህ ኤምባሲዎች መካከል የካናዳ፣ የጀርመን፣ የጃፓንና የእንግሊዝ ኤምባሲዎች ይገኙበታል። ይህን የኤምባሲዎች አቋም የኢትዮጵያን ብሔራዊ ክብር የሚነካ ሲሉ የፖለቲካ ተቃዋሚዎች አጥብቀው አውግዘውታል። በሕገመንግሥቱ ውስጥ የጎላና ቁልፍ የሥልጣን ድርሻ የተሰጠው ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ስለሆነ ከሚያዝያው ምርጫ በኋላ ፕራዚዳንት መለስ ዜናዊ የጠቅላይ ሚኒስትርነቱን ቦታ እንደሚይዙ ይጠበቃል። የፕሬዚዳንትነቱ ቦታ ከአማራ ወይም ከኦሮሞ ብሄረሰብ እንደማያልፍ ሲገመት የፕሬዚዳንቱ ሥልጣን ከርዕሰ ብሔርነትና ከፕሮቶኮል ተግባሮች እንደማያልፍ ታውቋል።



ዶ/ር በየነ ጴጥሮስ ሕገ መንግሥቱን በመቃወም ለተጠራው ሕዝባዊ ስብሰባ መግለጫ ሲሰጡ



ሕገ መንግሥቱን በመቃወም የተደረገው ሕዝባዊ ስብሰባ በከፊል

## የቀድሞ መንግሥት ባለሥልጣኖች ለፍርድ ቀረቡ

በቀድሞ መንግሥት ባለሥልጣኖች ላይ የቀረበው የክስ ቻርጅ ከታህሣሥ 4 ቀን 1987 ዓ.ም. ጀምሮ ለአራት ተከታታይ ቀናት ተሰምቷል። ክሱ ይመለከታቸዋል ከተባሉት 73 የጊዜያዊ ወታደራዊ ደርግ አባላት መካከል 46ቱ ከችሎት ቀርበዋል። የተቀሩት በአገር የሌሉ፣ በሞት የተለዩና በጣሊያን ኤምባሲ የሚገኙ መሆናቸው ታውቋል። ከእነዚህም መካከል ሻለቃ ደመቀ ባንጃው፣ ሻ/ባሻ ከበደ አሊ፣ የ፶ አለቃ ማሞ እጅጉና የ፶ አለቃ አምባቸው ዓለሙ ከዚህ በሞት መለየታቸው ተረጋግጠ ስማቸው ከክሱ ዝርዝር ወጥቶአል።
በዕለቱ ከቀረቡት ተከሳሾች መካከል ዝቅተኛ ዕድሜ ያስመዘገቡት ሻለቃ መሳኩ ተፈራ ሲሆኑ የ፶ አለቃ አክሊሉ በላይነህና ኮ/ል መኩሪያ ኃይሌ ከ70 ዓመት በላይ እንዳላቸው ተመዝግቧል። ብዙዎቹ በስጋትም ይሁን በህመም አካላቸው የገረጀፈ መስለው ታይተዋል። የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር ሻምበል ፍቅረ ሥላሴ ወግደረስና ኮ/ል ተካ ቱሉ ህመም የሚሰማቸው መሆኑ በግልጽ ከፊታቸው ይታይ ነበር። ሻምበል ለገሰ አስፋው ከስተዋል፣ ጠቁረዋል። አብዛኞቹ ስራቸውንና አድራሻቸውን ሲጠየቁ ወህኒ ቤት የሚገኙ እስረኞች መሆናቸውን ሲገልጹ የጎንደር ክፍለሃገር ኢሠፓ 1ኛ ፀሐፊ የነበሩት ሻለቃ መላኩ ተፈራ ግን ስራቸውን "የኢሕአዴግ ዕድሜ ለማኝ እስረኛ" በማለት ለችሎቱ ገልፀዋል። በዕለቱ በኤሌክትሮኒክስ የመፈተሻ መሣሪያ ከመጠቀም አንስቶ ጥበቃውና ፍተሻው በእጅጉ ጠንካራ ነበር። ድሬዳዋ በሚገኘው የጅቡቲ ቆንስላ በዲፕሎማሲ ጠለላ ሥር የነበሩት የምዕራብ ሐረርጌ ኢሠፓ 1ኛ ፀሐፊ ሻምበል ተሰማ በላይ በዕለቱ በችሎት ላይ ቀርበዋል። ሻምበል ተሰማ በላይ ከተጠለሉበት የጅቡቲ ቆንስላ በታጣቂዎች ተገደው መወሰዳቸው ቀደም ብሎ በዜና ምንጮች ተዘግቦ ነበር። የአብዛኞቹ ተከሳሾች የዕለቱ ተቃውሞ በደረሱበት ወታደራዊ ማዕረጋቸው አለመጠራታቸው ነበር።

በቀድሞ ባለስልጣኖች ላይ የቀረበባቸው ክስ የሰው ዘር ማጥፋትን፣ በሰብአዊ ፍጡር ላይ የተፈፀመ ግድያንና አካላዊ ስቃይን የሚመለከቱ ወንጀሎችን የሚያጠቃልል ሲሆን በ269 ገጾች ታትሞ ቀርቧል። ይህን መሰሉ ክስ ሲቀርብ በኢትዮጵያ ታሪክ በዓይነቱ የመጀመሪያው መሆኑ ሲታወቅ ከ1945ቱ የኑምበርግ ችሎት በኋላም በዓለም አቀፍ ደረጃ ሁለተኛ ነው።

በቀድሞ ባለሥልጣኖች በግፍ ተገድለዋል ከተባሉት መካከል የቀድሞው ንጉሥ ቀ.ኃ.ሥ፣ እነ ፀሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሐ/ወልድ፣ እነ ብ/ ጄኔራል ታደሰ ብሩ፣ እነ ብ/ ጄኔራል ጌታቸው ናደው፣ ኮ/ል አጥናፉ አባተ፣ አቡነ ቴዎፍሎስ፣ እነ አቶ ኃይሌ ፊዳ፣ እነ ፀሐፊ ትዕዛዝ ተፈራ ወርቅ ኪዳነወልድ፣ የእነ ብ/ጄኔራል ተፈሪ ባንቴ፣ የቄሴ ጉዲና ቱምሳ፣ የእነደጃዝማች አሰጋኸኝ አርአያና የደራሲ በዓሉ ግርማ ስም በክሱ ቻርጅ ውስጥ ተገልጾአል።

እንደ አንዳንድ ወገኖች ዕምነት ሕወሓት በጦር ሜዳ ከመንግሥት ጋር ሲዋጋ የወደቁበትን ታጋዮች ደም ለመቀበል በቀድሞ መንግሥት ባለሥልጣኖች ላይ "ዘርን የማጥፋት" ወንጀል መመሥረቱን በመጥቀስ ሕወሓት የሚመራው የሽግግር መንግሥት ይህን ለማድረግ ብቁ አይደለም ይላሉ። ዘርን በማጥፋት ወንጀል ፕሬዚዳንት መለስም ሆኑ የሽግግር መንግሥቱ ባለስልጣኖች ከተጠያቂነት አያመልጡም ሲሉ በአሶሳ፣ በበደኖ፣ በአሰቦት ገዳም፣ በአርባ ጉጉና በተለያዩ ከተሞች የተደረጉትን የዘር ማጽዳት ፍጅቶችን ይልቁንም በአሶሳ በአማርኛ ተናጋሪዎች ላይ የተካሄደውን ዕልቂት ይጠቅሳሉ።

## የመሣሪያ ቁርቋስና ግጭቶች አሁንም አልበረዱም።

የሽግግር መንግስቱን በመሣሪያ ኃይል ለመታገል ወደ ትጥቅ ትግል ያዘነበሉ የተቃዋሚ የፖለቲካ ኃይሎች እንደመበራከታቸው መጠን በአገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች የሚደረጉ የመሣሪያ ቁርቋሶችና የተቃዋሚዎች የትጥቅ ትግል በየማዕዘኑ መጠናከሩን የተለያዩ የዜና ምንጮች ዘግበዋል።

በሰሜን ሸዋ መንግሥት ከአካባቢው ነዋሪዎችና ገበሬዎች ጋር "ሽፍታ ትቀልባላችሁ። መእህድን ትደግፋላችሁ" በሚል ምክንያት የተፈጠረው ግጭት አለመብረዱን ከአካባቢው የሚደርሱ ዜናዎችና የዓይን ምስክሮች ይገልፃሉ። በደቡብ ጎንደር በአዲስ ዘመን፣ በወረታና በነፋስ መውጫ የመንግሥት ሰራዊት የአካባቢውን ነዋሪ ትጥቅ ለማስፈታት ያደረገው እንቅስቃሴ ከፍተኛ ተቃውሞ እንደገጠመውም ታውቋል።

በእነዚህ አካባቢዎች ለበርካታ ጊዜ ትጥቅ ለማስፈታት አሰሳና ፍተሻ መካሄዱ የሚታወቅ ሲሆን 'የመንግሥት ሰራዊት ዋና ትኩረትም በአካባቢው በስፋት የሚንቀሳቀሱትን የጄኔራል ኃይሌ መለስን እንቅስቃሴ ለማዳከም እንደሆነ ይገመታል።

በምሥራቅ ጎጃም በሞጣና በቢቡኝ ወረዳዎች የሚገኙ አርሶ አደሮች ከሽግግር መንግሥቱ ጋር ባደረጉት ግጭት ከ6 ያላነሱ የመከላከያ ሠራዊት አባላት መገደላቸውና በርካታዎቹንም ማቁሰላቸውን ከአካባቢው የደረሱት መረጃዎች ይጠቁማሉ። በጎንደር፣ በሰሜን ሸዋና በጎጃም ገበሬዎች ላይ የሽግግር መንግሥቱ ወታደሮች የሚያካሂዱት ግድያ፣ አፈናና እስራት ሕዝቡን ለባሰ አመድ ሊያነሣሣ እንደሚችል የፖለታካ ታዛቢዎች ያስጠነቅቃሉ።

በምዕራብ የአገሪቱ አካባቢዎችና በምሥራቅ በተለይ በሐረርጌ የኦነግ ሠራዊት ከፍተኛ ወታደራዊ እንቅስቃሴ ማድረጉንና ድል እየቀናው መሆኑንም ኦነግ በተከታታይ በሚያወጣቸው መግለጫዎቹ አስታውቋል። ኦነግ አገኘሁት የሚለው ወታደራዊ ድል በሌላ የዜና ምንጭ ያልተረጋገጠ ቢሆንም በተጠቀሱት

አካባቢዎች ግጭቶች መኖራቸውን የዓይን ምስክሮች ይናገራሉ። ከዚህም ሌላ በምሥራቅ ሐረርጌ የምትገኝ ቆቦ የምትባል አነስተኛ ከተማ ጥር 13 ቀን 1987 ዓ.ም ሌሊት ማንነቱ ባልታወቀ ታጣቂ ኃይል ቁጥጥር ሥር ውላ እንደነበር አንድ የዜና ምንጭ ዘግቧል። በነፍስ ወከፍና በከባድ መሣሪያ ተደግፎ ከሌሊቱ 9:00 ጀምሮ ከተማይቱን ለአጭር ጊዜ የተቆጣጠረው ታጣቂ ኃይል በሰው ህይወትና በንብረት ጉዳት ማድረሱንና ለጊዜው ቁጥራቸው በውል ያልታወቁ ሰዎችን ይዘው መሰወራቸው በተጨማሪ ተዘግቧል። በተያያዘ ዜና ከፍተኛ አለመረጋጋትና የጦርነት ስጋት በሚታይበት በኦጋዴን ክልል በቀብሪደሐር ከተማ የክልሉ ሽማግሌዎች፣ የፖለቲካ ድርጅቶች መሪዎችና ባለሥልጣኖች የተገኙበት ስብሰባ ተካሂዷል። በስብሰባው ላይ ፕሬዚደንት መለስ ተገኝተው ንግግር ያደረጉ ሲሆን የስብሰባው ዋና ዓላማ በክልሉ ውስጥ የሚንቀሳቀሱትን የፖለቲካ ድርጅቶች በመጪው ምርጫ ላይ እንዲሳተፉ ለማግባባት ሳይሆን እንደማይቀር ተገምቷል። በሌላ በኩል የኦሮሞ ነፃነት እስላማዊ ግንባር (ኦነእግ) ሊቀመንበር ጃራ አባገዳ በቅርቡ በባሕረ-ሰላጤው የእሥልምና አገሮች ጉብኝት ካደረጉ በኋላ ለአንድ የአረብኛ ጋዜጣ በሰጡት ቃለ-ምልልስ ድርጅታቸው በሚያካሂደው የትጥቅ ትግል ድል እያገኘ መሆኑን ገልፀው ከእስላሙ ዓለም ድጋፍ ማግኘታቸውንና የጦርነት ይዞታቸውንም በሐረርጌ ውስጥ በሚገኙ ከተሞች ላይ እንደሚያተኩሩ ተናግረዋል።

ለእነዚህና ለሌሎችም የተቃዋሚ ኃይሎች መግለጫዎች ከመንግሥት በኩል የተሰጠ ማስተባበያ የለም። ይሁን እንጂ በታህሣሥ ወር መጨረሻ ከድሬዳዋ ወደ አዲስ አበባ ይጓዝ በነበረ የመንገደኞች ባቡር ላይ ተኩስ ተከፍቶ 4 ሰዎች መሞታቸውንና ከሃያ የሚበልጡ መቁሰላቸውን መንግስታዊ ምንጮች ይፋ አድርገዋል።

## በመጨረሻ የደረሰን የተቃዋሚ ኃይሎችን ከኢህአዴግ ጋር ለማደራደር የተደረገው የአሜሪካ ምክር ቤት ሙከራ

በአሜሪካ ምክር ቤት የአፍሪካ ንዑስ ኮሚቴ በተቋቋመው ግብረኃይል አማካይነት በተቃዋሚ ኃይሎች ተወካዮችና በኢህአዴግ ተወካዮች መካከል ፌብሩዋሪ 6-9 ውይይት መካሄዱ ታውቋል። በሚስተር ሃሪ ጆንስተን ሊቀመንበርነት፣ በአሜሪካ መንግሥት ባለሥልጣኖችና በዓለም አቀፍ ዕርዳታ ሰጪ ድርጅቶች፣ በካርተር ማዕከልና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ተወካዮች በታዛቢነት በተገኙበት በዚህ ውይይት የተሳተፉት ተቃዋሚ ኃይሎች የመላው አማራ ድርጅት፣ ኢድኃቅ፤ የደቡብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ዴሞክራሲያዊ ቅንጅትና ኦነግ እንደሆኑ ታውቋል። የኢህአዴግን ተወካዮች የመሩት አቶ ዳዊት ዮሃንስ ነበሩ። የምክር ቤቱም ግብረኃይል፤ ድርጅቶቹም ስብሰባው ካበቃ በኋላ መግለጫዎች አውጥተዋል። ኢድኃቅን ባለፉት ሶስት ዓመታት በኢህአዴግ የወጡትን ደምቦች ህጎች እንዲሁም በቅርቡ ያጸደቀውን ህገመንግሥት እምናና ተቀብሎ ቢሮዎች ለመክፈት፣ በምርጫ ለመሳተፍ በሌሎችም ጉዳዮች ካለው መንግሥት ጋር ውይይት ለማካሄድ እንደሚችል ኢህአዴግ ቢገልጽም ደምቦቹም ሆኑ ህገመንግሥቱ ያለ ህዝባዊ ተሳትፎ በኢህአዴግ የቀረበ በመሆኑ ይህን እምኖ መቀበል ስለማይቻል የቀረበውን ሃሳብ ድርጅታቸው እንደማይቀበል ተወካዩ ዶክተር ሙሉጌታ ሥዩም ገልጸዋል። ከድርጅቶች ጋር በተናጠል የሚደረገውንም ውይይትና ስምምነት መሠረታዊ መፍትሄ ሊያስገኝ እንደማይችል ኢድኃቅ ያሳሰበ ሲሆን ይፈቱ ያላቸውን የፖለቲካ እስረኞችንም ጉዳይ የኢህአዴጉ ተወካይ "በወንጀል የተከሰሱ እንጂ የፖለቲካ እስረኞች በመንግሥት እጅ የሉም" በማለት ከደዋል።

የመላው አማራ ህዝብ የዕርዳታና የልማት ማህበር ባወጣው መግለጫ ከመላው አማራ ድርጅት ማዕከላዊ ኮሚቴ የተላከውን ደብዳቤ በተወካዩ በዶክተር ገብርዬ ወልደ ሩፋኤል አማካይነት ያቀረበና ማንኛውንም ዓይነት ድርድር ለመጀመር የሚችሉት የድርጅቱ ፕሬዚዳንትና የአመራር አካላት ከኢህአዴግ ቁጥጥር ነፃ ሲሆኑና በአባላት ላይ የሚደርሰው ሰቆቃ ሲገታ ብቻ መሆኑንና የሁሉም ድርጅቶች ተሳትፎ ሲኖርበት ብቻ መሆኑን ለጉባኤው ያስረዱ መሆኑን ይገልፃል።

ድርጅቶቹ ያወጡት መግለጫዎች ባይደርሱንም ከአደራዳሪው የአሜሪካ ምክር ቤት ግብረ ኃይል 1ኛ. የደቡብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ድርጅትን በተመለከተ ያወጣው መግለጫ እንደሚገልጸው፣ *"The parties agreed for the re-creation of a multi party forum to address issues of funding, mass media use, and other issues of party concerns"* ይልና *"the parties also agreed to estabilish a bilateral committee to address issues vital to the success of Ethiopia's democratization.* ብሎ ይህ ለመከናወኑ የታዛቢዎችን በጊዜያዊነት በስብሰባዎች ላይ መገኘት መስማማታቸውን ከጠቆመ በኋላ *"The parties agreed to continue discussions in Addis Ababa before the end of February to estabilish the composition of this committee."* ብሎ ይዘጋዋል። የዶክተር በየነ ጴጥሮስ፣ የአቶ ዳዊት ዮሃንስ፤ የሃሪ ጆንስተንና የአምባሳደር ዴቪድ ሺንን ፊርማ የያዘ መግለጫ ነበር።

2ኛ. ኦነግን በተመለከተ የአቶ ዲማ ኖጎ ፊርማ የታከለበት መግለጫ እንደሚጠቁመው፤ "The OLF maintained that in Ethiopia today there is no rule of law to gurantee respect for basic rights and fundamental freedoms. Therefore, discussions without preconditions and in the presence of third parties regarding mechanisms for guranteeing respect for basic democratic norms are the first necessary step." ይላል።

በአጠቃላይ ውይይቱ ይህን በመሰለ ሁኔታ የተገባደደ ሲሆን ለዚሁ ጉባኤ ያልተጠራው የመድህን ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ February 10, 1995 ባወጣው መግለጫ አራቱ የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ከወያኔ ብቸኛ ተወካይ ጋር ያደረጉትና በፊርማቸው ያፀደቁት ውይይትና ድርድር የኢህአዴግን የፖለቲካ ሥርዓት በይበልጥ የሚያጠናክር ነው በማለት ይከሳቸዋል።

# ሀናና ብንያም
# የልብስ ስፌትና ዲዛይን
# H & B TAILORING

የሠርግ የሚዜ ልብሶች በትዕዛዝ እንሠራለን።

ጤፍ ዱቄት
በሶ
እልበት
ቡና
በርበሬ
ሚጥሚጣ
ሽሮ
ቅመም በያይነቱ
በተጨማሪ
- የቪዲዮ ካሴቶች
- የቴፕ ካሴቶች
- የተለያዩ መጽሄቶች

**ወለላ ወርቁ**
**WOLELA WORKU**

LEMO SERVICE
ለሠርግና ለልዩ ዝግጅት
የሌመዚን አገልግሎትም
እንሰጣለን።
1-800-679-1816
Pager- 738-7783

**የተለያዩ የአገር ባህል ልብሶች እንሸጣለን።**

431 North Indian Creek Rd
Suite E
Clarkston, GA 30021
Phone: (404)296-2766
Pager - 632-6283

**ቆንጆ ጤፍ እንጀራም እንሸጣለን ጎብኙን!**

---

## ሰለሞን ተድላ




## Solomon Tedla
Certified Public Accountant
የተመሰከረለት የሂሳብ ሥራ ሙያተኛ
**Master of Business Administration ( M.B.A)**

ለአስተማማኝ የታክስና የፋይናንስ አገልግሎት
የታክስና የፋይናንስ ሥራ ባለሙያ
ሲ ፒ ኤ - ኤም ቢ ኤ

*Over 10 years of business & professional experience*
*For Reliable business Consultation*
*& Tax Return Preparation*

***Phone - (404)955-7551***

በተጨማሪ ለተቋቋሙ ሆነ አዲስ ለሚቋቋሙ
ንግዶች ምክርና ዕቅድ
ለማንኛውም ዓይነት የታክስ ሥራ
በተለይ ሪዬል ስቴት፣ ንግድና
የመሳሰሉት ላሉዋቸው

---

## H. GLENN FOGLE JR.

Attorney At Law
Suite 507. The Grant Building
44 Broad Street, N.W.
Atlanta, GA 30303

Office: (404) 522-1852
Facsimile: (404)522-9933

**ግሌን ፎግል**

**የህግ ጠበቃ**

የኢሚግሬሽን ጉዳይ
በሥራ ላይ ጉዳት
ወንጀል ነክ ጉዳዮች

የአሳይለም፤ የዘመድ ማስምጣት፣
የሥራ ፈቃድ
የመሳሰሉትን የኢሚግሬሽን ጉዳዮች
ይደውሉልን

# ??? አንድ ጥያቄ አለኝ ???

• ከአሁን በኋላ ስድስት ዓመት ሙሉ ከወያኔ አመራር ጋር እንዴት መኖር ይቻላል?
* ከአሁን በፊት ለአራት ዓመት እንደኖርከው።

——

• እንዲያው ደርሶ ጦር ምዘዝ ምዘዝ ይለኛል። ምን አባቴ ባደርግ ይሻለኛል?
* እግዚአብሔር ምሕረቱን ያውርድልህ።

——

• አሁን ሕገመንግስቱ አልቆ ያ መከረኛ ምርጫ እስኪደርስ ድረስ ደግሞ በምን እንደበር ይሆን?
* ችሎት መከታተል አትወድም? የቀድሞ ሹማምንት ለፍርድ እየቀረቡ አይደል!

——

• ምነው ሀገሩ ሁሉ ሴት ብቻ ሆነብኝ?
* እናቶችን መጠየቅ ነው። ወንድ መውለድ አቁመው እንደሁ?

——

• ለሚቀጥለው ምርጫ ከኢሕአዴግ ጋር ለመወዳደር ከአሜሪካ ይመጣል የሚባለው ማን ነው?
* ስሙ የገነነው ይመጣል ተብሎ ይጠበቃል።

——

• በሕገ መንግስቱ ጉባዔ በብዙ መቶ የሚቆጠሩ ተሳታፊዎችን እናያለን። የሚናገሩት ግን ጥቂት ናቸው። ሌሎቹ ምን ሲሰሩ ይውላሉ?
* ሲያዛጉና ሲያንቀላፉ ነዋ!

——

• የሕገ መንግሥት ጉባኤተኞች ሆነው በጉባኤው መሃል የሚያንቀላፉ ምን ይባላሉ?
* ያመኑበትን የሚሰሩ ዘዴኞች።

——

• እነዚህን የግል ጋዜጠኞች እንዳላይ የት ልሂድ?
* ጋቢ የሚያክለው አዲስ ዘመን ጋዜጣ በየኪዮስኩ ሞልቶልሃል ለብሰሽው ተኛ።

——

• ይሄ ለውጥ ለውጥ የሚባለው ምን አዲስ ነገር ተገኝቶ ነው?
* ኢሕአዴግ ኢሠፓን መተካቱ መች አነሰ።

——

• በሕገ መንግስት ጉባኤ ላይ ሁለት ተቃዋሚዎች ብቻ ናቸው የሚታዩት። ይህቺ ናት "ያልተገደበ ዲሞክራሲ" የተባለችው?
* ለፕሮፓጋንዳ መች አነሰች?

——

• አንዲት ዘወትር ሱሪ ከምትታጠቅ ልጅ የዓይን ፍቅር ይዞኛል። ማነጋገሩን ግን ፈራሁ። እንዴት ይሻላል?
* ሱሪህን እርሷ ስለታጠቀችው እርሷው እስክትጠይቅህ ጠብቅ።

——

• ኢሕአዴግ በቀ.ኃ.ሥ እና በደርግ ዘመን ያልታየውን ዲሞክራሲያዊ ሕገ መንግስት ሲሸልመን ምን እንበለው?
* ቀበሮ ባቀች ይበሉት።

——

• ባለቤቴ ከሠራተኛ ጋር ሲማግጥ አግኝቼ ብገድለው ኃጥያት ይሆንብኛል ትላላችሁ?
* መፍታት ሳለ መግደልን ምን አመጣው?

——

• "እኔስ ባሌ ይሙት የሰለቸሁት" የምትለው ዘፋኝ ጤነኛ ናት ትላላችሁ?
* እኛ ዘንድ አልታከመችም።

——

• የደርግ ባለሥልጣኖች ፍ/ቤት መቅረባቸውን ሰማሁ። የሆነስ ሆነና የነበራቸው ማዕረግ ለምን ተቀናነሰ?
* ለሩዋንዳ ዘማቾች ታድሎ ይሆናል!

——

• ኢሕአዴግ አዲሲቷን ኢትዮጵያ የዳቦ ቅርጫት፣ የዲሞክራሲ ደሴት እንደሚያደርጋት ትምክህተኞች የምታምኑት መቼ ነው?
* ያልወለድኩት ልጅ አባባ ቢለኝ አፌን ዳባ ዳባ አለኝ አሉ።

——

• የተወረሰ ቤታቸው እንዲመለስላቸው ሠልፍ ይወጡ የነበሩ ሰዎች የት ደረሱ?
* ቤት እያሉ ሲሮጡ ጫማቸው አልቆ አሳረፋቸው።

——

• ሶስት ዓመት ከምናምን የገዙን ጠቅላይ ሚኒስትር ቢሮአቸው ለጋዜጠኞች ክፍት መሆኑን የተናገሩት ሰሞኑን ምን ሰምተው ይሆን?
* ጠቅላይ ሚኒስትርነቱ የመጨረሻቸው መሆኑ ተነግሯቸው ይሆናል።

——

• ሠላማዊ ፖለቲካ እያሉ ወንዱን ሁሉ አልጫ ከሚያደርጉ ለምን ወጣ ብለው ጥይት አያጮሁም?
* የሆነውስ ሆነና እርስዎ ከየትኛው ኩሽና ነው የሚፎክሩት?

——

• ሆዳም በበዛበት አገር ስለአገራችን ማሰቡ ይዘገንነኛል። እነዚህን ሆዳሞች ምን ብናደርግባቸው ይሻላል?
* ጨጓራቸውን ማስገልበጥ።

——

• በሚመጣው አዲስ የመንግሥት መዋቅር ሥልጣን የጠቅላይ ሚኒስትሩ ከሆነ ፕሬዚዳንት ለምን አስፈለገ?
* ለጠቅላይ ሚኒስትሩ አጫዋችነት።

——

● ፕሬዚዳንታችን በዚህ በፀደቀው ሕገመንግሥት የሚደሰቱ ይመስላችኋል?

* ለምን አይደሰቱ? ከምንም ተነስቶ አሥር ዓመት መግዛት ቀላል ነው?

——

● እባካችሁ አንድ ዘናጭ ፌዝ ንገሩኝ።

* በዚህ ዓመት ፕሬዚዳንቱ በፈቃዳቸው ጠቅላይ ሚኒስትር ይሆናሉ።

——

● አንዳንድ የማይረቡ መጽሄቶችና ጋዜጦች ለምን ውሸት ይሸጣሉ?

* አንዳንድ የማይረቡ ሰዎች ለምን ውሸት ይገዛሉ?

——

● የዚህ ዘመን ዘፈን አልጥመኝ አለ። ምነው?

* ለቅሶው አመዝኖ ይሆናል።

——

● ፍቅር ሲጠና እንዴት ያደርጋል?

* ቆሎ ያጎራርሳል።

——

● ፕሬዚዳንት መለስ ምነው ድምፃቸው ጠፋሳ?

* የጠቅላይ ሚኒስትርነት ሥልጣናቸውን እያሰላሰሉ ይሆናል።

——

● ጩኸትና ዳቦ በርካሽ የሚገኙት የት የት ነው?

* ጩኸት መስቀል አደባባይ፣ ዳቦው ቤተመንግስት ሞልቷል።

——

● የማያገሱ ያረጁ አንበሶችን ለማየት የ6 ኪሎው አንበሣ ግቢ ሰው የሚንጋጋው ለምንድነው?

* ልክ እንደአንተ ራሱን በአንበሶቹ ውስጥ ለማየት።

——

● የደርግ ኢሠፓ ከርሰ መቃብር የት ነው የሚገኘው?

* የኢትዮጵያን ሬድዮን ጠይቅ። እሱ ነው አሉ ያቃበረው።

——

● ጥላሁን ገሠሠ "ስትሄድ ስከተላት" እያለ መዝፈኑን ትቶ "እግዚአብሔር ይመስገን" እያለ የሚያዜመው መቼ ይሆን?

* የሚከተላትን ሲደርስባት ነው?

——

● ፓርቲ ማቋቋማችንን ለሕዝብ ይፋ አድርጉልን።

* መግለጫው ይላክልን።

——

● ለፖስታ መግዣ ብር ይላክልን።

* ለመሆኑ ምን የሚባል ነው ስያሜው?

● የኢትዮጵያ ጮካዎች አነቃናቂ ፓርቲ።

——

● የኢትዮጵያ አየር መንገድ እየተበረበረ በቁሙ ከሚያልቅ እዚሁ ሁኖ የኤርትራውያን የአየር አገልግሎት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ኩባንያ ቢሉት አይሻልም?

* ሩጫውና አሽቅድምድም ወደዚያው ሳይሆን ይቀራል?

——

● ተቃዋሚዎች ለምን በሚያዝያው ምርጫ አይሳተፉም?

* ማጨብጨብ ስላልፈለጉ ይሆናላ!

——

● የቅስጠንጥንያው ቅዱስ በርቶሌሚዎስ "በተለይ ዲሞክራሲው አበረታች ነው" ማለታቸው አይገርምህም?

* የዘንድሮ ጳጳስ ሁሉ እግዚአብሔርን ትቶ ፖለቲከኛ ሆነ ማለት ነው!

——

● አንዲት ልጅ ወድጄ እንደ እናቴ ነው የምወድህ ስትለኝ ከርማ ፍቅር ካስያዘችኝ በኋላ ዘጋችኝ። ምን ትመክሩኛላችሁ?

* ነገሩ ያለቀው እንደ እናቴ እወድሃለሁ ያለችህ ጊዜ ነው። እርምህን አውጣ።

——

● የአሁኑን ሕገ መንግሥት ስብሰባ ከደደቢቱ የሚለየው በምንድነው?

* አዳዲስ የወያኔ አባላትን መጨመሩና በተሟላ የስብሰባ አዳራሽ መካሄዱ!

——

● ሥራ አጣሁ። ምን ይለኛል?

* ግንባርዎ ላይ ጫር ጫር አድርገው ወደ ክልል 'አንድ' ያዝግሙ።

——

● እኚህ ግብዖች ድሮ ያላነሱትን የአባይንና የዴር ሱልጣን ጥያቄ ምነው አነሱት?

* አረማመዱን አይተህ ጭብጦውን ቀማው ይባል የለ!

——

● የኤርትራ ኤምባሲ ወደ ሽሮ ሜዳ ከፍ ብሎ ከአሜሪካን ኤምባሲ ጎን ሊሆን ነው ይባላል። ምን ይመስላችኋል?

* አሜሪካ ኤምባሲ እየተመላለሱ ነዳጅ ከሚጨርሱ አንደኛቸውን ጠጋ ቢሉ ይሻላል።

——

● በሕገ-መንግስቱ ላይ ተሳትፎ የሚያደርጉት ከአሥር አይበልጡም። ሌሎች ለምን አስፈለጉ?

* ለማጨብጨብና እጅ ለመስቀል። ሲያስፈልግም ለስድብና ለዳንስ!

——

● ወያኔ ማለት ትርጉሙ ምንድነው?

* "በትነህ ጥፋ" ሳይሆን አይቀርም!

——

# ሁለተኛው የውጫሌ ውል ተፈረመላችሁ ! !

ከዶ/ር ሥዩም ገላዬ

## ቀዳማዊው የውጫሌ ውል ያደረሰው ችግር

ለረሳችሁት የውጫሌ ውል ኢትዮጵያችንን የቅኝ ግዛት ለማድረግ ጣልያኖች የተጠቀሙበት አንዱ የረቀቀ ስልታቸው ነበር። ኢትዮጵያ የምትባል የጥቁር የረዥም ጊዜያት ታሪክና ባህል ያላት አገር፣ ከአውሮፓና ከአሜሪካ መንግሥታት በፊት ተፈጥራ ለጥንት የግሪክ፣ እስያ፣ እንዲሁም ሌሎች ሃገሮች የፍልስፍናና የሥልጣኔ ምንጭ ሆና ለብዙ ዘመናት መቆየቷ አውሮፓውያንን ያስቆጣል። ስለዚህም የአውሮፓዋ ጣልያን በጊዜው አፍሪካ ውስጥ ቅኝ ግዛት ስላልነበራት የሮማን መንግሥት የበላይነት ለማረጋገጥ በታሪክ ትልቅ የነበረችውን ኢትዮጵያን በቁጥጥሯ ሥር ለማድረግ ታጥቃ ትነሳለች። ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋርም የውጫሌ ውል የተባለውን «የልማትና የመተባበር» ስምምነት ለመፈራረም ቆርጣ ትነሳለች።

የውጫሊው ውልም በአማርኛና በጣሊያንኛ ቋንቋዎች ይዘጋጅና በሁለቱ የመንግሥት ተወካዮች ተፈርሞ ይፀድቃል። በኋላም ውሉ ባጣልያንኛው ቋንቋ የተደበቀ አሻሚ ሐረጎች ሆን ተብለው ተጨምረውበት ኖሮ ከጊዜ በኋላ የጣልያን ፍላጎት ቁልጭ ብሎ ይወጣል። ይኸም መሰሪ ዕቅድ የኢትዮጵያን ፖለቲካ፣ ኤኮኖሚ፣ ባህልና ልምድ በጣልያን ቁጥጥር ሥር ለማድረግ የታቀደ እንደነበረ ግልፅ ይሆናል። ይኸ አዝማሚያ እንደታወቀ፣ ኢትዮጵያ በኢጣልያንኛ የተፃፈው ሰነድ እንደ አማርኛው ሆኖ እንዲስተካከል ትጠይቃለች። ይህም ሊሆን ባለመቻሉ ኢትዮጵያ የውጫሌውን ውል እንደማትቀበል ታስታውቃለች።

የታላቋን የሮማን መንግሥት አንዲት የጥቁር ሃገር አልቀበልም በማለቷ የጣልያንን መንግሥትና መሰሎቿን በጣም ያስቆጣል። ከዚያም ማስፈራራቱና ዛቻው እየተጠናከረ ይመጣል። ኢትዮጵያ ግን ፍንክች ስላለች የውጫሌውን ውል እንዳፈረሰች ተነግሮ ጦርነት ይታወጅባታል። የሮማዋ መንግሥት በጦርነት ኢትዮጵያን ልታስገብር ስትወስን ብዙ የአውሮፓና የአሜሪካ መንግሥታት ወዳጇ ቿ በተዘዋዋሪም ሆነ በቀጥታ የቁሳቁስ፣ የሃሳብ፣ እንዲሁም ይፋ የፖለቲካ ድጋፍ ለጣልያን ይሰጣሉ። የጣልያን መንግሥትም ይህችን በኢኮኖሚ ወደኋላ የቀረች ሃገር «የማሠልጠን ጉዞ» በማለት ወረራዋን ማለትም የአድዋውን ጦርነት ታስነሳለች። የኢትዮጵያ ሕዝብም በታንኩ ጋጋታ፣ በመትረየስና በባዙቃው እሩምታ ሳይደናገጥ ሃገሩን ለመከላከል ቆርጦ በአንድነት ይነሳል። ኢትዮጵያዊው ጀግናም ያለው ውኸግራውን፣ የሌለውም ጋሻና ጦሩን አንግቦ ሊወረው የመጣውን የጣልያን ወታደር በግንባር ይጋፈጠዋል። ይኸ ኃያል የተባለው የሮማው ወታደር ባልጠበቀው ሁኔታ እየተመታ ብትንትኑ ይወጣል። ውርደት የተከናነበው የጣልያን ጦርም ቢያፈገፍግም እንኳን «እምቢ ለሃገሬ፣ እምቢ ለወገኔ» ብሎ የተነሳው የኢትዮጵያ ጦር በማያዳግም ሁኔታ ለጣሊያኖች ትምህርት ይሰጣል። የጣልያኑም ጦር በብዛት አልቆ ሌላውም ተማርኮ ኢትዮጵያ የበላይነቷን በድርጊት ለዓለም ሁሉ ታስታውቃለች። የውጫሊው ውልም በማያዳግም ሁኔታ ተሰርዞ ኢትዮጵያ አንድነቷን ታረጋግጣለች። ይኸ ነው እንግዲህ የኢትዮጵያ አንዱ ታሪኳ። ስለዚህም ነው በጊዜው በነጭ ቁጥጥር ሥር በባርነት ቀንበር ውስጥ ለነበሩት አፍሪካውያን ኢትዮጵያ የነፃነታቸው አርማ የሆነችው።

## ዳግማዊው የውጫሌ ውል የሚፈጥረው ጣጣ

አሁን ደግሞ ለሁለተኛ ጊዜ በቅርቡ በድጋሚ ሌላኛው «የውጫሊ ውል» አዲስ አበባ ውስጥ ተፈርሟል። ይኸኛው ውል ግን «የውጫሊ ውል» መባሉ ቀርቶ «የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት» ተብሎ ተሰይሟል። እንደሚታወቀው የቀድሞው «የውጫሊ ውል» በኢትዮጵያና በጣሊያን መንግሥታት መሃከል ቢፈረምም፣ ይኸኛው ግን የፀደቀው የኢትዮጵያ ቆዳ በለበሱ እምባ ገነንና በቀበሮ ባህታዊ አጨብጫቢ ደቀ መዛሙርቶቻቸው መካከል ነው። ይኸኛው ውል በይዘቱ ከቀድሞው «የውጫሊ ውል» በምንም አይለይም። የኢትዮጵያን ሕዝብ በአስተዳደር፣ በባህል፣ በልማት፣ በቁጥጥራቸው ሥር ሊያደርጉት፣ የጀመሩትንም የንብረትና የገንዘብ ዘረፋቸውን «ሕጋዊ» ለማድረግ የሞከሩበት «የውል ሰነድ» ነው። በአማርኛና በላቲን ፊደል ቢፃፍም ቋንቋው ግን ጣልያንኛ አይደለም። በሮማው መንግሥትም ተደጋግሞ እንደተሞከረው ኢትዮጵያን በጎሣ፣ በሃይማኖት፣ የመከፋፈሉን ሙከራ ይኸኛውም «የውጫሌ ውል» ሕጋዊ ሊያደርግ ይሞክራል። ኢትዮጵያን በጎሣ ክልል ከፋፍሎ፣ ጎሣና ብሄረሰብ አንድ እንደሆኑ በማስመሰል፣ «የጎሣ ነፃነትን እስከ መገንጠል ድረስ» ብሎ ኢትዮጵያችንን ለመበታተን ሙከራው ተጀምሯል። አንዳንድ ሥፍራዎችም ውስጥ የመገነጣጠሉ ሁኔታ እንዲፋጠን እርምጀ ተወስዷል። «የሮማ ተወካይ መሪዎች» ጂጂጋ ሄደው ሕዝቡን ሲቀሰቅሱ «ማን ኢትዮጵያዊ እንድትሆኑ ጠየቃችሁ?» «የዲሞክራሲ ዕውቀታችሁን ለአማራው አስተምሩት» ብለው ያደረጉትን ንግግርና የሴይድ ባሬን (ነፍሳቸውን ይማራትና) ብሄራዊ መዝሙር

እንዲዘመርና የታላቋ ሶማልያ ዕቅድ በሥራ ላይ እንዲውል ያደረጉትን ቅስቀሳ ማንም ኢትዮጵያዊ አይረሳውም። አቶ መለስ፣አቶ ስዬ፣ አቶ ታምራት ላይኔ ጊዜው ሲደርስ በሕዝብ ተወካዮች ፍርድ ቤት ቀርበው የኢትዮጵያ ሕዝብ ይፋረዳቸዋል። የአማርኛው ተናጋሪ በቀድሞው የአገዛዝ ሥርዓት በደል እንዳልደረሰበት ሁሉ፣ በአስተዳደር ጉድለት እንዳልተጨቆነ ሁሉ፣ ይህን ጭቁን ወገን የኢትዮጵያ ጠላት አድርጎ ለማቅረብ የሚደረገውን ጥረት ዘፋኙ እንዳለው «ታሪክ ይፈርደዋል»። አማርኛና ትግሪኛ ተናጋሪው ሕዝብ ሥረ መሠረቱ አንድ፣ ባህሎቹም መንትያዎች መሆናቸው ከታሪክ አምድ ተፍቆ አንዱ ጠላት ሌላው ወዳጅ እንደሆነ ተደርጎ የሚለፈፈውን ማንም ኢትዮጵያዊ ይቅር አይለውም። አማርኛም ከኦሮሚኛ፣ ጉራጊኛ፣ ሱማሊኛ፣ ከምባትኛ፣ ትግሪኛ ጋር የተካለሰ ዲቃላ ቋንቋ መሆኑ ተዘሎ የጠላት ቋንቋ ሆኖ ቀርቦ አምባ ገነን መሪዎች የሚያኮሩውን በራሱ ፊደል የተደገፈውን የኢትዮጵያ ቋንቋ ጥለው በኮሎኒያሊዝም ሳቢያ ያደገውን ፊደልና ባህል ማለትም የላቲኑን ፊደል እንድናጠናና ልጆቻችንንም እንድናስተምር ሽር ጉዱን በሰፊው ተያይዘውታል።

የአዲሱ «ውጫሌ ውል» አስፈፃሚዎች በኅላ. ያከፋፈሉትን ሕዝብ በላቲን ፊደል መፃፍ ከቻለ ከዚያም በእንግሊዝኛ ቋንቋ መኮላተፍ ከያዘ ሥልጣኔ ወዲያው ስለሚያጥለቀልቀው በአጭር ጊዜ ውስጥ ጨረቃ ጋ ሊደርስ ይችላል ይሉናል። ይህን የትም ሊሠራ የማይችል መንገድ ተልመው የሚያደነቁሩንን አወናባጆች ለመበታተን ያሴሩልን መንገድ የሚያራርቅና በበለጠም ወደኋላ እንደሚጎትተን የነቃንባቸው መሆናችንን በሚገባቸው ቋንቋ እንዳንነግራቸው ጣልያንኛ አንችልም። የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ለማሳደግ መንገዱ ይህ አይደለም። በመጀመሪያ የማንኛውንም ግላዊ ኢትዮጵያዊ መብት የሚያረጋግጥ የሕዝቡ ተጠሪና ግለሰቡ በዴሞክራሲያዊ መንገድ የሚመረጠው ካላስፈለገም ሕዝቡ ሊያሰናብተው የሚችለው መንግሥት ኢትዮጵያ ያስፈልጋታል። ይህንንም ለማድረግ እነኚህ ወንበዴ አምባገነኖችንና አጃቢዎቻቸውን ማባረር ያስፈልጋል። በኋላም የምናርገው እርምጃ ኢትዮጵያችንን ከዓለም ለማኝነት፣ ወደ መፅዋችነት፣ አምባገነኖች የሚጨፍሩባት ሳትሆን ሰላምና ዴሞክራሲ የሰፈነባት ሃገር እንድትሆን ተባብረን የመሠረት ድንጋይ መትከል ነው። አሁን የተጀመረው የሁለተኛው የውጫሌ ውል አብዛኞቻችንን በጎሣ በሃይማኖት ከፋፍሎ የተበጣጠሱ ትናንሽ ሃገሮች በኢኮኖሚያቸው ዳካማ፣ በጦርነት ሃይላቸው «ሌሶቶንና ስዋዚ ላንድን» የሚያክሉ እንደ «የባቢሎን ግንበኞች» በቋንቋ የማይግባቡ በዚያውም ላይ ጠላት እንዲሆኑ የሚዘጋጁ ሃገሮችን በደቡቡ ኢትዮጵያ ለማቋቋም እንደሆነ ያልተገነዘበ፡እስከአሁን ካለ አውቆ የተኛ ስለሆነ ለማስነሳት ላንቃችንን አናደርቅም። አሁን የተጀመረው ዘረፋም እስከ ተቻለ ድረስ ይቀጥልና «ነፃዋ ሃገር ኤርትራ» ምንአልባትም የደቡብ ጎረቤትም ትግራይ በኢትዮጵያ አመድ ላይ ተንዘራፍጠው ለመቀመጥ የታሰበ የሁለተኛ የውጫሌ ወራሪ ባንዳዎች ያቀዱት ቅዠት ነው።ይህ ባይሆን ለምንድነው የኢትዮጵያ አየር መንገድ ለኤርትራ የሚሰጠው?እቅዱ ይህ ካልሆነ ለምንድነው የኢትዮጵያ ጥሬ ሃብት ወደ ውጭ ተሸጦ የውጭ ምንዛሬ ኤርትራ እንድታካብት የሚደረገው? «ኃያሏ ኤርትራ» የተበታተነውን የደቡብ መንደሮች ሥንጋጭ በጦር ኃይሏ ዝም እያሰኘችን፣ እንደፈረንሣይና እንግሊዝ የቅኝ ገዥዎች ጣልቃችን እየዘለለች በመግባት ልታስገብረን ትመኛለች። ተመልከቱት የሁለተኛው የውጫሌ ውል አስፈፃሚዎች እንዴት ዓይነት ቅዠታሞች እንደሆኑ። ለቱርክ፣ ለጣልያን፣ ለእንግሊዝና ለአረብ ያላገለገለው ዕቅድ ለነሱ ይሰራል ብለው ተያይዘው ለመጥፋት በመቁረጣቸው እንዴት የሚታዘንላችው ናቸው።

ማንም ኢትዮጵያዊ በመላው ሃገሩ ውስጥ ተዘዋውሮ መሥራቱ ሃገራችንን በሞላ ይጠቅማል። እስኪ ተመልከቱት፤ ጊንር፣ ባኮ፣ ሁመራ፣ ፋርሲ፣ ዕምድብር፣ ፎገራ፣ አዲግራት፣ ሚዘን ተፈሪ፣ ቀላፎ እንዲሁም ሌሎች የቀሩት ትናንሽ አካባቢዎች ከዚያ አካባቢ ጎሣ ላልሆነ ኢትዮጵያዊ ዝግ ከሆኑ የሚደርሱትን ችግሮች። የተማረ ኃይል በነፃ ሃገሩ ውስጥ እንዳይዘዋወር ያግዳል። የኢኮኖሚ እንቅስቃሴም ስለሚታገድ ንግድ በየቦታው አይስፋፋም። ሃብት ካለበት ወደሌለበት ተዘዋውሮ የልማት እንቅስቃሴዎች መስፋፋታቸውን ያግዳል። በየሰፈሩ የተወለዱና ቋንቋውን እንናገራለን የሚሉ አምባ ገነኖችን ፈጥረን የእድሜ ልክ ንጉሶች እንዲሆኑ ያደርጋል።

በተለይ በአሁኑ ጊዜ አሜሪካ ድንበሯን ለካናዳ፣ ለሜክሲኮና ለሌሎችም የጎረቤት ሃገሮች ስትከፍት፣ አውሮፓውያኖችም የድንብር ክልላቸውን እያደበዘዙ በኢኮኖሚ የሰለጠነ ኃይል ጉልበታቸውን የተለያዩ የተፈጥሮ ሃብቶቻቸውን አንድ ላይ በማቀናጀት በአንድ ላይ እንዲበለፅጉ ጥረቱ በተስፋፋበት ወቅት፣ የኢትዮጵያ ጠላቶች ሃገራችንን የበሬ ግንባር በምታክል ክልል እንድትበጣጠስና ደህንታችንን እንድንቀጥልበት የሚያደርጉትን ደባ ስለነቃንባቸው ምን አለ ቢለቁን። በከፍተኛ ትምህርት ላይ ለሚደረገው የመከፋፈል ዘመቻ እዚህ ላይ ሊጠቀስ ይችላል። በቅርቡ አዲሱ የዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶ/ር ዶሪ እንዳሉት የዩኒቨርሲቲው የምርምር ጥናት መዳከሙን ጠቅሰው ይህም የሆነበትን ምክንያት ሲያብራሩ «የውጭ አገር ተወላጅ የሆኑ አስተማሪዎች ችሎታ በሌላቸው ኢትዮጵያውያን በመተካታቸው ነው፤» ብለዋል። እንግዲህ ዩኒቨርሲቲአችንን በአውሮፓውያን፣ እስያውያን፣ አሜሪካውያን እና ካናዳውያን አስተማሪዎች ሊሞሏት ነው። ተመልከቱት እንግዲህ ሁለተኛው የውጫሌ ውል በሥራ ላይ ሲተረጎም። ትምህርት ከባህል፣ ከልምድ ጋር ተያይዞ ህብረተሰብን መለወጥ እንደሌለበት ሁሉ፣ ከኢትዮጵያ ጋር የባህል የልምድ፣ ወግ ቋንቋ ጋር ግንኙነት የሌላቸው እንግዳ መጦች መምህራን ኢትዮጵያ በሰፊው ገብተው በማይገባን ቋንቋ

ስለሮማ ታላቅነት፣ ስለአሜሪካ «እስቶክ ኤክስቼንጅ» ስለ እንግሊዝ ትምህርት መራቀቅ እንድንለፍፍ እየተፈረደብን ነው።

እንደምታውቁት ቀደም ሲል ኢትዮጵያ ውስጥ የተማረ ሰው መለኪያ ፈረንሣይኛ ቋንቋ ማኮላተፍ ነበር። የመንግሥት ትምህርት ቤቶች ውስጥም የፈረንሣይን ባህልና ቋንቋ አስተማርን፣ የሊሴ ገብረማርያምንም ትምህርት ቤትም አቋቋምን፤ ጥረቱ ከሃገራችን ባህል ጋር ስላልተያያዘ በልማት በኩል የፈረንሣይ ባህል መስፋፋቱ አብዛኛውን ኢትዮጵያዊ ካለበት እንዲንቀሳቀስ አላደረገውም። በኋላም እንግሊዞች ይበልጣሉ ተብሎ ኢትዮጵያ ውስጥ ባህላቸውን እንዲያስፋፉ በሩፍ ተከፈተላቸው። ትምህርቱ በሞላ በእንግሊዝኛ ለዚያውም በውጭ ሰው እንዲሰጥ የብዙ ዘመናት ዘመቻ ተደረገ። በዚህም የተነሣ መጠነኛ ቁጥር ያላቸው ኢትዮጵያውያን በዚሁ ቋንቋ ይኮላተፋሉ። አሁንም ትምህርታችንን ከኢትዮጵያዊው ሰፊው ሕዝብ ምኞት ተስፋ፣ ባህል ጋር ስላላገናኘን ካለንበት ፈቀቅ አላልንም። ተማረ ተብየውም ኢትዮጵያዊ፣ ጣልያናዊ፣ ግሪካዊ፣ አሜሪካዊ ስለሆነብን የተማረውን ባህሉን ይዞ ሲደነፋ የገበሬው መሣሪያ አስተሳሰቡ የህብረተሰቡ ድርጅቶች ማለትም እቁቦች ደቦዎች እድሮች ህጋዊና የተሻሻሉ የሕዝቡ ድርጅቶች አልሆኑም። ተማርኩ ባዩ የአሜሪካ ኢኮኖሚ መራቀቁን ሲለፍፍልን የኢትዮጵያዊው ንግድ የእድገት እንቅስቃሴ ባለበት ረገጠ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ግብር ከመክፈል በስተቀር ጥቅሙን የሚያስጠብቅለት መሪ ለመምረጥና ለማስወረድ አልቻልም። ,

ህብረተሰብን ለመለወጥ እድገቱ መጀመር ያለበት ሕዝቡ ካለበት ደረጃ እንጂ በአየር በሚንሳፈፉ ሃሳቦችና በሕዝቡ ምኞት፣ ተስፋ፣ ፍላጎት ባህል ላይ ባልተመሰረቱ የንግድ ሃሳቦችና ድርጊቶች በመመራት አይደለም። ብዙዎቻችን እንደምናውቀው ሰማንያ አምስት ከመቶው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚተዳደረው በእርሻ ሥራ ነው። ገበሬውም እራሱ በሰራው የእርሻ እቃ በመገልገል፣ የበሬና የሰው ሃይል በመጠቀም በቆሎ፣ ጤፍ፣ ሥንዴ፣ ማሽላ፣ ምሥር፣ ባቄላ፣ አተር፣ አደንጓሬ፣ ሰሊጥ፣ ሱፍ፣ ቡና፣ በርበሬ፣ ተልባ እያመረተ ነው። ይኸም አሰራሩ ለብዙ ዘመናት ሳይቀየር እንዳለ ነው። ባለፉት ሃምሣ ዓመታት «በዘመናዊ የእርሻ ሥራ» ኢትዮጵያውያንን አሰልጥነን መጠነኛ የእርሻ ተቋሞችንም በውጭ ሰዎች እርዳታና የጉልበት ኃይል መሠረትን። የገበሬው አሰራርና «ዘመናዊው የእርሻ» አሰራር «ፊትና ጀርባ» ስለሆኑ የኢትዮጵያ ገበሬ በቂ እህል ማምረት አልቻለም።በእርሻ ተቋሞች ውስጥ የሚሰጡትን የትምህርት ዓይነቶችንና የምርምር ጥናቶች ብናይ የኢትዮጵያ እርሻ ችግር ቁልጭ ብሎ ይገባናል። በመጀመርያ ነገር ገበሬው የእርሻ ባለሙያዎችን ደመወዝ ቢከፍልም የመቅጠር፣ ካልተስማማውም የማባረር ሥልጣን የለውም። ስለዚህም ካናዳ፣ እንግሊዝ፣ ፈረንሳይ፣ ጣልያን፣ አሜሪካ የተማረው የእርሻ ምሁር ውጪ የተማረውን ሃሳብ ከድርጊቱ ጋር ከኢትዮጵያ ሁኔታ ጋር ግንኙነት በሌለው መሥመሩ ይጀምራል። ስንታችሁ ታውቃላችሁ የአሣማ እርባታ ጥናት ኢትዮጵያ ውስጥ ይደረግ እንደነበረ? የኢትዮጵያ ጥራጥሬና እህል ብዙዎቹ ተረስተው የተለያዩ የእህል ዓይነቶች የግጦሽ ሳሮች አይነቶች ከውጭ ገብተው ለኢትዮጵያ ይጠቅሙ እንደሆን ሙከራ እየተደረገ ነበር። ኢትዮጵያ የተለያዩ የጋማና የቀንድ ከብቶች ቢኖራትም ከውጭ ስላልመጡ ብዙዎቹ ተንቀው ተትተዋል።

በሌላው የኢኮኖሚ ዘርፍ ማለትም፣ በንግድ፣ በትምህርት በሶሻል እድገቶች በኩል የተማረው ከሕዝቡ ጋር አልተገናኘም። ስለዚህም ኢትዮጵያችን አንዷ ኋላ ቀር ሃገር ሆናለች። ይህ ገብቶን አስተዳዳራችንን ለመለወጥ ስንዘጋጅ አምባገነኖች ሃገራችንን ይዘው ከበፊቱ የባሰ አዘቅት ውስጥ ኢትዮጵያን ለመወርወር እየተዶለተብን ነው። የአሁኑን የባሰ የከፋ ሥርዓት አጥፊነት ሌሎች ማብራሪዎች በመመልከት እንገንዘብ።

የእንግሊዝ፣ ፈረንሣይና ጀርመን አሜሪካ መሠረታቸው አንድ ቢሆንም የሕብረተሰብ ዕድገታቸው ግን ከየግለ ሃገሩ ባህል ልምድ ፍላጎት ስሜት ጋር ተዛምዶ ነው ያደጉት። የክቡር አቶ ከበደ ሚካኤልን «ጃፓን እንደምን ሠለጠነች» መፅሃፍን ብናነብ ጃፓኖች የራሳቸውን ባህል በማሻሻል አደጉ እንጂ ሌሎችን ለመምሰል በመሞከር ጊዜ አላጠፉም። እሥራኤል በቅርቡ በመንግሥትነት ስትነሳ ሕዝቧን ለመለወጥ የቀየሰችው በጣልያኑ፣ ወይንም በአረቡ መንገድ አይደለም። የኛዎቹ ገዥዎች ግን «ላቲኖች» ሁኑ፣ በእንግሊዝኛ ተኮላተፉ እያሉ የሚያወናብዱን ደባ የሞላው ተንኮል መሆኑ ግልፅ መሆን አለበት። የገና በዓላችንን በጥጥ የተሸፈነ ጥድ አቁመን እናከብርም። ጉንጨ ወፍራሙ ሆደ ጎተራው የነጮች የገና አባት ከኛ ጋር ግንኙነት የለውም። ከባህላችንና ከልምዳችን ያልተያያዙ እርምጃዎች ከቆዳችን አልፈው የሰውነታችን አካል ሊሆኑ አይችሉም። የኢትዮጵያ ዜጋ ማለት በእንግሊዝኛ፣ ፈረንሣይኛ፣ ጣልያንኛ የሚኮለተፍና እንደነሱው እያሰበ በነሱ ባህል መንገድ የሚኖር አይደለም። ኢትዮጵያዊ ማለት ቋንቋው፣ ሙዚቃው፣ ቅርሳ ቅርሶቹ፣ እምነቱ ሕዝባዊ ተቋሞቹ አንድ ላይ የሚያሰባስቡት እንጂ የሚበታትኑት አይደለም። ዘረኞች፣ ጎሰኞች፣ ያልተገነዘቡት ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ደማችን ውስጥ አጥንታችን መሃከል ሥር ሰድዶ የገባ ስለሆነ በቀላሉ የምንለያይና ኢትዮጵያም የምትጠፋ አለመሆኗን ነው። አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ ባንዲራችንም ለጊዜው መሳለቂያ እንድትሆን ብትደረግም ጠላቶቻችን እስከተባረሩ ድረስ በመንፈሳችን ውስጥ፣ በኋላም በመላው ኢትዮጵያ ውስጥ በከፍታ ሥፍራ ተሰቅላ ትውለበለባለች፣ የነፃነታችንና የአንድነታችን ዓርማ ሰንደቅ ዓላማችን በመሆኗ። በተጠነሰሰው ተንኮል የተነሳም በራሱ ፊደላት የተደገፈው ኢትዮጵያዊ ቋንቋችን (አማርኛ) አይጠፋም፣ ኢትዮጵያውያን የውጭ ጠላቶቻቸውን መቋቋም ልምዳቸው ስለሆነ።

## መደምደሚያ

ኢትዮጵያችን የሦስት ሺህ ዓመት ታሪክ ያላት ሃገራችን በመሆኗ ያኮራናል። የሰው ዘርና ሥልጣኔው የተጀመረው አውሮፓና እስያ ውስጥ እንደነበረ በማስመሰል የውጭ ጠላቶቻችን ለብዙ ጊዜ ዓለምን በሞላ ቢያወናብዱም «እውነት ስለማትጠፋ» እውነቱ ወጥቶ ኢትዮጵያችን የሰው ዘርና የሥልጣኔው ምንጭ መሆኗ ሲረጋገጥ ኢትዮጵያውያንን፣ የደስታ ሲቃ አስይዞናል። ከዚህም ሁሉ ከሚጓጓለት ታሪካችን እንካፈልም የሚሉ ወንበዴዎችንም «ፌንጣ ብትቆጣ እግሯን ጥላ ሄደች» የተባለውን ተረት እንተርትባቸዋላን። በጎሪጥ የሚያያቸውን የኢትዮጵያን ሕዝብ የሁለተኛውን "የውጫሌ ውል" ካልጠጣህ እያሉ እረፍት ስላሳጡት በህቡዕ መሰባሰቡን ወኸኘግራውንም መወላወሉን ጀምሯል። የኢትዮጵያውያን ቻይነትና አመዛዛኝነት እንደፍርሃት ወስደው ጠላቶቻችን መሠሪ ድርጊቶቻቸው ከቀጠሉ ግን «የቅድመ አያቶቻቸው» እጣ እንደሚደርስባቸው መላው ዓለም መገንዘብ አለበት። ከዚያም በክቡር አቶ መለስ ዜናዊና አጫፋሪዎቻቸው የተጫነብንን ሁለተኛ የውጫሌ ውል አስወግደን፤ የኢትዮጵያውያንን የግለሰብ ፍላጎት የሚያሟላ ዴሞክራሲያዊ መንግሥት በኢትዮጵያ ሕዝብ ይቋቋማል። ኢትዮጵያም በታሪክ አርማነቷ ለዘለአዓለም ትኖራለች። ጠላቶቿና ደንገጡሮቻቸውም ለሁለተኛ እንደገና ኩም ይላሉ። የሁለተኛው የውጫሌ ውልም፤ እንዳለፈው በማያዳግም ሁኔታ ይደመሰሳል።

---

ዶ/ር ሥዩም ገላዬ ጆርጂያ በሚገኘው በፎርት ቫሊ እስቴት ኮሌጅ የእርሻ ምርምር ጣቢያ አሶሺዬት ፕሮፌሰር ናቸው።

---

# ወይዘሮ ሕዝብ አየሽ አምባው

## 1930 - 1986



ወይዘሮ ሕዝብ አየሽ አምባው ከአባታቸው ከበላምበራስ አምባው ነጋሽና ከእናታቸው ከእማሆይ አባተች ተሰማ በ1930 ዓ.ም. በጎንደር ክፍለ ሀገር በጭልጋ አውራጃ ልዩ ስሙ ፈፈሪ ኪዳነ ምህረት በተባለው ቦታ ተወለዱ። ስነምግባርን፣ አኩሪ ዘይቤን፣ አስተዋይነትን፣ መንፈሳዊነትን፣ የቤተሰብ ፍቅርንና በቃል ኪዳን መጽናትን ከወላጆቻቸው በመቅሰም፤ በተጨማሪም የመንፈሳዊና ዘመናዊ ትምህርት በመማር ያድጋሉ። የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውንም ጎንደር ከተማ በሚገኘው ጻድቁ ዮሐንስ ትምህርት ቤት ያጠናቅቃሉ።

ወይዘሮ ሕዝብ አየሽ ለአካለ መጠን እንደደረሱ ውድ ባለቤታቸውን አቶ ታከለ ዳኘውን በማግባት ስድስት ልጆች በማፍራት ዘጠኝ የልጅ ልጆች ለማየት በቅተዋል። ለኢትዮጵያውያን ሴቶች በአርአያነት ሊያስጥቅሳቸው ከሚችለው ባህርያታቸው ሁሉ ለቤተሰብና ለወገን ያላቸው ፍቅር፣ ታማኝነታቸውና ፈሪሃ እግዚአብሄርነታቸው ነው። ወይዘሮ ሕዝብ አየሽ አምባው በአገራቸው ብቻ ሳይወሰኑ ወደ ቅድስት ኢየሩሳሌም ከአስራ ሁለት ጊዜ በላይ የተጓዙ ሲሆን ከባለቤታቸውና ከልጆቻቸው ጋር እግረመንገዳቸውን በአውሮፓ በአሜሪካና በካናዳ ጉብኝቶች አድርገዋል።
ወይዘሮ ሕዝብ አየሽ አምባው ባደረባቸው ህመም በአገርና በውጭ አገር ሲታከሙ ቆይተው ስላልተሻላቸው ጥር 13 ቀን 1986 ዓ.ም. ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተውናል።

ልብወለድ

# የዴብራ ጦስ

(በእውነተኛ ታሪክ ላይ የተመሠረተ ልብወለድ)

## ከገረሱ

### ክፍል አስራ አንድ

### የመጨረሻው መጨረሻ

ቀደም ሲል በካሣሁንና በፈጠነ መካከል የነበረው ክርክር እየቀነሰ መጣ። አንዱ ሌላኛውን አሸናፊ ሆኖ ሳይሆን ሁለቱም ለየራሳቸው ትክክል ነው ብለው ያምኑባቸው የነበረው ነገሮች ሌላ መልክ ይዘው በማየታቸው ነው።

ካሣሁን ከዴብራ ጋር ያለውን ግንኙነት አቋርጦ ከራሄል ጋር ወዳጅነቱን አጠናከረ። ከዴብራ ጋር የነበረውን ግንኙነት ለማቋረጥ ቀላል አልነበረም። እቤቱ እስሬ እየደወለች ስትቆጣው፣ አንዳንዴም ስትለማመጠው፤ እቤት ይኖራል ብላ በምትገምትበት ሰዓት እየመጣች ስትጨቀጭቀው ይኸው ዘዴዋ አላዋጣ ብሎአት በመጨረሻም ታስፈራረው ጀመረች። አንድ ምሽት ከሥራው ተመልሶ የራሄልን ስልክ በሚጠባበቅበት ሰዓት ዴብራ መጣችና በሩን በኃይል አንኳኳች።
እሷ መሆኗን ተረዳና ተነስቶ ከፈተላት። በትህትና ሰውን መቀበል አብሮ አደግ ባህሉ ሆኖና ከበሩ ሊያባርራት አልቻለም። ስትገባ አገባቧ ሁሉ የሚያስፈራ ነበር። እንደገባች ኮቷን አውልቃ ሶፋው ላይ ወረወረችና ሽንጧን በሁለት እጆቿ ይዛ በቁጣና እልህ በያዘው ሲቃ ታየው ጀመር።

«ቁጭ አትይም እንዴ?» አላት ፍርሃት ፍርሃት ብሎታል።

«አልቀመጥም፤ ደግሞ ልንገርህ እንኳን አንተ ማንም እኔን Dump ማድረግ አይችልም፤» አለችው ዓይኗን አፍጣ።

«ቁጭ በይ እንጂ» አላት። ከእሷ ራቅ ብሎ በመሄድ ከካውቹ ሌላ ጥግ ላይ ቁጭ አለ።
«ብቀመጥ ባልቀመጥ It is non of your business» አለችው።

«እሺ አሁን ምን እድርግ ነው የምትይኝ?» አላት በርግጥ ጨንቆት ነበር። እንደሷ አይገነፍል፣ አይጨህ አይቆጣ ነገር፣ ያለመደበት የማያውቀው ባህርይ ነው። ዝም ብሎ አይተው ነገር ሁኔታው እየከረረ መጣ። በዋዛ አትለቀውም።

«የምታደርገውን ታውቃለህ? እኔ ካንተ ጋር ጊዜ ያጠፋሁት አንተ ስትፈልግ እንዳንድ ቡቱቶ ጨርቅህ ሲበቃህ አውልቀህ እንድትጥለኝ አይደለም። ይህ አገር የሁሉም መብት የሚከበርበት አገር ነው ቢገባህ።»

«እኔ ስሜቴ ሲቀዘቅዝስ፣ ምን ማድረግ እችላለሁ?» አላት አሁንም ለስለስ ብሎ።

«የኔ አልቀዘቀዘማ!» አለችው።

«I am sorry ምንም ማድረግ አልችልም። I hope ይህ hurt እንደማያደርግሽ» አላት።

«Hurt የማያደርግሽ ትለኛለህ ደግሞ!» በቁጣ ወደ ፍሪጁ ሄደችና የሚጠጣ ነገር በብርጭቆ ይዛ መጣች።

«ከዚህ በላይ ምን ታደርገኛለህ። ስማ በቀላሉ የምለቅህ እይምሰልህ» አለችው በቁጣ።

ካሣሁን ትእግሥቱ እያለቀ መጣ። ከመቀመጫው ተነሳ፤ «እንግዲህ ነግሬሻለሁ በትዕግስት ላስረዳሽ ሞክሬአለሁ። ትዕግስት ደግሞ ወሰን አለው» አላት ወዲያው ስልኩ ተደወለ። ራሄል መሆኗን አውቋል።

እሱ ስልኩ ጋ ከመድረሱ በፊት ዴብራ ቀድማ አነሳች።

«Hello,» አለች፤

«Who is this?» አለች

ደረሰና ስልኩን ሊነጥቃት ሲል ቀድማ ዘጋችበት። ዓይኗን እንዳፈጠጠች የያዘችውን ብርጭቆ መሬት ላይ ከሰከሰችው

«Who is she?» አለችው።

በስልኩ መዘጋት የተናደደው ካሣሁን ተራውን ዓይኑን አፈጠጠና «That is none of your business, get out of my house!» አላት። በእጁ ትከሻዋንና አንገቷን ይዞ ወደ በሩ ሊመራት ሲሞክር ታገለችው። በጥፊም አጮለችው። ከዚያ በኋላ አይነሳ። ድብልቅልቁ የወጣ ረብሻ ሆነ። በልፊያቸው መሃል አመለጠችና የአበባ ማስቀመጫውን ከአቅራቢያ አንስታ ወረወረችበትና ሮጣ በሩን ከፍታ ወጣች። ተከትሏት ሊወጣ ብሎ በሩ ጋ ደረሰና በልፊያቸው መሃል አመለጠችና የአበባ

ማስቀመጫውን ከአቅራቢያ አንስታ ወረወረችበትና ሮጣ በሩን ከፍታ ወጣች። ተከትሏት ሊወጣ ብሎ በሩ ጋ ደረሰና ጎረቤቶች ምን ይሉኛል የሚል ሃሳብ ድንገት መጣበትና በሩን ዘግቶ ተመልሶ መጣ።

የተሰባበረው ዕቃ፣ ያጮለችው ጥፊ ብዙም አልተሰማውም። የተዘጋው ስልክ ጉዳይ ግን የበለጠ ከነከነው። ስልኩን ብድግ አድርጎ ፈጠነ ጋ ደወለ። ፈጠነን አላገኘውም። ትንሽ ቆይቶ ስልኩ ተደወለ። ራሄል መሆኗን አልተጠራጠረም። ለራሄል ስለዴብራ አልነገራትም። ብቻውን እንደሚኖር እንጂ ሌላ የሴት ድምፅ ያለው ሰው ቤቱ እንደማይኖር ነው የምታውቀው። ደግሞ ምሽት ነው። ይህ ይህ ሁሉ በአዕምሮው እየተመላለሰ በፍርሃት ተውጦ ስልኩን በ3ኛው ጥሪ አነሳው።

«ሃሎ!» አላት እየፈራ እየተባ።

«ይገርምሃል፣ ቅድም አንተ ጋ ደወልኩ ብዬ ተሳስቼ ሌላ ቦታ ደወልኩና አንዲት ሴትዮ ጮሃብኝ በጆሮዬ ለምን አትዘጋም መሰለህ?» አለችው። ያላሰበው ነገር ሆነ። ራሄል አልጠረጠረችም። ደስ አለው። ተመስገን አለ።

«ኸረ ባክሽ?» አላት ከወትሮው ለየት ያለ አባባል ነበር።

«አይገርምህም? እኔ ደግሞ ለምን አልደነግጥም መሰለህ፤» አለችው ለአፍታ ዝም አለ። የዋህነቷ ተሰማው። ነገሩ እንደዚያ መስሎ ቢታያትም እሱ ዝም ብሎ ቢቀበል ሊዋሻት ሆነ። ይወዳታል። ከዋሻት ደግሞ እንዴት ሊወዳት ይችላል። ከወደዳት ደግሞ እንዴት ሊዋሻት ይችላል።

«Tell me little sweet lies» የሚለው የዘመኑ ዘፈን ትዝ አለው። ይህ Little lie አይደለም። Big lie ነው። አይሠራም። ስለዚህ ትወቀው። ግን አሁን አልነግራትም፣ ሌላ ጊዜ እያለ ሲያሰላስል በስልኩ ወዲያኛው ወገን የምታነጋግረውን ራሄል አልሰማትም ነበር።

«ተኛተሃል እንዴ!» ስትለው ከሃሳቡ ባነነ

«ኸረ አልተኛሁም» አላት

«ታዲያ ያን ሁሉ ለፍልፌ ጥያቄ ሳቀርብልህ ምነው ዘጋኸኝ» አለችውና ቁጥብ ያለች ትንሽ ሳቅ አሰማች፣

«ጥያቄ አልሽኝ!» አላት።
«ውይ ጆሮህ ላይ ነው ወይስ ጉንጭህ ላይ ስልኩ፣ ትገርማለህ? ደብሮኛል፣ ሥራ ከሌለህ ናና ወጣ እንበል ብዬሂ ነበር። አለችው

«እቤት ነሽ?» አላት

«አዎ እቤት ነኝ ትመጣለህ»፤ አለችው።

«እመጣለሁ፤ እንዲያውም የምነግርሽ ጉዳይ ስላላኝ ማጋናኛታችን ጥሩ ነው።» አላት።

ራሄልን ጠቅላላ የነበረበትን ነገር ሁሉ ሊነግራት ወሰነ። ራሄልን ይህን ብቻ ሳይሆን ሌላም ሊነግራት ያሰበው ነገር ነበር። ዴብራ በሕይወቱ በቀላሉ ገብታ ግን በቀላሉ የምትወጣ አልሆነችም። ቢሆንም ራሄል ትልቅ ተስፋ ናት። ስልኩን እንዳስቀመጠ ስልክ ስልኩን እያየ ፈገግ አለ። በተቀጣጠሩበት ሰዓት ከራሄል ጋር ተገናኙ። ተያይዘው ፀጥታ ይኖረዋል፤ ቁም ነገር ጨዋታ ለመናገር ያመቻል ካሉበት አንድ ምግብ ቤት ሄዱ። የሚበሉትን ምግብ እንዳዘዙ ካሣሁን ቁና ተነፈሰና ማውራት ጀመረ።

«ራሄል ቅድም ተሳስቼ ደወልኩ ያልሺው ቦታ ስህተት አልነበረም።» አላት እየፈራ እየተባ፣ ቀና ብሎ ፊቷን ለማየት አልቻለም። ጎንበስ ብሎ ጠረጴዛው ላይ ያለውን ባዶ ሰሃን እያየ።

«አልገባኝም፣ እንዴት ስህተት አልነበረም?» አለችው በመገረም። ከሷ የሸሸውን ዓይን ለማየት እየጓጓች

«የደወልሽው እኔ ጋ ነበር»

«ታዲያ እንዴት...?»
አቋረጣት «እኔው ልንገርሽ። ካነሳችው ሴትዮ ጋር እንወጣ ነበር።»

«ነበር?» ብላ ጠየቀችው።

«አዎ ነበር?» አላት፤

«ነበር ከሆነ የዚያን ጊዜ ቤትህ ምን ታደርጋለች?» አለችው።

«ታሪኩ ብዙ ነው ራሄል፤» ትንሽ ተንፈስ አለና ቀና ብሎ አያት። በመገረም መልክ እንደምታየው ተረዳ።

«ስሟ ዴብራ ይባላል።»

«ቆይ! ቆይ! አትቸኩልብኝ፤ እንድትዋሸኝ ደግሞ አልሻም፤ ምንም ምንም ከመነጋገራችን በፊት አንድ ነገር Clear አድርግልኝ።» አለችው።

«የፈለግሽውን ጠይቂኝ» አላት።

«አሁን አብራችሁ ትወጣላችሁ ወይ?» አለችው። ዓይኗን አፍጣ መልሱን ስትጠባበቅ «ዋ! ትዋሸኛና» የምትል መሰለችው «አጭር መልስ ብቻ።»

«እንወጣም» አለና የተናገረውን ማመኗን ከዓይኗ ለማወቅ ይችል ይመስል ቀና ብሎ አያት።

«Wait! ታዲያ ካልዋጣችሁ እቤትህ ምን ታዳርጋላች? በተለይ በምሽት?» አለችው።

«እኔ አልፈልግሽም ካልኳት ቆይቻለሁ። እሷ ግን ... ምን ብዬ እንደምነግርሽ አላውቅም። ... በቃ አለ አይደል፣ አልተውሁም ብላ አስቸገረችኝ፤» አላት፤

«ስንት ጊዜያችሁ ነበር አብራችሁ ስትወጡ የነበረው?»

«አንድ ስምንት ወር ያህል!»

«እና ለምንድነው አሁን አልፈልግሽም ያልካት»

«ብዙ የማንግባባቸው ነገሮች ተፈጠሮ»

«በኋላ ተፈጠሩ ወይስ ከመጀመሪያውኑ ጀምረው ነበሩ።» አለችው።

ካሣሁን ያልጠበቀው ጥያቄ ነበር። በርግጥ ይህን ጥያቄ ራሱንም ቢሆን ጠይቆ አያውቅም ነበር። እና ትንሽ አሰብ አደረገና ቀና ብሎ አያት። በጉጉት የሚለውን ትጠብቃለች።

«ራሄል በርግጥ ይህን ጥያቄ አስቤበት አላውቅም። አሁን ሳስበው ግን የማንግባባቸው ነገሮች መጀመሪያውኑ ነበሩ ብል የምሳሳት አይመስለኝም።» አላት።

«እና ታዲያ...» ብላ ልትጠይቀው የጀመረችውን ሳትጨርስ አቋረጣት።

«ገብቶኛል የምትጠይቂው። እንዴት ብዬ እንደምመልስ ይቸግረኛል። አየሽ በዚያን ጊዜ የሴት ጓደኛ አልነበረኝም። ግልፅ ልሁንልሽና አበሻ ሴት ለማግኘት አልቻልኩም። ብቸኝነቱን ደግሞ አልቻልኩትም። አግኝቼ የተዋወቅሁዋት ቦታም የሚረባ አልነበረም። እና በቃ አለ አይደል ምርጫ አልነበረኝም።» ከሷ ጋር ሆኖ ያገኘውንም ደስታ፤ አልደበቃትም።

ጠቅላላ የነበረውን ሁኔታ ሁሉ አጫወታት። ራሄል ልብ ብላ አዳመጠችው። ይህን የራሱን የግል ምስጢር ሁሉ ሲያጫውታት ብዙ ነገር በአዕምሮዋ ይመላለስ ነበር። ሌላ ሴት ጋር በተለይ ከውጪ ሴት ጋር ለምን ወጣህ ብላ አልጠየቀችውም፤ አልነዘነዘችውም፤ አሁንም ተመልሰህ እሷ ጋ ትሄዳለህ ብላ አልጠረጠረችውም። «ትቻታለሁ ያልከዎ ውሸት ነው» ብላ አላለችውም። ብቻ አዘነችለት። ማዘን ብቻ አይደለም አሰበችለት። «የሆነውን ሁሉ ግልፅ አድርጎ የነገረኝ ቢወደኝ ነው» ብላም አሰበች። የነገረኝም ቢያስብልኝ ነው፣ የምስጢር ተካፋዩ እንድሆን፣ የከንፈር ወዳጁ ብቻ ሳይሆን ጥሩ ጎደኛም እንድሆነው ቢፈልግ ነው።» ብላ አሰበች። እንደወደዳት ገባት፤ ስለወደዳትም አልኮራችበትም፤ ጉራዋን አልነዛችበትም። በቃ እሷም ፈቀደችው።

ግን አንድ ነገር ለማወቅ ብቻ ፈለገች። ይህንንም ልትጠይቀው አላቅማማችም።

«ካሣሁን» አለችው ለስለስ ባለ የፍቅር ድምፅ

«ምን ልትለኝ ነው? በቃ አልፈልግህም ልትለኝ ነው? ምን ይሆን?» እያለ» በፍርሃት ቀና ብሎ ዓይን ዓይኗን እያየ «አቤት» አላት።

«አንድ ነገር ልጠይቅህ እስቲ?» አለችው።

«ጠይቂኝ» አላት።

«ይህን ሁሉ ምስጢር ለምን ነገርከኝ?» አለችው። ደነገጠ፤

«ባልነግራት ይሻል ነበር ማለት ነው? ወይኔ! አበላሸሁት! እያለ በመፍራት

«እንድታውቂው ብዬ ነዋ!» አላትና አንገቱን ሰበር አደረገ።

«አውቄስ?» አለችው።

«በቃ ሰለኔ ማወቅ ያለብሽ መሰለኝ፤ ምነው? አጠፋሁ እንዴ?» አላት

«አጠፋህ አላልኩም፤ ሌላ ደግሞ ልጠይቅህ? ግልፅ ሁን! እሺ?» አለችው።

«እሆናለሁ» አላትና ቀና ብሎ አያት።

«ትወደኛለህ?» አለችው።

«እ!» አለና ዓይኗን ፍዝዝ ብሎ አያት የአበሻን ሴት «እወድሻለሁ» ብሎ መናገር «በራስ ላይ ችግር ማምጣት ነው፤ እየተባለ ወንዶች ዘንድ የሚወራው ለአፍታ በዓይነ ሕሊናው መጣበት። ግን ግድ አልነበረውም። በርግጥ ራሄልን ወዷታል፤ ይህንኑ ደግሞ መግለፅ ምንም ኃጥያት የለበትም። የፈለገውን ያህል ትኩራ! ትንጠባረር! እወዳታለሁ ብሎም አሰበ። እናም አልደበቃትም።

«እወድሻለሁ ራሄል» አላት። «አንቺስ» ብሎ አላስገደዳትም። እሷም ጥያቄውን አልጠበቀችም። እንደምትወደው ታውቃለች፤ ስለዚህም ገለፀችለት

«እኔም እወድሃለሁ ካሣሁን» አለችው።

በጠረጴዛው ላይ እጁን ዘርግቶ እጇን ጭብጦ አድርጎ ዓይን ለዓይን ይተያዩ ገቡ። የሁለት ፍቅረኞች የልብ ምት ጨመረ። በሁለት እጆች ግንኙነትም አንዱ የሌላውን ምት ያዳምጥ ጀመረ። ካሣሁን መንፈሱ ረጋ፤ ራሄልም እንዲሁ። እሱም በሷ ሕይወት እሷም በእሱ ሕይወት እንደሚገቡ ሁለቱም እርግጠኞች ሆኑ።

ፈጠነ የዚያን ዕለት ምሽት ሲንቲያ «ዛሬስ አትሄድም እዚህ ነው የምታድረው» ብላ እጁን ጎትታ ወደ መኝታ ቤት ከወሰደችበት ቀን ጀምሮ በፍቅሯ ተጠመደ። በሁኔታዋ ሁሉ ወደዳት። ፊት የነበረው ግምት ሁሉ ትክክል እንዳልነበረ እየተገነዘበ መጣ። ከሁሉ በላይ ግልፅነቷ የምትፈልገውን ነገር በቀጥታየመጠየቋ፤ የማትፈልገውን ነገር በተዘዋዋሪ መንገድ ሳይሆን በቀጥታ የመግለጿ ሁኔታ ልዩ ስሜት አሳደረበት። ፍቅርን ወስዶ ፍቅርን የመስጠት ችሎታዋ ከዚህ በፊት አወጣሁዋቸው ከሚላቸው ሴቶች የበለጠ ሆኖ ታየው።

ፈጠነና ሲንቲያ ለአንድ ሶስት ወር ያህል ከተማው አልበቃ አላቸው። እሱ በግልፅነቷ እየተማረከ፤ እሷም በየዋህነቱ፣ በልብቀንነቱ እየተማረከች ፍቅራቸው እየጠነከረ መጣ። ፈጠነ ከሲንቲያ ጋር መውጣቱን አበሶሽ አወቁ አላወቁ ደንታ አልጠውም። እያያዛትም አበሻው ፓርቲ፣ ጓደኞቹ ቤት ይሄድ ጀመር። እሷም እንዲሁ ይዛው ጓደኞቿ ጋ ትሄድ ጀመር።ይህ ሁሉ ከንውን እያቀራረባቸው መጣ። ወጪያቸውን ለመቀነስ፤ የበለጠም ለመግባባት በማሰብ አንድ ላይ መኖር መጀመር እንዳለባቸው ሲንቲያ ያቀረበችውን ሃሳብ ፈጠነ ተቀበለ። አብረውም መኖር ጀመሩ።

ሲንቲያ ለፈጠነ በጣም ትጠነቀቅለታለች። ከባህሉ፣ ከጓደኞቹ በሷ ምክንያት እንዳይለይ በማለት እቤታቸው ጓደኞቹ እንዲመጡ ትገፋፈለች። የፈጠነ ጓደኞችም ወደዷት። ፈጠነም በበኩሉ ለሲንቲያ ይጠነቀቅላታል። ከዘመዶቿ ከጓደኞቿ በሱ ምክንያት እንዳትለይ እያለ የሷም ጓደኞች ሆኑ ዘመዶች ወደሱ ቤት ሲመጡ በትህትና ይቀበላቸዋል። እነሱም ይወዱታል። ባህል፤ ልምድ፤ ዜግነት ሳያግደው ፍቅር በሲንቲያና በፈጠነ ላይ ጎጆውን ቀለሰ። የበለጠ እየተግባቡ በመጡ ቁጥር የበለጠ ይዋደዱና ይነፋፈቁ ጀመር። ፈጠነም ትምህርቱን እንዲቀጥል ሁኔታውን ሁሉ አመቻቸችለት።

ካሣሁን ከዴብራ በፍፁም ለመሸሽ በማሰብ እስቴት ቀይሮ በሄደ በስድስተኛው ወሩ መለስ ያለ ዝግጅት ተደርጎ ከራሄል ጋ ተጋቡ። በጋብቻቸውም ዕለት የእሱ እናት፣ የራሄልም እናት ከኢትዮጵያ መጡ። ፈጠነና ሲንቲያም መጥተው የደስታው ተካፋይ ሆኑ።

ካሣሁንና ራሄል በተጋቡ በሁለተኛው ወር ፈጠነና ሲንቲያ ተጋቡ። ፍቅር ዘር፣ ጎሣና ብሔር ወስኖ የሚመጣ ስሜት አለመሆኑንም ሕያው ምስክር ሆኑ።

## ተ ፈ ጸ መ

## ውድ አንባብያን

በአስራ አንድ እትሞች በተከታታይ የወጣው "የዴብራ ጦስ" የተሰኘው በእውነተኛ ታሪክ ላይ የተመሠረተው ልብወለድ በቅርብ ጊዜ ውስጥ ሙሉ ታሪኩ በስፋት በመጽሐፍ መልክ የሚታተም መሆኑን እንገልጻለን።


OPEN 7 DAYS

Sweet Auburn Grocery

*We specialize in Ethiopian & American Products*

210 Auburn Ave
Atlanta, GA 30303
(404) 577-6756

ካብኛን

የተለያዩ የምግብ ሸቀጦች

በርበሬ
ምጥን ሽሮ
ሽሮ
ምስር ክክ
ድፍን ምስር
አተር ክክ
ቅንጬ
የጤፍ ዱቄት
ንፁህ የባህር ዕጣን
የተነጠረ ቅቤ
እንጀራ
ሚጥሚጣ
ቡና

የተለያዩ ቅመሞች

ቀረፋ
ሄል
ቅርንፉድ
የቅቤ ማንጠሪያ
ሌሎችም

በጥሩ ዋጋ

# ዕጣዬ

## ከአብረኸት

### ከአለፈው የቀጠለ

### ክፍል ፮

እውነተኛው የስደት ኑሮአችን የሚጀምረው ከጎንደር ከተማ ተነስተን ሌሊቱን በመጓዝ በተክል ድንጋይ በኩል ያደረግነው ጎዞ ነበር። የሰይፉ ጓደኛ ሁሉን ነገር አመቻችቶልን መንገድ አሳይቶ ሱዳን ጠረፍ ለሚያደርሰን የገጠር ነጋዴ ሁለት መቶ ብር ከፍለን ነበር ጉዞአችንን የጀመርነው። እንደነገ ሌሊት ልንነሳ እንደዛሬ ሌሊት ያደርኩበትን፣ የነበርንበትን የመንፈስ ጭንቀት ልነግራችሁ አልችልም። እኔ እንቅልፍ አልወስድ ብሎኝ አስሬ ስገላበጥ ሰይፉ ዓይኑ እንደፈጠጠ ነበር ያደርነው። አንዳንድ ጊዜ ከዚህ ሁሉ ውጥንቅጥ ሁኔታ ወጥተን በሰላም እፎይ የምንልበት ቦታ ስንደርስ ይታየኝና እጽናናለሁ። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ጭራሽ የጨለማ ጉዞ ይሆንብንና ያሰብንበት ሳንደርስ በመከራና በስቃይ ስንቸገር ይታያኛል። አፍ አውጥቶ አይናገረው እንጂ ሰይፉም ከዚህ የተለየ ነገር እንደማይሰማው እርግጠኛ ነበርኩ።

«ኩራት ኩራት አይልሽም ወይ?» ተብሎ ተዘፍኖልኝና ተሠርጎልኝ በወግ በማዕረግ ተድሬ፣ ጥሩ የትዳር ኑሮ ሲታየኝ ይቆይና ይህ ደግሞ ውኃ በልቶት ከርቀት በዓይነ ሕሊናዬ «ፍርሃት፣ ፍርሃት አይልሽም ወይ?» ተብሎ ሲዘፈንልኝ ይሰማኛል።

«እህህ!» አልኩኝ እንዴ ፍርሃት ሰውነቴን ውርር አደረገውና ሰይፉዬን ጠጋ አልኩት።

«ምን አልሽኝ?» አለ እሱም መከታነቱን ለመግለፅ ብሎ ጠጋ እያለኝ።

«ምንም! አልኩና ዓይን ዓይኑን ትክ ብዬ እየው ጀመር ወደሱ ጠጋ ብዬ። እሱም ዓይን ዓይኔን እያየ ዝም አለ።

"አይዞሽ! አይዞህ" የተባባልንበት ተስፋ የተሰጣጠንበት፤ ሁኔታችን መሆኑ ነው መሰለኝ። ከንፈሮች ተንቀሳቅሰው አፎች ባይናገሩም በዓይን ብዙ መባባል ይቻላል።

ጉዞው ረዥም፤ አድካሚ ነበር። መሪያችን በጣም ያበረታታን ነበር። አይዞአችሁ ደርሰናል ይለናል። ደረስን ስንል «ምንም አልቀረንም» ይለናል። በየጫካው በየዱሩ እያደርን፤ ያስፈራል የሚባልባቸውን አካባቢዎች በሩቁ እየተውን ጥማቱንና ድካሙን እየቻልን ከጎንደር በተነሳን በ12ኛው ቀን እርማጮሆ ደረስን።

መሪያችን አንድ የሚያውቀው ገበሬ ቤት ወሰደንና እንድናርፍ አደረገን። የአንድ ቀን እረፍት ካዳረግን በኋላ እንደምንቀጥል ተነገረን። የደመከውን ጎናችንን ቁርበት ከለበሰው መደብ ላይ አሳረፍን። ያረፍንባቸው ሰዎች «እነኚህን ጨቅላዎች ደከማቸው አይደል» ብለው እንዴት ጠቦት በግ አረዱልን። ቤት ያፈራውንም ጎሽ ጠላ አቀረቡልን። አስተናገዱን። የአገሬውን እንግዳ ተቀባይነት፣ ሰው ወዳድነት፣ ልነግራችሁ አልችልም። «አይዞአችሁ» ተባልን። በርቱም ተባልን። እኔ በእውነቱ የአገሬን ሰው የበለጠ የወደድኩበት፣ የኮራሁበት ጊዜ ነበር። ለጠላቱ አይበገርም የሚባለውን የእርማጮሆ ሕዝብ ለወገኑ፣ ለሚወደው ያለውን ፍቅር አየሁት። በሚቀጥለው ቀን እናደርጋለን የተባለው ጎዞ በአንዳንድ እክል ምክንያት ቆየ። እኔም እግሬ ትንሽ አበጥ ብሎ ስለነበር ትንሽ ቀን እዚህ መቆየታችንን አልጠላሁም። ያረፍንባቸው ገበሬ ሚስት ጥሩ እናት ነበሩ። ያደርጉልን የነበረው ነገር ሁሉ ለአፍታ እናቴን አስታወሰኝ።

ሁለተኛውን ቀን ሳይሳካ ቀረና በሶስተኛው ቀን ጉዞአችንን ጀመርን። ይኸኛው ጉዞአችን ፊት ካደረግነው የበለጠ የሚያስመርር ነበር። በመንገዳችን ላይ ዝናብ ሲጥል የምንጠለለው ከዛፍ ቁጥቋጦ ስር ኩርምት በማለት ነበር። አልፎ አልፎ የሚገኙትን ወራጅ ወንዞች የምንሻገረው በድልድይ ሳይሆን ጥልቀት የሌለውን ቦታ በመፈለግ ውስጥ ውስጡን በመሄድ ነበር። ለኔ ይህ ሁሉ አዲስ ነገር ነበር።

ከረዥም ጉዞ በኋላ ኮር ሁመር ከምትባል ቦታ ደረስን። የሱዳንና የኢትዮጵያ ነጋዴ የሚተላለፍበት የሱዳንና የኢትዮጵያ ጠረፍ ከተማ ነበረች። ቦታዎ በጣም ሞቃት ጊንጥና እባብ በብዛት የሚገኝበት ቦታ ነበረች። ጥቂት አበሾች ይኖሩበታል። ከሁለት ዓመት በፊት ወደዚህ የመጣች በለጡ የምትባል ሴት እንደሌላው የአገሬው ሕዝብ በሳር ሰንበሌጥ በተቀለሰች ጎጆ ውስጥ ሻይ እየሸጠች መንገደኛውን ታስተናግዳለች። በለጡን ስናገኛት በጣም ደስ አለን። የመንገድ መሪያችን በቀጥታ ወደሷ ቤት ሲወስደን በደስታ ተቀበለችን። በዚህ አካባቢ የሚያልፉ ኢትዮጵያውያን ስደተኞችን ሁሉ እያስተናገደች አፅናንታ ምግብ አብልታ፣ ሻይ አጠጥታ የምትሸኝ እንደሆነች መንገድ መሪያችን ነገረን። እሷ ጋ ከደረስን በኋላ እሱ ወደ ጎንደር እንደሚመለስ ሲነግረን ትንሽ ብንደነግጥም በለጡ አይዞአችሁ ብላ አጽናናችን። ገዳሪፍ ወደሚባል ቦታ ከነጋዴ ጋር እንደምትልከን ተስፋ ሰጠችን። እስከዚያም እሷ ጋ እንደምንቆይ ነገረችን።

አንድ አስር ቀን ያህል ኮር ሁመር ቆየን። የሚወስደን ነጋዴ እስከሚመጣ በሚል ሰበብ በለጡ አቆየችን።

የአገሯን ልጆች ስታገኝ ምን ያህል ደስ እንደሚላት ስትነግረን እኛም ብቸኝነቷን ተረድተን ትንሽ ቀን መቆየታችን አላሳዘነንም። በዚሁ ቆይታችን ብዙ ብዙ ነገር ማወቅ ቻልን። የስደት ኑሮ ምን ያህል አስቸጋሪ እንደሚሆንና ከወዲሁ መዘጋጀት እንዳለብን በለጡ አስተማረችን። በለጡም ታሪኳን አጫወተችን። የመጣችው ከጎንደር ከተማ ሲሆን አብሯት የመጣው የምትወደው እጮኛዋ በወባ በሽታ ተቀስፎ እዚሁ ኮር ሁመር ሲደርስ ስድስት ወር ታሞ መሞቱን ነገረችን። ከዚያም ወደፊት ገፍታ በመሄድ ፈንታ ተስፋ ቆርጣ እዚሁ እንደቀረች አጫወተችን።

«እዚህ መቅረቱ ታዲያ ጥሩ ነው ብለሽ ነው» አልኳት ይህንኑ ያጫወተችን ዕለት።

«ጥሩም ይሁን መጥፎ ከዚህ የተለየ ነገር ማድረግ አልቻልኩም። ሁለት ምክንያቶች አሉኝ። አንደኛ እጮኛዬ ለመጥፋት ብዙም አልፈለገም ነበር። እኔ ነኝ የገፋፋሁት። እና ገፋፍቼ ገፋፍቼ እንዲሰደድ በማድረግ ለሞት ያበቃሁት እኔ ነኝ የሚል ስሜት አለኝ። ለዚያ ጥፋቴ ራሴን ለመቅጣትም ጭምር ነው። ሁለተኛው ምክንያቴ የወደፊት ዕቅዴ፣ ዓላማዬ ሁሉ ነገር የተያያዘው ከእጮኛዬ ጋር ነበር። በጣም እወደዋለሁ። እሱም ይወደኛል። እና እሱ ሲሞት የዓለም ጣዕሙ አልገባሽ አለኝ። እሱ የተቀበረበትን ቦታ ጥሎ መሄድም አላስቻለኝም። ብቻዬን ስለሆንኩ ደግሞ እፈራለሁ። እዚህ ከሆንኩ እሱ ያለ ስለሚመስለኝ እፅናናለሁ» ብላ እንባዋ እርግፍ እርግፍ አለ።

እኔም አልቻልኩም። የኔም እንባ ፈሰሰ። አዲስ አበባ እያለሁ ያነበብኩት «ፍቅር እስከ መቃብር» ትዝ አለኝ። ፍቅር መስዋዕትነት እንደሆነም የተማርኩበት ሁኔታ ነበር።

«እና ለወደፊቱ ምን አስበሻል?» አልኳት።«እኔ እንጃ። ይኸው እሱም ከሞተ ሁለት ዓመት ሊሆነው ነው። ትዝታው እስኪጠፋብኝ ምን እንደማደርግ አላውቅም። ይህን አደርጋለሁ ብዬ አስብና የእሱ ፍቅርና ትዝታ ፊቴ ድቅን ይላል። የከዳሁት ይመስለኝና ወደ ገዳሪፍ ወይም ካርቱም ለመሄድ ያቀድኩትን ነገር እተወዋለሁ። በቃ ለጊዜው ይኸው ነው» ብላ ትክዝ አለች።

በጣም አሳዘነችኝ። እኔም የቻልኩትን ያህል ምክር ሰጠሁዋት። ከእንግዲህ ለእጮኛዋ ምንም ማድረግ እንደማትችል፤ እርሷም ደግሞ በእጮኛዋ ላይ በደረሰው የሞት አደጋ ኀጥያተኝነት፣ ወይም ጥፋተኝነት ሊሰማት እንደማይጋባ ነገርኳት።

ትንሽ የመንፈስ መረጋጋት እንድታገኝ በማሰብ ነበር። መንፈሷ ሲረጋጋ ትክክለኛውን ነገርና መንገድ ለማቀድ ትችላላች ብዬ ነው። በጽሞና አዳመጠችኝ። እኔም በበኩሌ ከተሳካልኝ እንምንረዳት ቃል ገባሁላት።በሚቀጥለው ቀን ልንሄድ ምሽቱን በለጡ ጥሩ እራት ሠርታ ሶስታችንም ቁጭ ብለን እየተጫወትን እንቅልፍ በዓይናችን ሳይዞር አደረ።

የስደት ኑሮ እንደአገር ሊሆን እንደማይችልና ብዙ ችግሮች እንደሚገጥሙን ብረዳም ሰይፍዬ አብሮኝ መኖሩ አጽናናኝ። ከወደዱት ጋር አብሮ ሆኖ የፈለገው ቢደርስ ምን ይሰማል?

እንኳን እኔ ሰይፉ አብሮኝ ያለው ይቅርና ብቻቸውን ያለምንም ዘመድ ከቤታቸው ጠፍተው የሚሰደዱ ስንት ሴቶች ልጆች አሉ። ይህ የበለጠ አጽናናኝ።

በለጡም አንድ የሱዳን ነጋዴ አገኘችልንና እኔን በቤተ ሠራተኛነት ሰይፉን ደግሞ በአሽከርነት ቀጥሮ እንዲወስደን አነጋገረችልን። ነጋዴውም ሰይፉን ለመቅጠር ብዙ ባይፈልግም ወንድሟ ነው ተብሎ በስንት ማግባባት እሺ እንዳለ በዚሁ ምሽት ነገረችን። በነጋታውም ከበለጡ ጋር እንባ በእንባ ሆነን ተሰነባብተን ጉዞአችንን ወደ ገዳሪፍ ጀመርን። ነጋዴው ለኔ በስምንት 40 ጂኔ (የሱዳን ገንዘብ) ለሰይፉ ደግሞ 30 ጂኔ እንደሚከፍለን ነበር በለጡ የተነጋገረችልን። ጉዞአችን በጣም አድካሚ ነበር። እንደአጋጣሚ ሆኖ ምንም ፍተሻ ሳያጋጥመን ገዳሪፍ ገባን።

ነጋዴው ሰይፉን የኔ ወንድም አድርጎ እንደወሰደና በመካከላችን ያለውንም ግንኙነት እንዳያውቅ በለጡ አጥብቃ አስጠንቅቃን ነበር። እሱም ምንም ጥርጣሬ ስላላደረበት ሁለታችንንም በትህትና ነበር የሚያነጋግረን የነበረው። በለጡ ይህን ለምን እንዳለችኝ ጥርጣሬ ቢኖረኝም ሊመጣ ለሚችለው ነገር ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለብኝ አወቅሁ። የቀጠረን ነጋዴ በመንገዳችን ላይ ትህትና ከማሳየት በቀር ምንም ምልክት አላሳየኝም። ያም ሆነ ይህ ገዳሪፍ እንደደረስን በቀጥታ ወደ ቤቱ ይዞን ሄደ። ደህና ቤት ነው ያለው። ለኔ አንድ ክፍል ለሰይፉ ደግሞ ከሌላው አሽከሩ ጋር በሌላ ክፍል እንድንገባ ተደረገ። ሥራችንንም ጀመርን። ከአዲስ አበባ ከወጣሁ ለመጀመሪያ ጊዜ ከሰይፉ ተለይቼ አደርኩ። እኔ ሥራዬ ምግብ ማዘጋጀትና ዕቃ ማጠብ ቤት መጥረግ ነበር። ሰይፉ ደግሞ በአብዛኛው በነጋዴው ሱቅ በመላላክና ዕቃ በመሸከም እቤትም እንዲሁ ከበድ ከበድ ያሉትን ሥራዎች እንዲሠራ ነበር የተመደበው። የመጀመሪያው ቀን አዳሬ በፍርሃት የተሞላ ነበር። ከሰይፉ ተለይቼ ማደሬ ትልቅ ቅሬታ ቢያሳድርብኝም የተኛሁበት ክፍል በር ካሁን እሁን ተከፈተ የሚል ፍርሃት ሰውነቴን ሞልቶት እንቅልፍ የሚባል ባይኔ ሳይዞር እንዲሁ ስጨነቅ ስጠበብ አደርኩ። በነጋታው በጠዋት ተነስቼ ሥራዬን ሠራራሁና ሰይፉን ፈልጌ አገኘሁትና ስለፍርሃቴ አጫወትኩት። እሱም ሲጨነቅ እንዳደረ ነገረኝ። ምንም ነገር ያን ምሽት እንዳልተፈፀመም ስነግረው ልቡ ረጋ። የሚቀጥለውም ቀን፣ ከዚያም በሚቀጥለው ሁኔታው ሰላም ሆነና የኔም ልብ ረጋ እያለ መጣ። ግን በዚያው አልቀጠለም። በመጣን በሳምንቱ የፈራሁት ደረሰ።

(በሚቀጥለው እትም ይቀጥላል)

# ኑሮ በአሜሪካ

## « የማታ የማታ እውነት ትረታ !!»

### በአትላንታ የቅድስት ማርያም ቤተክርስትያን ምዕመናን ረቱ።

በአትላንታ ከተማ የፓትርያርክ ጳውሎስ ተከታይ ነኝ በሚሉት ቄስ ሙሴና በዚሁ ከተማ ባለችው የቅድስት ማርያም ኦርቶዶክስ የኢትዮጵያ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ምዕመናን መካከል ሲካሄድ የቆየው የፍርድ ክርክር ባለፈው January 1995 በምዕመናኑ ረቺነት ማብቃቱን ለመረዳት ተችሏል። በተገኘው መረጃ መሠረት ቄስ ሙሴ በዚህ በምዕመናን በተቋቋመው ቤተክርስትያን ለተወሰኑ ዓመታት በምዕመናኑና በአስተዳደር ቦርዱ ተመድበው በቅስና ሲያገለግሉ ከቆዩ በኋላ በ1993 አባ ጳውሎስ አትላንታ ለጉብኝት ሲመጡ ቦርዱን ሳያማክሩና ሳይጠይቁ በቤተክርስቲያኒቱ ስም ጉብኝቱን በድብቅ በማዘጋጀታቸውና ይህም ምዕመናንን ስላስቆጣ የአስተዳደር ቦርዱ በመሪ ቄስነት እንዳያገለግሉ ወስኖ ይህንንም በምዕመናን ጉባኤ ያጸድቃል። ቄስ ሙሴም ይህኛውን ቤተክርስቲያን በትምክህተኛ አማሮች የፖለቲካ ሰዎች የተያዘ በመሆኑ ሌላ ቤተክርስትያን ከፍቻለሁ ይላሉ። Ethiopian Commentator በተሰኘ መጽሔትም ላይ የአትላንታ ምዕመናን በመክሰስ ሰፋ ያለ መግለጫ ያወጣሉ። ከዚያም የቤተክርስቲያኒቱን የባንክ ሂሳብ ጠበቃ በመያዝ ሄደው እንዲታገድ (freeze) ያስደርጉታል። ለዚህም ዋንኛ ምክንያት አድርገው ያቀረቡት "እኔ የቤተክርስቲያኒቱ ሃላፊ ስለሆንኩና አሁን ያለውን ቦርድ ያባረርኩ ስለሆነ ውሳኔ በቅርቡ በፍርድ ቤት እስካስመጣ ድረስ እንዳይንቀሳቀስ ይደረግ፤" በማለት እንደሆነ ከቦርዱ ያገኘነው መረጃ ያስረዳል። ባንኩም ነገሩ ስላሳሰበው ሂሳቡን እንዳይንቀሳቀስ በማድረግ ወደ ፍርድ ቤት ይልከዋል። ቄስ ሙሴ "እኔ በሕጋዊው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስትያን ፓትርያርክ በአባ ጳውሎስ ስር ያለሁ በመሆኔና በእሳቸው አመራርና ዋሽንግተን በሚገኙት በአባ ማትያስ ትዕዛዝ መሠረት የአስተዳደር ቦርዱን ያባረርኩ በመሆኔ ገንዘቡ ለኔ ይገባል፤ ይህንንም በተመለከተ የማሰናበቻ ወረቀት ለቦርዱ አባላት በአንድ ኤንቬሎፕ አድርጌ በፖስታ ቤት ልኬአለሁ፤" ባይ ናቸው። የቤተክርስቲያኒቱም ምዕመናን ጠበቃም "ቄሱ በምዕመናን በተቋቋመው ቤተክርስትያን መንፈሳዊ አገልግሎት መስጠት እንጂ ከምዕመናን በተዋጣው ገንዘብ ላይ ምንም ሃላፊነት አልነበራቸውም፤ በተጨማሪም በምዕመናን የተመረጠውን የአስተዳደር ቦርድ የማውረድም የመሻርም ሥልጣን የላቸውም፤"ብሎ የመተዳደሪያ ደምቡን ጠቅሶ ከመግለጹም ሌላ የተጠቀሰው የማባረሪያ ወረቀት ለቦርዱ አባላት ያልተላከ መሆኑን አስረድቷል።

ለቄስ ሙሴ ዋነኛ ምስክር ሆነው የቀረቡት ከዋሽንግተን የመጡት ጳጳስ አቡነ ማትያስ ሲሆኑ እሳቸውም በሰጡት የምስክርነት ቃል በፍርድ ቤቱ የተገኙ የቤተክርስቲያኒቱ ምዕመናን በጣም የታዘቡዋቸውና ያዘኑባቸው መሆኑን ለመመልከት ችለናል። አባ ማትያስ ከቄስ ሙሴ ጠበቃ የቀረበላቸውን ጥያቄ ሲመልሱ አትላንታ ከ15 ጊዜ በላይ የመጡ፤ ይህችንም ቤተክርስቲያን በመመሥረትና በማቋቋም ከፍተኛ ሚና እንደተጫወቱ፤ በተጨማሪ ለቄስ ሙሴ የአስተዳደር ቦርዱን እንዲያወርድ ትዕዛዝ የሰጡ መሆኑን ይህንንም ያደረጉበት ምክንያት የተዋህዶ ኦርቶዶክስ ሃይማኖት ሕግጋትን በመጣስ መሆኑን አስረድተዋል። ከቤተክርስቲያኒቱ ምዕመናን የቀረበላቸውን መስቀለኛ ጥያቄ ፍሬ ሃሳቡን ከነጥያቄው አቅርበነዋል። ይህ ሙሉው ቃላቸው ሳይሆን በፊል የቀረበ ነው።

<u>ጠበቃ</u> ፤ ኢትዮጵያ ውስጥ ካሉት ኤትኒክ ቡድኖች ብዙ ህዝብ ያለውን ኤትኒክ ቡድን ቢነግሩን

<u>አባ ማትያስ</u> ፤ ሁላችንም ኢትዮጵያውያን ነን።

<u>ጠበቃ</u>፤ ለምሳሌ ኤርትራዊ፣ ትግሬ፣ አማራ፣ ኦሮሞ

<u>አባ ማትያስ</u>፤ ኤርትራ ራሷን የቻለች አገር ናት።

<u>ጠበቃ</u> ፤ ለመሆኑ የትግሬ ተወላጆች መንግሥት ይዘው ማስተዳደር ከጀመሩ ስንት ጊዜአቸው ነው?

<u>አባ ማትያስ</u> አላውቅም፤ እኛ አገር እንደሚያውቁት ከአንዱ ወደ አንዱ ይዘዋወራል።

<u>ጠበቃ</u>፤ ፕሬዚዳንት መለስ ዜናዊ ትግራዊ አይደሉም?

<u>አባ ማትያስ</u> ፤ አዎ ናቸው።

<u>ጠበቃ</u> ፤ ፓትርያርክ ጳውሎስስ ትግራዊ አይደሉም?

<u>አባ ማትያስ</u> ፤ አዎ ናቸው።

<u>ጠበቃ</u>፣ሁለቱም የትውልድ ቦታቸው አድዋ አይደለም?

<u>አባ ማትያስ</u> ፤ አዎ አድዋ ነው።

<u>ጠበቃ</u> ፤ እርስዎስ ትግራዊ አይደሉም?

<u>አባ ማትያስ</u> ፤ አዎ ነኝ።

<u>ጠበቃ</u> ፤ ቄስ ሙሴስ ትግራዊ አይደሉም?

<u>አባ ማትያስ</u> ፤ አዎ ናቸው።

<u>ጠበቃ</u>፤ ታዲያ ከላይ እስከታች በትግሬዎች ብቻ ሥልጣኑን ለማስያዝ የሚደረግ ጥረት አይደለም?

<u>አባ ማትያስ</u> ፤ ትግሬ መሆን ምን ፕሮብሌም አለው።

<u>ጠበቃ</u> ፤ ለዚች ቤተክርስቲያን እርስም ሆኑ አባ ጳውሎስ ገንዘብ ሰጥታችኋል?

<u>አባ ማትያስ</u> ፤ አልሰጠንም።

<u>ጠበቃ</u>፤ቄስ ሙሴ ቦርዱን እንዲያባርሩ አዘዋቸዋል?

<u>አባ ማትያስ</u> ፤ አዎን።

<u>ጠበቃ</u>፤ ቄስ ሙሴ ከፕሬስቢቴሪያን ቤተክርስትያን ጋር በጋራ ለመሥራት ግንባር መፍጠሩን ያውቃሉ?

<u>አባ ማትያስ</u> ፤ አላውቅም።

(በሚቀጥለው ገጽ ይቀጥላል)

ጠበቃ፤ ቄስ ሙሴ በፐሬስቢቴርያን ቤተክርስትያን ሥልጠና ወስደው ምስክር ወረቀት እንደተቀበሉ ያውቃሉ?
<u>አባ ማትያስ</u> ፤ አላውቅም።
<u>ጠበቃ</u> ፤ ይህን አሁን ሲሰሙ አልገረምዎትም?
<u>አባ ማትያስ</u> ፤ በጣም ገርሞኛል።
(አባ ማትያስ ቃላቸውን ከሰጡ በኋላ የፍርዱን ውሳኔ ለመስማት ሳይጠብቁ ወዲያውኑ ወደ ዋሺንግተን መመለሳቸውን ለማወቅ ተችሏል።)
ቄስ ሙሴ የኔ ነው ብለው ያሳገዱትና አሁን በፍትህ የተለቀቀው ገንዘብ ከአርባ አምስት ሺህ ዶላር በላይ መሆኑ ታውቋል። ተመሳሳይ ክሶችም በሌላ ቦታዎች (ዲ ሲ ለምሳሌ) ያሉ መሆናቸውንና አቡነ ማትያስም እነኚህን በህዝብ የተዋጡ ገንዘቦችን በአዲሱ ፓትርያርክ ስር ለማግባት እየተሯሯጡ መሆናቸውን ከየቦታው የደረሰን ዘገባ ይጠቁማል ።

## የገናና የጥምቀት በዓል
## በአትላንታ ተከበረ



በስደት ላይ ያሉት የኢትዮጵያ ተዋህዶ ቤተክርስትያን ፓትርያርክ የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆርዮስ እንደራሴ ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ ዜና ማርቆስ በተገኙበትና የቅዳሴ ሥነሥርዓቱን በመሩበት የመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ልደት በዓል ታህሣስ 29 ቀን 1987 ዓ.ም. በደማቅ ሁኔታ በአትላንታ ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን ተከበረ። ከምሽቱ 7:00 pm ጀምሮ እስከ ሌሊቱ 1:00 am በተከናወነው በዚሁ የቅዳሴ ሥነ ሥርዓት ላይ በአትላንታ ከተማ የሚገኙ ብዙ የኢትዮጵያ ኦሮቶዶክስ ሀይማኖት ተከታዮች መገኘታቸውን ለማወቅ ተችሏል። በተጨማሪ የጥምቀት በዓልም በተመሳሳይ ሁኔታ መከበሩ ታውቋል።

## ከአቡነ ዜና ማርቆስ ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ

ብፁዕ አቡነ ዜና ማርቆስ መስከረም 20 ቀን 1987 ዓ.ም. በኒውዮርክ ከተማ የተደረገውን ሲኖዶሳዊ ስብሰባ በሰብሳቢነት የመሩ መሆናቸውን ለማወቅ ተችሏል። ይኸው ሲኖዶሳዊ ስብሰባ በስደት የሚገኙትን ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትን ማለትም ብፁዕ አቡነ ይስሃቅ የምዕራብ አገሮች ሊቀጳጳስን፤ ብፁዕ አቡነ ኤልያስ የምሥራቅ አፍሪካና አውሮፓ ሊቀ ጳጳስ፣ ብፁዕ አቡነ መልከ ጸዴቅን በአባልነት የያዘ መሆኑ ታውቋል። ሲኖዶሳዊ ስብሰባው በኢትዮጵያ ሕዝብ ችግር ላይ፣ የኢየሩሳሌምን ገዳም ችግር በተመለከተና በውጭ አገር ስለተቋቋሙት ቤተክርስቲያኖች አመራር ችግር ላይ ሰፊ ውይይት በማድረግ ውሳኔዎችን ማስተላለፋቸው ዘግይቶ የደረሰን ዜና አብስሯል። በውጭ አገር በተቋቋሙት ቤተክርስቲያኖች ላይ ከአመራር በኩል የደረሰውን ችግር ሲኖዶሳዊ ስብሰባው በሰፊው ከተመለከተ በኋላ ጳጳስ ያላወቀውና ያልባረከው ቤተክርስቲያን ኦርቶዶክሳዊ ሊሆን እንደማይችልና ከዚህ ቀደም የተቋቋሙትም ሆኑ ወደፊት የሚቋቋሙት በአገረ ስብከቱ ጳጳስ አመራር ሥር ሆነው ቡራኬ ካልተቀበሉ በቀኖና ቤተክርስቲያን መሠረተ ቤተ ክርስቲያን የሚባለውን ስምና ግብር እንደሚያጡ አስገንዝቧል። ብፁዕ አቡነ ዜና ማርቆስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ፓትርያርክ የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆርዮስ እንደራሴና ሊቀ ጳጳስ ናቸው። በቅርቡ ኒውዮርክ የተደረገው ሲኖዶስም ሰብሳቢ ናቸው። ብፁዕ አቡነ ዜና ማርቆስ አትላንታ በመጡበት ጊዜ የዝግጅት ክፍላችን አነጋግሯቸው ነበር። ከብፁዕነታቸው ጋር ባደረግነው ውይይት የኢህአዴግ መንግሥት በሃይማኖት አመራር ላይ ጣልቃ በመግባት እውነተኛውን ፓትርያርክ በማውረድ የሱን መመሪያ የሚቀበል ፓትርያርክ ለመሾም ያደረገውን ፖለቲካዊ ድራማ የሚመለከት ይሆናል። በተጨማሪም በብፁዕነታቸው ሰብሳቢነት በኒውዮርክ ስለተቋቋመው ሲኖዶስ በጥቂቱ ያወያዩናል።

ላንዳፍታ –
ኢህአዴግ አዲስ አበባ በገባበት ወቅት ብፁዕነትዎ የፓትርያርኩ እንደራሴ እንደነበሩ ይታወቃል። የሲኖዶሱም ሰብሳቢ ነበሩ። ኢህአዴግ እንደገባ አንዱ ያተኮረበት ነገር ቢኖር ፓትርያርኩን ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆርዮስን ማውረድ ነበር። ይህን እንዴት ሊፈጽም እንደበቃ ሊነግሩን ይችላሉ።

**ብፁዕ አቡነ ዜና ማርቆስ -**
«ኢህአዴግ አዲስ አበባ እንደገባ ፓትርያርኩን ለማውረድ ከፍተኛ ጥረት ካደረገባቸው ጉዳዮች አንዱ ነበር። በመጀመሪያ ሲኖዶሱና ቤተክህነት የማያውቀው በአንድ ቄስ (ቄስ ሀብተማርያም የሚባሉ ካህን) ሰብሳቢነት አንድ ኮሚቴ ኢህአዴግ ያቋቁማል። ይህም ኮሚቴ ራሱን እንደ ሲኖዶስም እንደ ቤተክህነትም በመቁጠር ፓትርያርኩን ለማውረድ በሳቸው ላይ ወንጀል ማርቀቅ ይጀምራል። ፓትርያርኩም እንዲወርዱ ውሳኔ ይወስናል። ሁኔታው ትክክል ያልሆነና ከቤተክርስቲያኒቱ ሥርዓት ውጭ የተከናወነ መሆኑን ለማስረዳት እኔና 24 የሲኖዶሱ አባላት ቀጠሮ ይዘን ጠቅላይ ሚኒስቴር ታምራት ላይኔን አነጋገርን። በቤተክርስቲያን አመራር መንግሥት ጣልቃ መግባት የለበትም፤ የሚሠራውም ነገር ትክክል ያልሆነና ብዙ ችግር የሚፈጥር እንደሆነ በምክር መልክ አንድ ቀን ሙሉ በፈጀ ስብሰባ ልናስረዳቸው ሞከርን።

በቄስ ሀብተማርያም የሚመራው ኮሚቴም በቤተክርስቲያኒቱ ደምብ መሠረት የተቋቋመ ስላልሆነ በኮሚቴው የተወሰነውን ውሳኔ እንደማንቀበል አስረዳን። በውሳኔው መሠረት ፓትርያርኩን ካላወረዳችሁ ከመንግሥት ተፈቅዶ ይሰጥ የነበረው ድጎማ ታግዷል የሚል ውሳኔ ተሰጠን። በታገደው ገንዘብ ምክንያት ብዙ የቤተክህነቱ ሠራተኞች ችግር ላይ በመውደቃቸው የፓትርያርኩን ጉዳይ በኛ በኩል መመልከት አስፈላጊ ሆነ። በኢህአዴግ የተቋቋመው በካህኑ የሚመራው ኮሚቴ የፓትርያርኩ ወንጀል ናቸው ብሎ ያቀረበውን ተቀብሎ ለመወሰንና ፓትርያርኩን በዚህ ምክንያት ለማውረድ የፈጠራ ውንጀላዎች በመሆናቸው ሲኖዶሱ አልተቀበላቸውም። ። ሌላ ዘዴ ፈለግን። ፓትርያርኩ በሕመም ምክንያት ሊሠሩ ባለማቻላቸው ሥልጣናቸውን ለሲኖዶሱ አስረክበዋል የሚል ውሳኔ ላይ ደረስን። በሽታቸው ኢህአዴግ መሆኑ ግልጽ ነው። ይህንኑ ውሳኔ ለኢህአዴግ አቀረብን። ተቃወመው። "ወንጀል አለባቸው ብላችሁ አውርዱ፤" ተባልን። እኛ ደግሞ ያላየነውን ወንጀል "አለባቸው" ብለን መወሰን ፍፁም ትክክል አለመሆኑን ገለጽን።

ከዚያም ፓትርያርኩ መንበረ ፓትርያርኩንም መኖሪያ ቤታቸውንም ለቀው እንዲወጡ ወያኔ ትዕዛዝ ሰጠ። "እንደሱ ከሆነ ለመኖሪያቸው ቤት ይሰጠን" ብለን ብንጠይቅ ተከለከልን። ለኑሮአቸው መደጎሚያ ካለን ገንዘብ አበል ፈቀድንና ለጊዜው ለሕይወታቸውም ስለፈራን ገለል ማድረጉን መረጥን። እኔ እንግዲህ እንደራሴነቴ ለእሳቸው ስለሆነ መልቀቅ አለብኝ ብዬ በገዛ ፈቃዴ ለቀቅሁ። ሲኖዶሱ እንደገና መረጠኝ፣ ልምዱ አለህ ብሎ። እኔም ከሲኖዶሱ ጋር ሥራ እንደጀመርን የወያኔ ወታደር መጥቶ መንበረ ፓትርያርኩን፣ የቤተክህነቱን ጽ/ቤት በሙሉ አሸጎ ሄደ። ከዚያም አቡነ ያዕቆብ የሚባሉ ኤርትራዊ ጳጳስ ኢህአዴግ አስቀመጠ። ከሲኖዶሱ ያፈነገጡ ስድስት ጳጳሳት (በሙሉ የትግራይ ተወላጅ የሆኑ) ጨምረው አቡነ ያዕቆብ ሥራ ጀመሩ።

የመጀመሪያው ሥራቸው ፓትርያርኩን የማውረጃ ወንጀል ማዘጋጀት ስለነበር ይህንኑ አከናወኑና የሲኖዶስ አባላት የሆኑትን ከያሉበት በመፈለግ ለማሰባሰብ ሞከሩ። ፓትርያርክ በሕይወት እያለ ሌላ ፓትርያርክ መሾም በኦርቶዶክስ ሃይማኖት ፈጽሞ የማይቻል በመሆኑ እሳቸውን ወንጅሎ አንድ ነገር ለማድረግ ሩጫው ተጧጧፈ። ለዚህም የሲኖዶስ አባላትን በተደጋጋሚ ለስብሰባ ጠሩ። እንሰበሰብም ቢሉ ማስጠንቀቂያና ማስፈራሪያ ተደርጎባቸው ተሰበሰቡ። የፓትርያርኩ ወንጀሎች ናቸው በተባለው ሰነድ ላይ ፈርሙ ቢባሉ አንፈርምም አሉ። አሁን ኢህአዴግ እንደገና በነገሩ ገባና የሲኖዶስ አባላትን በሙሉ ሰብስቦ ማስጠንቀቂያ ሰጠ። ያም ውሳኔ ተቀባይነት አግኝቷል ተብሎ ፓትርያርኩ ወርደዋል ተብሎ በምትካቸው አባ ጳውሎስ ከኒውዮርክ እንዲመጡ ተደርገው እሳቸው ተሾሙ። ታሪኩ ይኸው ነው። በሳቸው አማካይነትም አዲስ ሲኖዶስ ተቋቋመ ተባለ። ቀደም ሲል የነበሩት የሲኖዶስ አባላት በማስፈራራትም በማባበልም ተመልሰው የዚህኛው ሲኖዶስ አባል እንዲሆኑ ተደረገ። በሕገ ቤተክርስቲያን ማለትም በምሥራቁ ኦርቶዶክስ ሕግ አንድ ፓትርያርክ በሕይወት እያለ ሌላ ፓትርያርክ ሊሾም ስለማይችል አሁን ተሾሙ የተባሉት አባ ጳውሎስም ሆኑ በሳቸው ስር የተቋቋመው ሲኖዶስ ሕጋዊነት የላቸውም። ስለዚህም ሕጋዊው ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆርዮስ ናቸውና እሳቸውም በስደት ላይ ያሉ በመሆኑ ሕጋዊ ሲኖዶስም በስደት ላይ ነው።

**ላንዳፍታ -**
በቅርቡ እርሶን ብፁዕ አቡነ ይስሃቅን፤ ብፁዕ አቡነ መልከጼዴቅንና ብፁዕ አቡነ ኤልያስን ጨምሮ በኒውዮርክ በተደረገው ስብሰባ ሲኖዶስ መቋቋሙ በዜና ተገልጿል። ስለዚህ ሲኖዶስ አመሠራረትና ተግባር እንዲሁም ዕቅዱን ቢገልጹልን፤

**ብፁዕ አቡነ ዜና ማርቆስ -**
ለሲኖዶሱ መቋቋም ትልቅ አስተዋጽዖ ያደረገውን በ1992 የተቋቋመውን ማህበረ ቤተክርስትያን ዘተዋህዶ የተባለውን ማህበር ማስተዋወቅ እፈልጋለሁ። አስራ ስምንት አብያተ ክርስቲያናት ያቀፈው ማህበረ ቤተክርስቲያን ዘተዋህዶ ስለአንድነት፣ ስለኢኮኖሚ፣ በተለያዩ አካባቢ ያሉ ቤተክርስቲያናት ሰበካ ጉባዔዎች ግኑኝነት በመስጠት መንበረ ጵጵስናውን የሚያጠናክር ማህበር ነው። የዚህ ማህበር ተግባር ከላይ የገለጽኩትን የሚመለከት ሲሆን ሲኖዶሱ መንፈሳዊ መመሪያ የሚሰጥ፣ ስለጵጵስና፣ ክህነትና ሕገ ቤተክርስቲያን ውሳኔ የሚሰጥ ይሆናል። በመጀመሪያ ዳላስ ላይ በተደረገው ስብሰባ የፓትርያርኩን እውቅና ተቀበልን። እውነተኛዋ ቤተክርስቲያናችን በስደት ላይ መሆኗ ታወቀ። ይህ ሲኖዶስ ዓለማቀፋዊ ነው። ካናዳ፣ ስዊድን፣አውሮፓ፤ አፍሪካም ውስጥ

የተቋቋሙትን አብያተ ክርስቲያናት ያጠቃልላል። አሁን የቋቋመው ሲኖዶስ ዕቅዶች ከሞላ ጎደል፣
1ኛ/ ጽ/ቤቱን ማቋቋም፣
2ኛ/ የቅርብና የሩቅ ጊዜ ዕቅድ አዘጋጅቶ በስደት ያሉትን አብያተ ክርስትያናት ማስተባበርና ማደራጀት፣3ኛ/ ሀገር ቤት በቤተክርስቲያናችን ውስጥ እየተደረገ ስላለው የሐይማኖቱ መከፋፈል (ተዋህዶና ተሃድሶ) ማጋለጥና እውነተኛው ኦርቶዶክሳዊ ትምህርት የሚደርስበትን ሕዝቡ ትክክለኛውን እንዲያውቅ ማድረግ።
4ኛ/ በስደተኛው ሕዝብ መካከል አለመግባባት እየፈጠሩ መለያየትን የሚያመጡ ሁኔታዎች ሊጠፉ የሚችሉበትን መንገድ መፈለግና የሕዝቡን አንድነት ጠቃሚነት ማስተማር ናቸው።

**ላንዳፍታ -**
ብፁዕነትዎ በስደት ላለው ሕዝብና በስደት ለተቋቋሙት አብያተ ክርስትያናት የሚያስተላልፉት መልዕክት ካለ፤

## ብፁዕ አቡነ ዜና ማርቆስ -
በዚሁ አጋጣሚ በስደት ለሚገኘው ሕዝባችን የምናስተላልፈው መልዕክት አለ። ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴዎስ ወንጌል ም 12 ቁ 25 ላይ " እርስ በርሷ የምትለያይ መንግሥት አትፀናም፤ እርስ በርሷም የምትለያይ ቤት ወይ ከተማ ትፈርሳለች/አትቆምም፤" ሲል ባስተማረን መሠረት በልዩ ልዩ ምክንያት ከመለያየት አንድነትን፣ ከጥላቻ ይልቅ ፍቅርን መሥርተን በያለንበት ለአገራችን አንድነት መከበር መሥራት፣ወደ እውነተኛው አምላካችንም ማመልከት ይኖርብናል። ይህንንም አገር ቤት ካለው ህዝባችን መማር ይኖርብናል። ለረጅም ጊዜ ህዝቡን በሃይማኖትና በዘር እየከፋፈሉ እርስ በርሱ የሚጠፋፋበትን መረብ ቢያዘጋጁበትም ህዝቡ ግን ተከባብሮና ተቻችሎ ያለመሪ፣ ያለፖሊስና ያለዳኛ ራሱን በራሱ እየመራ ይገኛል። በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ስለአገራችን አንድነት መከበርና ከመበታተን ለማዳን በአገር ውስጥ ላለው ህዝብ ጽኑ ድጋፍ መሆን እንዳለብን እናስገነዝባለን። ለአገራችን አንድነት ቤተክርስቲያናችን ያደረገችው አስተዋጽዖ ከፍተኛ መሆኑ ይታወቃል። ይህንን በሚገባ የሚያውቁ ቀንደኛ የአገራችን ጠላቶች ህዝቡን ለመበታተንና እምነቱን ለማዳከም በመጀመሪያ ያተኳሩበት ኢላማቸው ቤተክርስቲያናችን ላይ ነበር። በዚህም የቤተክርስቲያኒቱን ራስ (ፓትርያርኩን) ከሥልጣናቸው ካወረደ በኋላ በምትካቸው የራሳቸውን ፈቃድ ፈፃሚ የሆኑትን አሻንጉሊት ከቅዱስ መንበር ላይ ካስቀመጠ በኋላ ሕዝቡንና ሀገሪቱን ለመበታተን ሁኔታዎችን በማመቻቸት ላይ ነው። ስለዚህም እንደቀደሙት አባቶቻችን የአገራችን ዳር ድንበር፣ የህዝባችን አንድነት እንዲከበር፣ በግፍ የታሠሩ ወገኖቻችን ከእግዚአብሔር ዘንድ እውነተኛውን ፍርድ እንዲያገኙ በየአብያተክርስቲያናቱ፣ በማህበር በየግለሰብም ቤት ሁሉ የዘወትር ጸሎተ ምህላ እንዲደረግ በድጋሚ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን።

### ብፁዐነ ሊቃነ ጳጳሳት


ብፁዕ አቡነ ዜና ማርቆስ


ብፁዕ አቡነ ይስሃቅ


ብፁዕ አቡነ መልከጼዴቅ

# ታደሰ አስራት

## ኢትዮጵያዊው የፊልም ባለሙያ



ታደሰና የፊልሙ ዲሬክተር ዴቪድ ዚጋር

በቅርቡ "Displaced in the South" የተሰኘ ሰነዳዊ (Documentary) ፊልም በአትላንታ የታሪክ ማዕከል (Atlanta History Center) የመጀመሪያው ትርዒት ታየ። አንድ ሰዓት ተኩል የሚፈጀው ፊልም የሚያተኩረው በደቡብ ዩናይትድ ስቴት ግዛቶችች ያሉትን ስደተኞች አኗኗርና ባላባቻው ችግር ላይ ነው። ከቬትናምና ከሜክሲኮ የሚመጡ ስደተኞች ላይ በብዛት የሚያተኩረውን ይህን ፊልም በተመለከተ ይህንን ዜና ያቀረብንበት ዋናው ምክንያት በፊልሙ ዝግጅት የተሳተፈውን ኢትዮጵያዊውን ታደሰ አሥራትን ለማስተዋወቅ ነው።

ሰፋ ያለ የዝግጅት ክፍል አባላት መካከል በከፍተኛ ደረጃ የሚታዩት ዋና አዘጋጆቹ ዴቪድ ዚጋርና ኤሪክ ፎርድ እና የፎቶግራፊ ዲሬክተሩ (Director Of photograph) ታደሰ አሥራት ናቸው። ጠቅላላ የፊልም ማንሳቱን ሥራ ያከናወነው ታደሰ አሥራት ሲሆን በዚህ የዝግጅት ሥራ ብቸኛ ኢትዮጵያዊ ብቻ ሳይሆን ብቸኛም ጥቁር ነው። የፊልሙ የመጀመሪያው ትርዒት በታየበት ምሽት 1,000 በላይ ተመልካች የተገኘ ሲሆን ከትርዒቱ በኋላ አዘጋጆቹ ሲተዋወቁ የታደሰ ተራ ደርሶ ወደ መድረክ ሲወጣ አዳራሹ በጭብጨባ ማስተጋባቱን በቦታው ተገኝተን ለማየት በቅተናል። ከትርዒቱ በኋላ በተደረገው ሪሲፕሽን ወቅት ከታደሰ ጋር ለመተዋወቅና ፊርማውን ለማግኘት ብዙ ተመልካቾች ከበውት ስናይ በጣም የሚያኮራ ድርጊት መሥራቱን ለማረጋገጥ በቅተናል።



ታደሰ በሄሊኮፕተር የሚያነሳበትን ፊልም ሲያዘጋጅ

በኢትዮጵያ ቲቪ ከካሜራ አንሽነት ጀምሮ እስከ ክፍል ኃላፊነት የሰራው ታዳሰ አሥራት በ1982 (እ.ኤ.አ.) ወደ ፕራግ ቼኮዝሎቫኪያ በመሄድ በፊልም አካዳሚ ትምህርቱን የቀሰመ ሲሆን ከዚያም በማከታተል በስዊዘርላንድ፣ በጀርመንና በዩጎዝላቪያ የበለጠ ዕውቀትን ያዳበረ መሆኑን ልንረዳ ችለናል። እዚህም አሜሪካ አገር ከፍተኛ ፊልሞች ለመሥራት በሚያስችል ምት ኮንትሮል ሂድና ከሄሊኮፕተር ለማንሳት በሚያስችል መሣሪያዎች ላይ ተጨማሪ ሥልጠናዎችን ወስዷል።




ከፊልም ማንሻው ካሜራ ጋር

ሌሎች ፊልሞች "The Brake" "Grass Root", "Fried Green Tomatoes", "Walking Dead" በተሰኙ ታዋቂ የፊቸር ሥራዎች ላይ ባለው ሙያ ተሳትፎል። በአሁኑ ጊዜ በግል ኮንትራት በመያዝ ፊልሞች በአትላንታና በሌሎች ከተሞች እየሰራ ነው። ፊልሙ በpublic Tv. (Chanel 8 or 30) 10:00 pm Feb 20 ምሽት ይታያል።

ታደሰ ባለትዳርና የሁለት ልጆች አባት ሲሆን የሚኖረው አትላንታ ከተማ ነው።

አዳም ሔዋን

# አላለልኝ ይሆን

ከትዝታ አለባቸው

## የመጨረሻው ክፍል

በዚህ ዓይነት የኑሮ ውጣ ውረድ፣ የስሜትና ፍላጎት አለመረጋጋት ውስጥ ያለፍኩ በመሆኔ አሁን የማደርገውና፣ የማስበው፤ የማልመውና የምመኘው ነገር ሁሉ በዚሁ ላይ የተመሠረተ ነው ብል የምሳሳት አይመስለኝም። ባል ማግባት በርግጥ ፈልጌያለሁ። ግን ማግባት የምፈልገው ባል እኔ ባወጣሁት ፎርሙላ መሆን አለበት። ጥንትም ማድረግ እንዳለምኩት አሁንም የማገኘውን ወንድ ያልሆንኩትን ነኝ ብዬ፣ ያላደረኩትን እንዳደረግሁ አድርጌ በመዋሸት ነው የምቀርበው። ብልጥ ሆኖ መገኘት፣ አለመበለጥ፤ በቃ አለ አይደለ ፋራ፣ ጥፍራም፤ ድሮ በኛ ዘመን ቋንቋ ደግሞ ጀጋ፣ ገሪባ አለመሆን ለዚህ መድሃኒቱ ደግሞ መዋሸት። ደግሞ ይህ ብቻ መሰላችሁ። ጉራ፣ ደግሞ አለ። ትንሿን ችሎታ በጣም አጉልቶ ትልቅ አድርጎ ማውራት፣ ማስወራት፣ «ጉራ መንዛት፣ መንጠባረር»... ምን አባቱ! ለየትኛው ዓለም! በዚህ አቀራረብ ያመጣሁትን ወንድ ደግሞ እኔ የምፈልገውን ነገር ሁሉ ማድረግ አለበት። የማልፈልገውን ማድረግ የለበትም። ከሱ የተሻለ ከመጣ ደግሞ «በጨረታው አልገደድም» እሱም ጭራሽ እንዳይሸሽ ለጊዜው ራቅ አድርጎ አዲስ ከመጣው ጋር መንጎድ፤ ድንገት ከአንዱ ጋር ስሄድ ሌላኛው ካየ «የእኅቴ፣ የአክስቴ ልጅ» ብሎ ማታለል። ማምታታት! ይህ ነው እንግዲህ ያለፍኩበት የሕይወት ድራማ። በዚሁ ፎርሙላዬ ተጠቅሜ ደግሞ ባል ፍለጋ ዘመቻ! አሁን!

አንዴ እዚሁ አሜሪካን እንደመጣሁ ያደረግሁትን ልናዘዝላችሁና ወደ ዋናው ታሪኬ ልግባ። በመጣሁ በአንድ ዓመት ውስጥ ወደ አራት ቦይ ፍሬንድ አፈራርቄያለሁ። የዛሬ አስራ አራት ዓመት ገደማ የሆነ ነው። የነበርኩት አሁን ካለሁበት እስቴት የተለየ ቦታ ነበር። አራት ቦይ ፍሬንድ ስላችሁ ሁለቱን በአንድ ጊዜ የያዝኳቸው ነበሩ። (አደራችሁን በአስራ ስድስት ዓመት የአሜሪካን ኑሮዬ ያወጣሁዋቸውን ወንዶች ቁጥር አትጠይቁኝ)። እና እንዲህ ሆነ። ከአንደኛው ጋር ሆኜ አንድ አበሻ ፓርቲ እሄዳለሁ። ከዚህኛው ጋር መውጣት ከጀመርን አንድ ሁለት ወር ሆኖን ነበር በዛን ወቅት። ፓርቲው ላይ ሌላኛውን ሳየው ወከክ አልኩ። ይህኛው አብሮኝ ያለው የሌለው ያኛው ያለው እኔ ደስ የሚለኝ አንድ ነገር አየሁበት። ልተዋወቀው ፈልግሁ። ከኔ ራቅ ብሎ ከተቀመጠበት ቦታ እኔን የሚያይበትን አጋጣሚ ጠብቄ ፈገግታ ወረወርኩለት። አራዳ ብጤ ነበረና ገባው። ተነስቶ ወደኔ እየመጣ

መንገድ ላይ እያለ ይህ አብሮኝ የተጎለተውን የምሸውድበት መንገድ አሰብኩና ወዲያው መጣልኝ። አጠገቤ ያለው ጎልት ሳያስበው

«ወይኔ! አሰፋ» ብዬ ጮህኩ።

«የማነው አሰፋ?» አለኝ፤ አጠገቤ የነበረው።

«የአጎቴ ልጅ፤ ይገርማል እኮ!» ብዬ ስጨርስ ያኛው አጠገቤ ደርሶ ኖሮ ብድግ ብዬ

«አሰፋ! አንተ አሰፋ፣ ወይኔ አኔ አላምንም» ልኩና እዚያው ተጠመጠምኩበት። እሱም ቢሆን

«የማን ቀውስ ናት» ሳይለኝ አልቀረም። በሆዱ። እሱም ምንጨነቀው ተጠመጠመብኝና ጉንጭ ለጉንጭ ተሳሳምን።

«ታዲያስ ዳህና ናሽ!» አለኝ።

«ደህና መቼ መጣህ?» አልኩት

«ቆይቻለሁ» አለኝ በደፈናው ነገር ነገሩ የገባው መሰለኝ።

«በል ና ላስታዋውቅህ» አልኩትና ከኔው ጉልት ጋር አስተዋወቅሁት።

ሲተዋወቁ ስሙን «አሰፋ» ብሎ ተዋወቀው ትንሽ እንዳወራን

«እናንተ ጥቂት አውሩ» አለንና የኔው ጉልት ጥሎን ጎደኞቹ ጋ ሄደ።

ይህኛው ለምን በሳቅ አይፈነዳም መሰላችሁ። «ምን ያህል ቢደብርሽ ነው?» አለኝ።

«ዝም ብሎ ጀጋ ብጤ ነው» አልኩት።

እውነተኛ ስማችንን ተቀያየርንና ለመደዋወል ስልክ ተሰጣጠን። ከዚያም ሁለቱን እየፈራረቅሁ ማውጣት ጀመርኩ። መጀመሪያ ያወጣሁት ከዚህኛው ጋር ሲያየኝ ምንም እንደማይሰማው እወቁ፤ የአጎቴ ልጅ ብዬ ስላሳመንኩት። ያኛው በኋላ ያወጣሁት ነገሩን እየወቀ ስለሆነ የገባበት ግድ የለውም። እንዲያውም ይንን በቅርቡ እንደምተው ነገርኩት። ሁለቱም እንደዚያ እየሸዋወድኩ ማውጣት ለኔ እንደአንድ ትልቅ ኩራት ነበር የሚታየኝ። አዋቂ፤ አራዳ፤ ጎበዝ አድርጌ ራሴን የምለካበት ዘዴዬ ነበር። እንደዚህ እየሸወድኩ የምሰራው ነገር የልብ ትርታዬን ይጨምረዋል። እረካበታለሁ። አሸናፊነት ይሰማኛል።

ታዲያ ሁለቱንም እንዲሁ እያፈራረቅሁ፣ ለሁለተኛውም ያኛውን እንደተውኩ አድርጌ በማሳመን ለአንድ ስድስት ወር ካወጣሁዋቸው በኋላ ሁለቱንም በሁለት ሳምንት ልዩነት ዘጋሁዋቸው፤ (Dump አደረግሁዋቸው)። አቤት ወንድን Dump ሳደርግ ይሰማኝ የነበረው እርካታ። «እንትና እኮ እንትናን Dump አደረገች» መባል እኮ ራሱ ኩራት ነው! አይመስላችሁም።

እስቲ ይህን ለናሙና (Sample) ያህል ያቀረብኩላችሁን ከብዙዎቹ አንዷን ታሪኬን ገምግሟት። ስንት ውሸት ተደረገበት፤ ስንት ተንኮል ተሰራበት። ከዚህ ነው እንግዲህ የአሁኑ እኔነቴ የሚመነጨው፤ የአሁኑ ባህርዬ የሚመሠረተው። ዛሬ ጊዜው መሽብኝና የባል ያለህ ብዬ አደባባይ ስወጣ ያ አብሮኝ ያደገው የተቅበዘበዘው ባህርዬ እፊቴ ድንቅር እያለ አሰቸገረኝ መሰለኝ።

በንፁህና በትክክለኛ መንገድ የመጣውን ሁኔታ ሁሉ በዛው መልኩ መቀበል አቃተኝም መሰለኝ። እና ይህ ሁሉ ሆኖ ሳለ እኔን ብሎ፣ ስቴት አቋርጦ ያውም ስንት ያወራሁት፣ ስንት ያጫወትኩት ሰውዬ እቤቴ ድረስ ሲመጣ ምን ነካኝ? እውነት እንደነገሩ ስለሆነ ነው? አይደለም። ይህ የኑዛዜዬ መጨረሻ ነውና ያኔ ሳይሆን ዛሬ በፀፀት የሚሰማኝን፣ ለዚህ ምናልባትም ምክንያቱ ይሆናል ብዬ የገመትኩትን ልንገራችሁ።

ገና ያኔ መጀመሪያ ላይ ስንተዋወቅና በስልክ መነጋገር ስንጀምር የሆነ ነገር ሆኖ ነበር። ትውውቅ ሲደረግ መቼም ልማድ ነውና መግባባትን ለመፍጠር ስለ ዓላማ፤ ስለፍላጎት ስለ ስሜት (Interest) መነጋገር ያለ ነው። እኛም ብዙ አውርተናል። ብዙ ተባብለናል።

«ይህን እወዳለሁ፤» «ይህን እጠላለሁ፤» «እኔ እንደዚህ ነኝ፣» እንደዚህ ያለ ነገር ያናድደኛል፣» እየተባለ የሚወራው ዓይነት ነገርበትውውቅ ማግስት የሚነሱ ጉዳዮች ነበሩና እኛም በዚሁ ነገር ላይ ብዙ ተነጋግረን ነበር።

በዚህ ወቅት ታዲያ ያቺው አብራኝ ያደገችው መቀላመድ፣ ያልሆኑትን ሆኖ መታየት፤ ጉራ መቸርቸር፤ ሥራዋን ሰርታ ነበር ብዬ ስናገር አሁን በፀፀት ነው። ከልቤ ነው የምላችሁ በፀፀት ነው። እሱን ለማስደሰትም ይሁን ወይ መስሎ ለመታየት፤ ወይ ደግሞ ራሴን ለመካብ ስል ስለኔ በስልክ የነገርኩት ነገሮች በአብዛኛው ውሸት ነበር።

ያልሆነ፣ ያልተፈጠረ፤ ያልሆንኩት፣ ያላደረኩትን ነገር ሁሉ ጨምሬ ጨማምሬ ነበር የነገርኩት። ያኔ ይህን ሁሉ ውሸት ስነግረው በትክክል ማድረግ የሚገባኝ፣ ማለት የሚገባኝ (Normal) ነገር አድርጌ ነበር የወሰድኩት።

ምናልባትም በኔ ላይ ያለውን ግምት ከፍ እንዲያደርግ ያድርግሁት ሊሆን ይችላል። አስታውሱ እሱ የተማረ፣ በሙያው ጥሩ ሥራ ያለው፤ የአሜሪካን ኑሮ ቆይታውን በቁም ነገር ያዋለ፤ እኔ ደግሞ በመዝለል፤ ቁም ነገር ያለው ነገር ሳልሰራ ዕድሜዬን የጨረስኩ፣ ትምህርት ቤት ደጃፉን ያልረገጥኩ ነኝ። እና ከሱ የምበልጥ እንጂ የማላንስ፣ ባይሆን እንኳን እኩል ነኝ ለማለት እንዲያስችለኝ ብዬ በማሰብ ነው። ደግሞ ምናለበት የተለመደ ነው። እና ብዙ የዋሸሁት ነገር ነበር። እሱን ግን እዚህ መጥቶ እንዳየሁት ኮስታራ ብጤ ስለሆነ ለኔ መቀላመድ ጥሩ ግምት እንደማይሰጠኝ ተረዳሁ። የውሸት መዓት አውርታችሁ ሁኔታዎች ሁሉ ሊያጋልጡአችሁ ሲሉ የሚሰማችሁ ስሜት አለ አይደል? እሱ ዓይነቱ ነበር የኔ ሁኔታ። ያቅበጠብጣል፣ ቁጣ ቁጣ ያሰኛል። ማነው በውሸታምነት መጋለጥ የሚፈልገው? እና የኔም ችግር ይህ ነበር። ምን ነበር የዋሸሁት ነገር? ይህን ሁላችሁም ለማወቅ የምትጓጓት ነገር ነው።

በመጀመሪያ የዋሸሁት ስለ ሥራዬ ነው። መቼም እዚህ አሜሪካ አገር ስንኖር ሥራ ማማረጥ የለም። ሁሉንም ዓይነት ሥራ ነው የምንሰራው። እና እኔም የምሰራው ቀን ቀን በአንድ ሱቅ ካሽር ሆኜ በሳምንት እራት ምሽት ደግሞ በአንድ ምግብ ቤት በአስተናጋጅነት ነው። (waitress)። ሁላችሁም እዚህ አሜሪካ ያላችሁ ታውቃላችሁ፤ የምግብ ቤት አስተናጋጅ መሆን ሆነ ሱቅ ውስጥ ካሽር ሆኖ መሥራት የሚያሳፍር አይደለም። እንደው ለምን እንደሆነ እንጃ ይህን መናገር ብዙ ጊዜ አልፈልግም። እና ለዚሁ ሰውዬ የነገርኩት ይህንኑ እውነተኛውን ሥራዬን ሳይሆን የReal State Broker ነኝ ብዬ ነው።

አንድ ትልቅ ቢሮ ውስጥ ቁጭ ብዬ የምሠራ አድርጌ ነው ራሴን ያስተዋወቅሁት። አንድ ቀን በስልክ የተነጋገርን ዕለት የደወልኩት ከቤቴ ሆኜሳለ «ከየት የምደውል ይመስልሃል?» ስለው «እኔ እንጃ!» ቢለኝ «ቢሮዬ ወንበሬ ላይ እየተሽከረከርኩ ነው» አልኩት ውሸቴን እኔ ግን

የነበርኩት ቤቴ ኩቺና ውስጥ ነበር። ሰው እኮ አንዴ ዋሽቶ ይተዋል። እኔ ግን ደጋግምኩት። በሥራዬ ላይ ያጋጠመኝ ነገር እያልኩ እየፈጠርኩ የምሠራቸው ነገሮች ሁሉ አሁን ሳስታውሳቸው ይሰቀጥጡኛል።

ይህ ብቻ አይደለም። እሱ የተማረ፣ በሙያው ሥራ የያዘ፣ በአነጋገሩና በአመለካከቱ የበሰለ ስለሆነ ለኔ ጥሩ ግምት እንዲኖረው በማሰብ የማላውቀውን አውቃለሁ፤ ያልተረዳሁትን ተረዳሁ፤ የማልወደውን እወዳለሁ እያልኩ የቀባጠርኩት ብዙ ነገር ነበር። ታዲያ «ተፈጥሮን ተመክሮ» አይመልሰውም ነውና፣ ምንም ሳወራው ቀላል ቢመስለኝም በተግባር ያልኩትን ሁሉ ሆኜ ለመገኘት ኋላ እንደሚያስቸግረኝ ለምን እንዳልተገነዘብኩ ይገርመኛል።

መዋሸት፤ መቀባጠር፤ ያልሆኑትን ሆኖ መታየትና፣ የማያውቁትን ሁሉ አውቃለሁ ብሎ ግትር መሆን ከእውነቱ ምንም ያህል ፈቀቅ አያሰኝም። ይህን ነው ለእህቶቼ የምመክረው። ያልሆኑትን ሆኖ በመታየት የሚገኘው ተራ እርካታ እውነቱ ተጋልጦ ሲወጣ ከሚያሳድረው እፍረትና መሸማቀቅ የተሻለ ነው ብሎ ማመን ያስቸግራል።

በሐሰት የተሞላ ሕይወት ከሰው ያርቃል። በሆነው ባልሆነው እንድንነጫነጭ ያደርገናል። የኔም ኑሮ በዚህ የተገነባ ስለሆነ ነው ያቅበጠበጠኝ፤ ያነጫነጨኝ። ጠንከር ብለው ሲመጡብኝ የተነቃብኝ እየመሰለኝ ቁጣዬ ይቀድማል። እንግዲህ በዚህ ባህርዬ የሚስማማኝ ባል አግኝቼ፣ ትዳር መስርቼ፣ ልጆች አፍርቼ እኖራለሁ የሚል ምኞቴ የነፋስ ምኞት ነው። ምናልባት የኔው ብጤ ቀላማጅ መጥቶ እምታቶ በቁጥጥሩ ስር ያገባኝ እንደሆነ ነው እንጅ ቁምነገረኛ ሰው በቁምነገረኛነቱ እኔን ማርኮ ሚስቱ እሆናለሁ የሚለው ተስፋዬ እየመነመነ በመሄዱም ነው «አላለልኝ ይሆን» ያልኩት።
በሉ ደህና ሁኑልኝ።

ለኔም የሚበጀውን ያምጣልኝ።

ተ ፈ ጸ መ

---

## እስቲ ይህችን ጥያቄ መልሱልኝ

?? እንዲያው ከመሬት ተነስተሽ ፍረጪ ፍረጪ ይለኛል።
(አበበች ከቶሮንቶ)
■ ውፍረት ይሆን?
---
?? ድርጅቱም፣ ሁሉም አንድ ሰሞን አለን አለን አለና አሁን ፀጥ አለሳ!
ምነው?
(ከተማ ከላስ ቬጋስ)
■ እርሶ ፀጥ ብለው ይሆን?
---
?? እወድሻለሁ ይለኛል፣ ላግባሽ ግን አይለኝም፤ እንዲያው ለነገሩ
የቤቱን ስልክ ቁጥር ለምን ከለከለኝ? (ፍሬህይወት ከዳላስ)
■ ስልኩ በቢል ምክንያት ተቆርጦበት ይሆን ወይስ ባለትዳር ነው?
---
?? ፈረንጆቹ ስሜን መጥራት ቢያቅታቸው ባጭሩ «አስ» በሉኝ አልኩዋቸው።
ጓደኞቼ ግን ደስ አላላቸውም። (አስናቀች ከሲያትል)
■ ወየው ጉድ! አንቺ "አስ" መባል ከተስማማሽ ምን ጨነቃቸው።
---
?? እንደው የሚለያየን እንጂ የሚያቀራርበን ምነው ብቅ አልል አለ?
እንዳንዴ ሳስበው አልቅሽ አልቅሽ ይለኛል። (አስቴር ከአትላንታ)
■ ከምታለቅሽ ጠንከር ብለሽ የሚለያየነን ነገር ብትታገይ አይሻልም።
---
?? ባሌ ሁለት ሥራ እየሠራ ማታ ሲገባ ድክም ብሎት ይተኛል፣ ምን
ይሻለኛል? (ዳርዬ ከሳንፍራንሲስኮ)
■ ለሦስተኛ ሥራ ከሆነ ቀስቅሺው።
---
? ? ? ? ? ? ? ? ? ? ? ? ? ? ? ? ? ? ? ? ? ? ? ?

# የኮለምበስ ጉዞ

## ልብ ወለድ

(ከአብዬ)

ውቢት መንገሻ የሞላት የተረፋት፣ ሺህ ብር የምትቆጥር ቀጭን እመቤት መሆን የልጅነት ምኞቷ ነበር። ሀብታም ለመሆንም ያላደረገችው ነገር ያልፈነቀለችው ድንጋይ የለም። ዳሩ ሀብታም መሆን የማይፈልግ ማን ይኖራል? የውቢት መንገሻ ግን ለየት ይላል። ስታወራ ብትውል ስለ ገንዘብ ነው። ስታስብ ስታሰላስል የምታድረው ገንዘብ የሚገኝበትን መንገድ ነው። ገንዘብ በጣም ትወዳለች። እንደገንዘብ መውደዷ የገዛ እናቷን እንኳ የሚገዛት ብታገኝ ትቀውራታለች።

ገንዘብ ይገኝበታል ብላ በገመተችው መስክ ሁሉ ተሰማርታለች። አቅሟ የፈቀደውን፣ ባልተማረ ጭንቅላቷ የመሰላትን ሞክራለች። ችሎታዋን ሳትመዝን በድፍረት አይገቡ ገብታ ታውቃለች። አንዳንዴ ዕድልም ነው መሰል ብዙ የደከሙለትና የጓጉለት ነገር ቶሎ እጅ አይገባም። እንደገንዘብ መውደዷ ገንዘብ እጇ አልገባም። ፀጉር ቤት ከፍታ ነበር አልሆነላትም። አንድ ሰሞን ብቅ ብቅ የሚሉ ደንበኞቿ ድርሽ ማለት ሲተዉ ፀጉር ቤትነቱን ተወችውና መሶብ ቤት አደረገችው። ለአንድ ወቅት ስም ያለው ሬስቶራንት ሆነላት ግን አላዋጣም። ለመጣው ሁሉ ቅልጥም አቅርቦ በእናቱ ቅቤ ጨምሮ ጠብ የሚል ነገር አላገኘችበትም። ተወችው። Import-Export ንግድም ጀምራ ነበር። ትምህርት የሚጠይቅ የማትወጣው ሆነባት። ወደ ዱባይ ለመመላለስም ብዙ አስባለች። ያለ በቂ ገንዘብ የማይሞከር ሲሆንባት ተወችው። ግን ሀብታም ለመሆን ምኞቷን ትታው አታውቅም።

ባለፀጋ ባል አግብታ ዲታ ለመሆን ሀብታም ናቸው የተባሉትን ሰዎች አጥምዳ ታውቃለች። ሆዱን የሚወድ ለመሰላት ጠቦት እያረደች ስትቀልብ፣ ፍቅር የሚፈልግ ለመሰላት መውደድ ያነፈዛት ስትመስል ከርማ ወጥመዷ ሳይዝላት ቀርቷል። ወንዱ አይጨበጥም። ወረተኛ ነው። መታመኛ ነገር የለውም። ስንቱን ከርሳም ስታበላ ከርማ የሚተርፋት መሞኘቷና ያችኑ እንደእናቷ ልጅ የምትወደውን ገንዘቧን መከስከስ ብቻ ነው።

በዚህ መሃል ዕድሜ ነጎደ፣ አያቆሙት ነገር እንዴት ተደርጎ! የልጅነት ወዟ አልቆ፣ የሴትነት ወጓ ሊያበቃ ተዳርሳለች። የምትወደው ገንዘብ እንደልቧ ከእጇ አልገባም። ወይ ትዳር የላት ወይም ደህና ወዳጅ እንኳን አላቆየችም። ከአንዱም ሳትሆን እድሜዋ ማለቁ እንደ እግር እሳት ያንገበግባታል። እንዲያም ሆኖ ተወዛዝታ ተቀባብታ አበሳዋን አይታ ወጣ ስትል ብዙም አታሳጣም።

አሁን የምትኖርበትን አነስተኛ ቤቷን ቡና ቤት ከፍታበት ዛሬ ዛሬ ምንም አትል። ደህና ገንዘብ ይዛለች። እንደምኞቷ ብዙ ሺህ ብር የምትቆጥር፣ ቢጠሯት የማትሰማ ዓይነቷ እንኳ ባትሆንም ደህና ትነግዳለች። ንብረት አፍርታለች። አሁን አልቋጠር አልያዝ ያላት የትዳር ነገር ነው። የወንዶች ነገር አልዋጣልሽ ብሏት ተቸግራለች። ዛሬ ዛሬ ባለፀጋም ባይሆን ግድየላትም። ችግሩ ወንዱ ሁሉ ስንት ሲቀሳፍትና ሲያወራ ከርሞ የልቡ ሲደርስ ጉዳዩ ሲያበቃ እንደ አሮጌ ቁና ጎልቷት ይጠፋል። አንዳንዱ ቀጣፊ መልቲ ነው። አንዳንዱ ደግሞ ጉረኛ ዋሾ ነው። የአንዱን ሲሉት ሌላው ይብሳል። ወንዶች ሲባሉ ዘዴያቸው ሁሉ እንደየመልካቸው የተለያየ ነው። ሁሉም ደግሞ ከዚያችው ከእርሷ ገንዘብ ትንሽ ለመቆንጠር እንጂ ሰባራ ሽልንግ ቤሳ ቤስቲን አይወጣቸውም። እርሷ ደግሞ በወንዶች ነገር አትቀጣም። ሁለተኛ አይለምደኝም ብላ ትፎክርና መልሳ ትዘፈቅበታለች። ሁሉን ትታ እርግፍ አድርጋ ትንሽ ቀን ደህና ትሰነባብትና እንደ ቡና ሱስ በዓይኗ ላይ ውል ሲልባት ከአንዱ ጋር ፍቅር ትጀምራለች። ሰው ያገኘች መስሎአት እላይ ታች ስትል ሰው ያለችው የበግ ለምድ የለበሰ ተኩላ ሆኖ ታገኘዋለች። የዛሬ ዘመን ወንድ የሴት ገንዘብ ሲያይ ሣምባ እንዳየች ድመት ዓይኑን ያጉረጠርጣል። ገንዘብ ደግሞ ፍቅር የማይገዛላት መሆኑን ተረድታለች። ሰሞኑን ሁሉን እርግፍ አድርጋ ትታ ሰብሰብ ብላ ቁጭ ብላለች።

ውቢት መንገሻ ዛሬ ያለ ወትሮዋ ጤንነት አይሰማትም። ይህን አመመኝ የምትለው የላትም። ግን ደግሞ ጤንነት አልተሰማትም። ምንም አልጎደላትም። ግን ምቾት የላትም። መኝታ ቤቷ ውስጥ ሆና ብስክስክ እያደረጋት ታፋሽካለች። ሰዓቷን አየች። ከምሽቱ 3:00 ሆኗል። ወደ ቡና ቤት ብቅ ማለት ነበረባት ግን እርሱም አስጠላት። ዙሪያ ገባውን ቃኘት አድርጋ አየች። የጎደለ ምንም ነገር የለም። በመኝታ ቤቷ ውስጥ በመልክ በመልኩ የተደረደሩትን ምርጥ ዕቃዎች አንድ በአንድ ተመለከተች። ዙፋን የመሰለውን አልጋዋን፣ በኮመዲናዋ ውስጥ የታጨቁትን ህምራዊ የብር ኖቶች አሰበች። ግን ከልቧ አልደረሰም። ዕድሜዋን ሙሉ ያጠራቀመችውን ገንዘብና ንብረት ለአፍታ በሃሳቧ ቆጠረችው። በዚያች ምሽት ቁብ የሚሰጣት ነገር አልሆነም። ቁም ነገር የሌለው እርባና ቢስ መስሎ ተሰማት። ይልቁንም አስጠላት . . . ለዚያች አፍታ እርሷ ብቻዋን በምድር ላይ ያለች አንዲት ብቸኛ ፍጡር አድርጋ ራሷን ቆጠረች። በግራ መጋባት ስሜት በመኝታ ቤቷ ውስጥ ተንጎራደደች። ዘጭ ያለው ልቧ ግን ቀና አላለም። አብሯት አልተንጎራደደም። በክፍሏ ውስጥ ወዲህ ወዲያ ተንሸራሸረች። ሃሳቧ ግን አብሯት አልተንሸራሸረም።

"ምን ሆኛለሁ?" ስትል ራሷን ጠየቀች። መልስ አላገኘችለትም። "ለምን ይሆን?" ስትል ደግማ ራሷን መልሳ ጠየቀች። መልስ የለም። የአዕምሮዋን ጓዳ መላልሳ ፈተሸች። መልስ የሚሆን ነገር አልመጣላትም። አዘቅት ውስጥ የገባ ያህል የዛለ ልቧን ሞቅ የሚያደርግ አንዳች ነገር በልቦናዋ ውስጥ የለም። ምን እንደሆነ ደግሞ በውል አላወቀችውም።

"ምን ሆኛለሁ?" ስትል ደግማ ራሷን ጠየቀች።

"ሴት ልጅ ብቻዋን ስትሆን ብስክስክ እያደረገ ያማታል" የሚል አንዳች የሹክሹክታ ድምፅ ከአዕምሮዋ ጓዳ አቃጨለባት።

"ወንዶች ቢሆኑ . .?" ስትል ከሰው ጋር የምታወራ ይመስል ለራሷ አጉረመረመች።

ወንዶችስ ብቻቸውን ሲሆኑ ምስኪን ይሆናሉ። ሲብስባቸውም ይደድባሉ።" ሲል አንሾካሾከባት ያው ድምፅ መልሶ። ደግማ ራሷን ሌላ ጥያቄ መጠየቅ አልፈለገችም። አልፈቀደችም። ከአዕምሮዋ ጓዳ ከሚነተርካት ድምፅ ጋርም መመላለስ አላሰኛትም። ልታስበው፣ ልታሰላስለው የማትፈልገውን የልቧን ቁስል እንዳይጎጉጣትም ፈራች።

እንደዋዛ ራመድ ራመድ ብላ በመኝታ ክፍሏ ጠርዝ ላይ ጥጉን ይዞ በተቀመጠው የመልበሻ መስታወት ፊት ለፊት ቆመች። ለስንት ዓመት በዚያ እንዳልነበረ ያህል ልብ ብላ ተመለከተችው። ጌጠኛ መስታወት ነው። ያምራል። በሞዛይክ የተለበጠው የመስታወቱ ፍሬም ያንፀባርቃል። አንፀባራቂ ውበቱ ወለል ብሎ ታያት። ያምራል። ከመስታወቱ መሳቢያ ላይ የተደረደሩትን የሽቶና የቅባቶች ዓይነት፣ አደራደርና የብልቃጦቹን ቀለማት ልብ ብላ አስተዋለች። ያምራል። በሽቶ ብልቃጦችና በቅባት ፕላስቲኮቹ ላይ የተለጠፉትን የንግድ ምልክቶች ፀጉራቸው ዠርገግ ያለ ዘንፋላ ኮረዳዎችን ምስል አንድ በአንድ ተመለከተች። ያምራሉ። "ልጅነት ደጉ እንደዋዛ ጥሎ ሳያልፍ ያሳምራል" አለችና ለራሷ የመናገር ያህል አጉተመተመች።

ዓይኗ እየተንከራተተ ሄዶ የሽቶ ብልቃጦቹን አልፎ፣ የፀጉር ቅባቶቹን የሻምፑና የፓውደር ድርድር አልፎ ከነፓኮው ከተቀመጠ After-shave ላይ ሲደርስ ቀጥ አለ። ከዚያ ፖኮ ጀርባ ያለውን ታሪክ ማስታወስ አልፈለገችም። ከፓኮውም በስተጀርባ ስላለው ሰው ማሰብ አልፈቀደችም። ደህና የጠገገውን የልቧን ቁስል መጎርጎር መስሎ ተሰማት። ዓይኖቿ ግን በፖኮው ላይ የተሰካ ይመስል አልንቀሳቀስ ብሎ አሻፈረኝ አለ። ልብ ብላ ተመለከተችው። "Old Spice" የሚል ጽሁፍ በአንዲት የመርከብ ስዕል ስር ተጽፎአል። የፖኮው ጠረንና ሽታ ታወሳት። ያሸተተችውን ያህል የአንድ ሰው ጠረንና መዓዛ አፍንጫዋን አወደው። ልታስታውሰው የማትፈልገውን የአንድ ሰው ቁመና ወደ አይነ-ልቦናዋ ብቅ አድርጎ አሳያት። ለዚያች አፍታ ፓኮውን ሳይሆን ከፓኮው በስተጀርባ ያለው ሰው ውልል ብሎ ታያት። ያንን ሰው ፊት ለፊት ያገኘችው መሰላት በፓኮው ላይ አፈጠጠችበት።

"ወንድ ልጅ እንዴት ይታመናል?" ስትል ራሷን ጠየቀች።

"ታማኝነት ከራስ ይጀምራል"። ሲል በአእምሮዋ ጓዳ ውስጥ የተሸነጎረው ድምጽ አንሾካሾከባት። ከህሊናዋ ጋር መሟገት አልፈለገችም። እንደማትረታው ታውቃለች። ፍዝዝ ትክዝ ብላ ፓኮው ላይ ያለችውን ትንሽዬ መርከብ ተመለከተቻት። ካፒቴን የሌላት፣ መርከበኞቿ ጥለዋት የሄዱ የምታሳዝብ መርከብ! ህይወት ያለው ፍጡር የሌለባት ከነጭነቷ፣ ከነንብረቷ፣ መሕልቋን ከጣለችበት ባሕር ተገትራ የቀረች መስላ ታየቻት። ለአፍታ የራሷ ህይወት ታሰባትና ዝግንን አላት። . . . የሕይወት ውጣ ውረድ አንፏቆ፣ እድሜ ገፍቶ፣ አንደርድሮ በአንድ ሕይወት ጠርዝ ላይ ያቆማት ሕይወት የሌለባት ትልቂቱ መርከብ ራሷ እንደሆነች ጥርት ብሎ ገባት። በህሊናዋ ጓዳ ውስጥ የተወሸቀው ድምጽ ደግሞ አረጋገጠላት። አንዳች የሆነ የንዝረት ስሜት ሁለመናዋን ወረራት።

እንደምንም ብላ አይኗን ከፓኮው ላይ አንስታ ቀና አለችና በመስታወቱ ላይ የተለጣጠፉ የአበባ ስዕሎችን ትኩር ብላ ተመለከተች። ያምራሉ። የመስታወቱን ፍሬም ደግማ ተመለከተች። ያምራል። በረጅሙ ተነፈሰችና ሌላ ነገር ለማየት የፈለገች ይመስል መስታወቱን ትኩር አድርጋ አንቅራ ተመለከተች። ኩልል ውልል ብሎ ያንፀባርቃል። በመስታወቱ ውስጥ ጎልቶ የሚታይ ምስል ላይ አተኮረች። ትኩር ብላ አየችው። በመስታወቱ ውስጥ ያለው ምስልም ትኩር ብሎ አያት። እንደገና ትክር ብላ መልሳ አየችው። የራሷ ነው። ምንም አዲስ ነገር የለውም። ከቆመችበት ነቅነቅ አለችና ዘንበል ብላ ቆመች። በመስታወቱ ውስጥ የምታየው ምስልም ነቅነቅ አለና እርሷ እንዳደረገችው ዘንበል ቅዝዝ ብሎ አፈጠጠባት።

የምታየው የራሷን ምስል ነው። ትክክል! ግን በመስታወቱ ውስጥ የምታያት ሴት አታምርም። አታንፀባርቅም። ወልውል ብላ አትማርክም። መዓዛዋና ውበቷ አይስብም። ተመናጨረችና ፈንጠር ብላ ቆመች። በመስታወቱ ውስጥም ያለው ምስል ገፍተርተር ደብለል አለና ተገትሮ አያት።

በረጅሙ ተነፈሰችና መስታወቱን ትክር ብላ ተመለከተች። በትክክል የራሷ ምስል ነው።

"ውቢት መንገሻ!" አለችና ራሷን አወዛወዘች። ለራሷ አዘነችለት። በሐዘኔታ ፍዝዝ ቅዝዝ ትክት ብላ የምታያትን "ውቢት መንገሻ" መልሳ አየቻት። በመስታወቱ ውስጥ የምታያት "ውቢት መንገሻ" አታምርም። አታንፀባርቅም። ውበቷ አይማርክም። ቀስ ብላ ወደ መስታወቱ ተጠግታ ልብ ብላ አየቻት። ያው ነች። የሚያምር ነገር የላትም። አንገቷን ወደ ግራና ወደ ቀኝ ዘንበል ቀለስ አድርጋ አንገቷ ስር ጆሮዎቿ ግድም የተሸበሸበውን የፊቷን ቆዳ ተመለከተች። መሸብሸቡ፣ መጨማደዱ በደንብ ያስታውቃል። "ዕድሜ የጠገብሽ አሮጊት" ተብሎ የተፃፈባት መሰላት። ጆሮ ግንዷ ስር ቆዳዋ

ጭርምት ብሎ ፈቷ ሳንባ ይመስላል። ፊንጠር ብላ ወደ ኋላዋ ተመለሰችና በረጅሙ ቁመናዋን ልብ አለች። ቁመናዋም ቢሆን አላማራትም። ቀሚሷን ወደፊት ውጥር አድርጋ ቀጥ ብላ ቆመችና ጀርባዋን ለመስታወቱ ሰጥታ እንደምንም ተጠማዛ በትከሻዋ አናት ወደ መስታወቱ አንጋጠጠች። ከትከሻዋ እስከ ቁርጭምጭሚቷ ድረስ በስጋ የተሞላ የተዘረፈጠ ገላ ታያት።

"እንዳማሩ መሞት የለ! . . . ውቢት መንገሻ ዘርፋጤ ሆንሽ!" አለቻት በሀዘኔታ ድምፅ! የእግሯ ቅጥነት የሆዷ ወደፊት መግፋት፣ የመቀመጫዋ መተለቅ ከሁሉም ደግሞ ድብልብል ዙሪያ-ሆድ መሆኗ አስጠላት።

"በቃ አርጅተሻል። መርከበኞችሽ ጥለውሽ የሄዱ ጠያቂ የሌለሽ በህይወት ባህር ጠርዝ የቆምሽ ትልቂቱ መርከብ አንቺ ነሽ።" አላት አንድ ድምፅ ከህሊናዋ ጓዳ! ልትሰማው አልፈለገችም። ልትቀበለውም አልፈለገችም።

በረጅሙ ተነፈሰችና የጊዜውን መሮጥ ለአፍታ አሰበችው። መልሳም "ውቢት መንገሻ" አለች። እንደመቆጨት ብላ። በመስታወቱ ውስጥ ያለችው "ውቢት መንገሻ" ግን አትሰማትም። የድሮ ውበቷን እንደፈካ ጽጌረዳ የምታምረዋን አንፀባራቂዋን ውቢት መንገሻን አሰበች። በጣም ርቃለች። ጥርት ብላ አትታይም። ጊዜው በጣም ይሮጣል። ይፈጥናል። . . . በልጅነት መልኳና ውበቷ ምትክ በዕድሜዋ ያጠራቀመችውን ሀብትና ንብረት ከአሁኗ "ውቢት መንገሻ" ጋር አዳምራ ልታስባት ሞከረች። ግን ያን የድሮ መልኳን የያኔውን ውበቷን አያክልም። አጨንቁራ ተመለከተቻት። የለም ጨርሶ አይስተካከሉም።

ከእርሷ ይልቅ ያጠራቀመችው ሀብትና ንብረት ሆጨጭ ብሎ ጎልቶ ይታያል። እርሷነቷ ብዙም አትታይም። ብዙ ብር ሐብትና ንብረት ያላት "ውቢት መንገሻ" በዚያ ሁሉ ሀብት መሃል ትንሽ ሆና ተሰማቻት። በመስታወቱ ውስጥ ልብ ብላ አየቻት። እየሟሟች፣ እየደከመች፣ እያለቀች፣ እየተጨማደደች የምትሄድ ትንሽት "ውቢት መንገሻ" ፍንትው ብላ ታየቻት። እየሟሟች - እየሟሸሸች - እያነሰች ስፍራዋን ስትለቅ ታሰበቻት። ዕድሜዋን ሙሉ የደከመችበት ወርቅና ብር፣ ሀብትና ንብረት ለብቻው ሆጨጭ ብሎ ማንም እጁን ሲዘረጋበት ተሰማት። በእጅጉ ለራሷ አዘነችላት። ደግሞም ተበሳጨች። አጉረመረመች። ልጅ የላትም ይወርሳታል አይባልም። የቅርብ ዘመድ የለ አይጠቀምበትም። ስንት የደከመችበትን ሀብት ማንም ሲቀራመተው ታሰባትና ዓይኖቿ እንባ አቀረዘዙ። ከፉኛ ምሬት ልቧን ሸነቆጣት። ተበሳጨች። ስሜቷ ተደባላለቀባት። . . . "ውቢት መንገሻ" አለች ራሷን መልሳ መላልሳ በሀዘኔታ ስሜት! በመካከሉ የሆነ የጫጫታና የውካታ ድምፅ ከቡና ቤቱ አቅጣጫ የሰማች መሰላትና አይኖቿን ከመስታወቱ ላይ ነቅላ ጆሮዎቿን አቆመች። መጀመሪያ የጫጫታ ድምፅ ተከትሎም የኡኡታ ድምፅ ስትሰማ ፈጥና ወደ ቡና ቤቱ አቀናች።

ቡና ቤቱ ውስጥ ጥቂት ሰዎች ጥግ ይዘው ጥቂቶቹ ደግሞ ባንኮኒ ላይ ተደርድረው ይጠጣሉ። ረዘም ሰልከክ ያለ አንድ ልጅ-እግር ሰው ይለፋደዳል። ይረብሻል። ካሸር ባንኮኒ ውስጥ የተቀመጠችውን ለምለም ኩርኩርን ካልሳምኩሽ እያለ ይጎትታል። ሰውዬው ለምለም ኩርኩርን አንገቷን አንቆ ፀጉሯን ጨምድዶ ይዟል። እርሷ ደግሞ የአንገቱን ኮሌታ አንቃ ይዛ ትጮሃለች።

"ምንድነው?" አለች ውቢት። በቁጣና በንዴት ተሞልታ።

"ሰክሮ ነው የሚያስቸግረን" አለች ደብሪቱ ትንፋሿ ቁርጥ ቁርጥ እያለ።

ውቢት ከትንሽ ደቂቃ በፊት በመስታወቱ ፊት ለፊት ቆማ በዓይነ-ሕሊናዋ የተመለከተችው ትርዒት ብልጭ አለባት። እያነሰች፣ እየሟሸሸች፣ እየተጨማደደች አንሳ በንብረቷ ላይ ማንም እጁን ሲዘረጋበት ታሰባት። በካሸር ባንኮኒ ላይ ከካሸሯ ጋር እየተናነቀ ያለው ሰካራም የዚያ ትርዒት ዕውን መሆን ጅማሬ መስሎ ተሰማት። በልቧ ውስጥ አንዳች የቁጣ እሳት ጫረባት። ደመኛዋን ፊት ለፊት ያገኘችው መሰላት።

"የማነው ጨምላቃ ይሄ! ለፍዳዳ ባለጌ! ስትል አንቧረቀችበት። ይህቺ ናት ውቢት መንገሻ ገና . . ." አለችና መናገር የፈለገችውን ለመጨረስ እንዳልፈለገች ያህል ዝም ብላ ቆየችና ወደ ውጭ ራመድ ራመድ ብላ በሁለት እጆቿ ወገቧን ይዛ እየተውረገረገች:-

"ደጉ . . . አንተ ደጉ" ስትል በቁጣ ድምፅ ተጣራች። አንድ ፈርጠም ደልደል ያለ ሰው ከዋናው መግቢያ በር ገደማ ፈጠን ብሎ ወደ እርሷ መጣ።

"አንተ ከርፋፋ እጁን ጠምዝዞ ገንዘቡን ዘርግፎ ይዞ እስከሚሄድ ነው የምትጠብቀው?" ስትል እንደነጎድጓድ ጮኸችበት። ለምለምና ሰካራሙ ሰውዬ እንደተናነቁ ናቸው። ይታገላሉ። ጠጪው የእነርሱን ትንቅንቅ እያየ ይስቃል፣ ያወካል።

ወ/ሮ ውቢት ጠርተውት የመጣው ደጉ ወደ ሰካራሙ ጠጋ አለና ጥርሱን ነከሰ:-

"ልቀቃት" አለው።

"እ-ወ-ዳ-ታ-ለ-ሁ።" ሲል ስካር ባኮላተፈው አንደበት ተለፋደደ።

"ልቀቃት ነው የምልህ?" ሲል ጎተት አደረገው።

"እ-ወ-ዳ-ታ-ለ-ሁ። ምን አባክ . . . አገባህ?" ሲል መልሶ ተለፋደደ ሰካራሙ።

ወገቧን እንደያዘች በቁጣ ተሞልታ የቆመችው ውቢት መንገሻ ከፊት ለፊት ቆማ ከለምለም ኩርኩር ጋር እየተናነቀ ያለውን ሰካራም ሳይሆን በመስታወቱ ፊት ለፊት ቆማ የታያትን ትርዒት እያሰላሰለች በጆሮዋ ሲያንሾካሹክ የነበረውን ደመኛዋን ያገኘች ያህል በቁጣና በበቀል ስሜት "አትለውም እንዴ?" ስትል በደጉ ላይ ጮኸችበት።

የእመቤቱ ጩኸት ያስደነገጠው ደጉ ሆዬ ስካር የሚያለፋድደውን ሰውዬ ትንሽ ለአመል ያህል ወደ ራሱ ሳብ ጎተት አደረገውና ፋታም ሳይሰጠው በአካፋ እጁ ጆሮ ግንዱ ላይ በቡጢ መረገበት። ደገመና በቃሪያ ጥፊ አይነስቡን አወጣለት። አንድ ሁለቴ በቡጢ ነረተውና ማጅራቱን ይዞ እንጠልጥሎ አውጥቶ ከበረንዳው ደረጃ ላይ ፈጠፈጠው።

ውቢት መንገሻ እንጀቷ ራሰ። በድል አድራጊነት ስሜት ወደ መኝታ ቤቷ ተመለሰችና አልጋዋ ላይ ወጥታ ቁጢጥ ብላ ተቀመጠች። የመልበሻ መስታወቷን፣ የዚያችን After shave ፓኮ ላለማየት የፈለገች ይመስል ዓይኖቿን በሩ ላይ ተከላ ብስክስክ ትክዝ ብላ ቁጭ አለች። ሃሳቧ ብትንትን ብሏል። ብዙም ሳትቆይ የመኝታ ቤቷ በር ተንኳኳ። ማነው ለማለት እንኳ ፋታ ሳታገኝ በሯን ብርግድ አድርጋ ደብሪቱ ዘላ ገባች።

"እትዬ! እትዬ! ሰውዬው ሊሞት ነው" አለች ትንፋሿ ቁርጥ ቁርጥ እያለ።

"የትኛው ሰውዬ?" አለች ውቢት መንገሻ። አንዳች የድንጋጤና የፍርሃት ስሜት ሁለመናዋን ወረራት። ደብሪቱ ግን እርሷ የምትጠይቃትን እንደደመመለስ ፋንታ

"እትዬ! አይተርፍም። አይተርፍም። . . . ውይ! ውይ – ውይ ምን ይሻለኛል? የት አባቴ ልግባ?" እያለች በሩ ላይ ተለጥፋ ስፍስፍ እያለች ትጮሃለች።

ወ/ሮ ውቢት የደብሪቱ ሁኔታና ለቅሶ አናዷታል። አስደንግጧታል። ድሮም ብዙ አትወዳትም። ወሬኛ ናት የሰው ወሬኛ! . . . ቅድምም እየጮኸች ስታጋግል የነበረችው እርሷ ነበረች። አሁንም ሰውዬው ሊሞት ነው እያለች የምትጮኸውም እርሷው ነች።

"ምን አባቷ ሆናለች ይህቺ? . . . የትኛው ሰውዬ እኮ ነው የምልሽ? አለች ውቢት መንገሻ በቁጣና በንዴት የማይቀርላትን መርዶ ለመስማት የቸኮለች ይመስል!

"አሁን ደጉን አስወጣው ያልሽው ሰውዬ" አለች ደብሪቱ እየነፈረቀች።

"ፍንችር ይበላ!" አለች። ውቢት መንገሻ። ለማለት ያህል ለአፏ አለችው እንጂ ከልቧ አልነበረም። አስደንግጧታል። ከተቀመጠችበት ተነስታ ወደ ቡና ቤቱ ተንደረደረች።

ቡና ቤቱ ውስጥ ሰው የለም። በረንዳው ላይ ሰው ይተራመሳል። ከበረንዳው ደረጃ ስር አንድ ሰው ጭብጥብጥ ብሎ ተደፍቷል። ከአፍንጫውና ከአፉ ደም ይፈሳል። ከጆሮ ግንዱ ከፍ ብሎ ደግሞ ደም የቀላቀለ ፈሳሽ ፍጭጭ እያለ ወርዶ ፀጉሩን እርሶታል። ራሱን አያውቅም። ነፍሱ አልወጣችም። የሚተርፍም አይመስልም። ውቢት መንገሻ ሰውዬውን ተመለከተችና ቀና ብላ የተሰበሰበውን ወሬ አዳማቂ ደግሞ ቃኘት አደረገች። ብዙ ሰው ተሰብስቦ ጉድ ጉድ ይላል። ይህ ሰው እዚህ ቢሞት የሚመጣባትን ጣጣ አሰበች። የምትለው ሁሉ ጠፋባት። ምን ሆነ እንዳትል ከደቂቃዎች በፊት የሆነውን ታውቃለች።

ማን መታው እንዳትል በአይኗ ፊት ደጉ የሰራውን አይታለች። አንደበቷ ተዘጋ። ከንፈሮቿ ደረቁ። ምላሷ እስርስር አለ።

ደጉን በአይኗ ፈለገች። ግራ ገብቶት ፈዞ ቆሟል። እንደምንም የሞት ሞቷን ተበራታችና ወደ ውስጥ እንዲያስገባው ለደጉ በምልክት ነገረችው። ነፍሱ ይውጣ አይውጣ ያልለየለትን ሰውዬ ደጉ ሆዬ እፍስፍስ አደረገና ይዞት ወደ ውስጥ ሮጠ።

ሰውየው ዝልፍልፍ ብሎ ሬሣ ሆኗል። በረንዳው ላይ የወደቀበት ሥፍራ ደም በቀላቀለ ትውከት ተጨማልቋል። ደብሪቱ ከወዲያ ወዲህ እየተራወጠች ትጮሃለች። ለምለም ኩርኩር እዚያው ካሸር ባንኮኒ ውስጥ ቁንን ብላ ቁጭ ብላ ተቀምጣለች። ደጉ ሆዬ ግራ በተጋባ ስሜት ሰውዬውን እንጠልጥሎ ቀስ ብሎ ከጓሮ ውቢት መኝታ ቤት በረንዳ ላይ አስደግፎት ወደ ስፍራው ተመለሰ።

"ኧረ! ወደ አንዱ ክፍል አስገቡት" አለች ውቢት መንገሻ።

"ሁሉም ተይዟል" ስትል መለሰች ደብሪቱ ችኩል ብላ።

"እናንተ ክፍል አስተኙት"

"እሰለፍ ዘግታ ተኝታለች"

ዘግታ ተኝታለች ማለት ምን ማለት እንደሆነ ውቢት ገብቷታል። ትንሽ ለራሷ አጉተመተመችና ድንገት ከአፏ የወጣ ያህል "እኔ ክፍል አስገቡት" አለች። ቶሎ ብሎ ዞር ማድረጉ ደህና ዘዴ መሆኑን አውቃ። ደጉ ሆዬ! እንጠልጥሎ ወስዶ ከሚያምረው የወ/ሮ ውቢት ሶፋ ላይ አጋድሞት ተመለሰ።

ውቢት መንገሻ በግራ መጋባት ስሜት ዝም ብላ ፈዛ ቆማለች። ይህ ሰውዬ ቢሞት መኝታ ቤቷ ውስጥ ሊሞት? የት ታደርገዋለች? ምንስ ይባላል? የሚመጣባት ደፋ ወለል ብሎ ታያት። ደግሞም ክፍሎቹ ሁሉ ተይዘዋል። የሴቶቹን መኝታ ቤት እሰለፍ ወዳጇን ይዛ በጊዜ ዘግታ ተኝታለች። ራቅ አድርጋ አትጥለው ነገር ሰው ሁሉ አይቷል።

ደብሪቱ አሁንም ትጮሃለች። ውቢት ልብ ብላ አየቻትና መቆጣቱም መናደዱም ምንም ጥቅም እንደሌለው ተረድታ:–

"ይልቅ ሂጂና ደሙን በፎጣ ጠራርጊለትና እንደሚሆን አድርገሽ አስተኚው" ብላት በዘዴ ከቡና ቤቱ አስወጣቻት። ውቢት የሚቀጥለውን ክፉ እያሰላሰለች ትክዝ ብላ ቀረች። ዛሬ ያለ ነገሩ አልቀፈፋትም። "ውቢት መንገሻ" ቡና ቤቷ ውስጥ ሰው አስገድላ መኝታ ቤቷ ውስጥ አልጋዋ ስር አስቀበረች ተብሎ ሲወራባት ተሰማት። ውቢት መንገሻ ሰው አስገደለች ተብሎ ወህኒ ስትወርድ ታየቻት። ከትንሽ ጊዜ በፊት ያየችው ትርዒት ዕውን መሆኑ ታሰባትና ዘገነናት። ውቢት እየቀፈፋትና እየከበዳት ወደ መኝታ ቤቷ ሄደች። ሳሎንም መኝታ ቤትም አድርጋ የምትጠቀምበት ክፍሏ ጠረን ተለውጧል። የካልሲ ግማት፣ የመጠጥና የገላ ቅርናት ሽታ ተቀያይጦ አፍንጫ ይቆርጣል። ደጉ ሆዬ ሶፋው ላይ ያጋደመውን ሰውዬ ደብሪቱ አመቻችታ ከውቢት አልጋ ጠርዝ ላይ ልክ እንደሞተ ሰው አስተካክላ፣

በደረቱ ደፍታ፣ በትራሱ ላይ ፎጣ ደርባበት አጋድማዋለች። ውቢት አልጋዋ ላይ የተዘረጋውን ሰው ስትመለከት ክፉኛ ቀፈፋት። የደብሪቱም ድፍረት እናደዳት። ሞት በአልጋዋ ላይ ተንሰራፍቶ የተኛ መስሎ ተሰማትና አልጋዋ ላይ የተጋደመውን ሰውዬ ፈራችው። በዚህ ሁኔታ መፍራቷም መቆጣቷም ነገር ማበላሸት ስለመሰላት ዋጥ አደረገችው።

እንደምንም ብላ ተጠግታ ሰውዬውን ተመለከተችው። ነፍሱ አለች። ከትራሱ ስር የተደረገለት ፎጣ በደም ርሷል። እንደከበዳት ጋቢዋን ተከናንባ የሸቶ ብልቃጥ አውጥታ ተቀባባችና ሶፋው ላይ ተቀመጠች። የተለያየ የሃሳብ ዘባተሎ ተጫጫናት። የሚያስፈራና የሚያስጨንቅ ሃሳብ አንድ በአንድ ወደ እሷ ይመጣ ጀመር። ከዚህ ሰው ሞት የሚደርስባትን ክፉ ሁሉ እያሰላሰለች ዝም ትክዝ ቅዝዝ ብላ አይኖቿን በሰውዬው ላይ ተክላ ቆየች። . . . አሁን እዚህ አልጋዋ ላይ እንዳለ ቢሞት ምን ይባላል? ማን ገደለው ሊባል ነው? ከሰዎች ተጣልቶ ቡና ቤት ውስጥ ደብድበው ጥለውት አይባል ነገር በሰው ፊት ቆማ አሽከሯን ስታስደበድበው አገር አይቷል! ደግሞ ያቺ ለፍላፊ ደብሬ አለች ሳትጠየቅ የምታወራ። በወጥመድ እንደተያዘች ቆቅ ከወዲያ ወዲህ በሃሳብ ተመላለሰች። . . . ደግሞስ ለምን አስመታችው? ምን አጠፋ? በራሷ አእምሮ በፈጠረችው ብስጭት ይህን ሰው ማስደብደቧ የህሊና ፀፀት በውስጧ ለኮሰባት። ክፉኛ ቆጠቆጣት። ህሊናዋ ተቀየማት። ይህን እያሰላሰለች ስትተክዝ ሌሊቱ ተጋመሰ። የሙዚቃም ሆነ የሰው ድምፅ ብዙ አይሰማም። እርጭ ብሏል።

ድንገት ከሰውየው ግድም የሆነ ድምፅ የሰማች መሰላትና ፈጥና ወደ ሰውየው ቀረበችና ተመለከተችው። አፍንጫው ሰልከክ ያለ ልጅ እግር ቢጤ ነው። ትክ ብላ ተመለከተችውና "ይሄኔ የእንዲቷ ባል ይሆናል" ብላ አሰበች። በጣቱ ላይ የጋብቻ ቀለበት የለውም። አልጋዋ ላይ ወንድ ያደረበት ጊዜ ርቀት ታወሳትና የዚህ ሎጋ ልጅ እግር አልጋዋ ላይ ሊሞት መሆኑ ደግሞ ቆጫት። በደህናው ቢሆን ሊፈጠር የሚችለው ሁሉ ለአፍታ በአእምሮዋ ጓዳ ውስጥ ውልብ አለባት። ደግሞም በሞት አፋፍ ላይ ስላለ ሰው ይህን ማሰቡ አሳፈራት። ሌላ ነገር ለማሰብ አልቻለችም። እንደቆመች ሰውዬውን ቁልቁል ተመለከተችው። ዝርግትግት ብሎ ተኝቷል። አተነፋፈሱ ከላይ ከላይ ቅትት ቅትት ይበል እንጂ ደህና ነው። ይሞት ይሆናል የሚለው ስጋት አሁን ከአዕምሮዋ እየወጣ ነው። ደስ አላት። የከበዳት የስጋት ሸክም ወረደላት። ያጠላበት የሞት ጥላ ሥፍራውን ለቀቀ። ጋቢዋን እንደለበሰች በእንደኛው ጥግ አልጋው ላይ ወጥታ ቁጢጥ ኩርምት ብላ ትራስ ተደግፋ ተቀመጠች። የሰውዬው የጠነባ የካልሲ ግማት፣ የመጠጥ ሽታና የገላ ቅርናት አፍንጫዋን ቆርጦ ሊጥለው ደርሷል። እልፎ እልፎ ሽቶ እያወጣች እጇንና አፍንጫዋን ትቀባባለች። ምንም አልረዳትም። ደግሞ የወንድ ጠረን፣ የወንድ ሽታ መሆኑን ወደደችው።

ሰውዬው ድብን አድርጎ እንቅልፍ ወስዶታል። ትንፋሹም ሆነ አስተኛኘቱ ሁኔታው ለሞት የሚያደርሰው አይመስልም። ውቢት መንገሻ ግን በተመሰቃቀለ ስሜት ዓይኗን በሰውዬው ላይ ተክላ በሃሳብ ፈረስ ጋልባ አንዱ ዘንድ ደርሳ ትመለሳለች። ሳይታወቃት ስለሰውዬው ማንነት የተለያዩ ሃሳቦች ወደ ልቧ ይመጣና ይኮረኩራታል። ምንም ያላደረጋት ይህን ሰው ማስደብደቧ የበለጠ ቆጫት። የምሽቱን ሁኔታ አንድ በአንድ መልሳ መላልሳ አሰበችው። በመስታወቱ ውስጥ ያየችው የራሷ ምስልና በመሳቢያው ላይ የተቀመጠው "Old Spice" የሺም ቅባት ትዝ አላት። በዚያ የቅባት ፓኮ ላይ የተመለከተችው የመርከብ ስዕል ወለል ብላ ታየቻት። ሰው ዝር የማይልባት "ትልቂቱ መርከብ" እርሷ መሆኗ ታሰባትና በጣም አዘነች።

ሁኔታውን ደጋግማ ስታስበው በራሷ ብስጭትና ንዴት ይህን ምስኪን ሰው ማስደብደቧ ነውር ስራ መሆኑ በጣም ገባት። "ወንድ ልጅ ጡር አለው" አለች ለራሷ! . . . ይህንኑ ከወዲያ ወዲህ ስታወጣ ስታወርድ ሰውዬው አቃሰተና ተወራጭቶ በጎኑ ተገላብጦ ጀርባውን አዙሮ ተኛ። ትንሽ ቆይቶ እንደማቃሰትም እንደመቃዠትም እያደረገው ከጎኑ አንዳች ነገር እንደሚፈልግ ሰው ቀኝ እጁን ዘርግቶ ዙሪያውን ይዳብስ ጀመር። ደግሞ ትንሽ ይቆይና በጨለማ ዕቃ እንደሚፈልግ ሰው በእጁ እየዳበሰ አንዳች ነገር ይፈልጋል።

ውቢት ካለችበት ነቅንቅ ወይም ፈቀቅ ሳትል ትንፋሿን ዋጥ፣ ድምጿን ጥፍት አድርጋ የሚሆነውን ትከታተላለች። ምናልባት ለምለም ኩርኩርን ይሆን ከጎኑ የሚፈልገው? . . . ሚስት ትኖረው ይሆን? እርሷን ይሆን ከጎኑ እየፈለገ ያለው? የሚል ሃሳብ መጣባት። ግን መጨረሻውን ለማወቅ ፈልጋ እየሆነ ያለውን ለማየት ወሰነች።

ወዲያው ሰውዬው አቃሰተና ተወራጭቶ በሌላኛው ጎኑ ተገልብጦ ፊቱን ወደ እርሷ አዙሮ ተኛ። አሁን ፊቱ በደንብ ይታያታል። አይኑን ግን አልገለጠም። ከቅንድቡ ከፍ ብሎ የተገሸለጠ ቁስልና ደም ፊቱን ሸፍኖታል። አሁን ከቅድሙ ወደ እርሷ በመጠጋቱ ትንሽ የፍርሃት ስሜት አሳደረባት። ፊት ለፊት ስታየው ደግሞ ወንድነቱ መልከ መልካምነቱ ሰልከክ ያለ ፊቱ ሴትነቷን ኮረኮራት። ይህን የመሰለ ሎጋ ከለምለም ኩርኩር ዘንድ ምን ይሰራል? ስትል ቅናት ቢጤ በልቧ ብልጭ አለባት። በዚህ መሃል ሰውዬው እጁን ዘረጋና ዙሪያውን ዳበስ ዳበስ አደረገ። አሁን እጁ ውቢት ጋ ይደርሳል። ፈቀቅ ለማለትም ፈለገችና እንዳትንቀሳቀሽ የተባለች ይመስል ሳትንቀሳቀስ ፀጥ ብላ የሚያደርገውን መከታተል ያዘች። ዓይኖቹ እንደተከደኑ ናቸው። ለትንሽ ጊዜ ድምፁ ጥፍት ብሎ ይተኛና ደግሞ መወራጨት ይጀምራል። በእጆቹ ዙሪያውን ይዳብሳል።

በዚህ ሁኔታ ትንሽ ቆየና ሰው አጠገቡ መኖሩን ሊያረጋግጥ የፈለገ ይመስል እንደገና ይዳብስ፣ ይወራጭ ጀመር። አሁን እጁ ውቢት መንገሻ እግሮች ጋ ይደርሳል። ቀስ ብሎ ዳበስ አደረጋት።

ትንፋሿን ውጣ ድምጿን አጥፍታ ዝም አለች። ብሬይል እንደሚያነብ አይነ ስውር በጥንቃቄ እስከ ላይ ድረስ ቀስ ብሎ ዳበሳት። ዳሰሳ

"ስድ አደግ ባለጌው መሆን አለበት" አለች ለራሷ ሁኔታውን ተመልክታ። ወዲህ ደግሞ "ትልቂቱን መርከብ" እየዳሰሰ፣ እየዳበሰ የሚያደንቅ መገኘቱ በልቧ ውስጥ የደስታ ስሜት ፈጠረባት። እጁ በጣም ያተኩሳል። ትኩሳቱን ራሱን አልጠላችውም። እጆቹን በጋቢው ውስጥ አሾልኮ ትምቡክ ትምቡክ የሚለውን ገላዋን ዳሰስ - ዳሰስ - ዳበስ አደረጋት። በጥንቃቄ እንደተቃኘ የክራር ክር መላ አካሏን ነካ ነካ ዳበስ ቆንጠር አደረገው። ዝም አለችው። የመፍቀዷ ምልክት መሆኑን አረጋገጠ። ሁለቱንም እጆቹን በጋቢው ውስጥ አሾልኮ እንደተባዘተ ጥጥ የሚለሰልስ ጭኗን አባበሰ። እንደ አንዳች ነገር የተቆለለ ዳሌዋን በመዳፉ ሙሉ ለመያዝ የፈለገ ይመስል ያዝ ጭብጥ አደረጋት። ትኩሳቷ አንዳች ነገር ነገረው። ድው ድው የሚለው የልቧ ምት ይህንኑ ደገመለት።

በዓይኑ ላይ የተመረገበትን የቡጢ የጥፊ ናዳ ያስታወሰ ይመስል እንደፍርሃትም እንደመጠራጠርም አደረገውና ለአፍታ ፀጥ ዝም ብሎ የተኛ መሰለ። ቀስ ብሎ ወደ አንገቷ ተጠጋና ቀመስ አደረጋት። ጣፈጠችው። ደገማት። ዝም አለችው። አሁንም ያ የወረደበት ቡጢና የጥፊ መዓት ከአሁን አሁን ዳግመኛ እንዳይወርድበት የፈራ ይመስል አንገቷ ስር ተወሽቆ ልጥፍ ብሎ አደፈጠ። "ትልቂቱ መርከብ" ፍም እሳት ያነደዱባት ያህል ከላይ እስከ ታች ግላለች። . . . የደም ስሯ ይገፋተራል። የልቧ ምት ከሩቅ ይሰማል። ዳገት እንደጋለቡት ፈረስ አለክልካለች።

ሰውዬው ድምፁን አጥፍቶ አንገቷ ስር ተለጥፎ አዳመጠ። የደም ስሮቿ ገፍትረው ሊጥሉት ደርሰዋል። አድፍጦ ከቆየ በኋላ አንገቷን በከንፈሮቹ ዳበሳት። ችፍ ብሎ በበቀለው ጢሙ ተሻሸባት። እንደአሞሌ ጨው ላሳት። "ትልቂቱ መርከብ" እያነሰች እየሟሸሸች ድንቢጥ አከለች። ጭብጥ ጭብጥብጥ አደረጋት። ትምቡክ ትምቡክ የሚለውን ለስላሳ ገላዋን ዳብሶ ደባብሶ ቆንጥሮ ቆነጣጥሮ ተመልሶ አንገቷ ስር ተወሽቆ ፀጥ አለ። ሽቶዋ አፍንጫውን አወደው።

"ትልቂቱ መርከቢቱ" ተቀጣጠለች። በራሷ ግለት ነደደች። እንደ እብድ አደረጋት። ነፍሷን ሳተች። የምትሆነውን አጣች። ተቅበዝብዛ መድረሻ ጠፋት። ሰውዬው ግን አንገቷ ስር ተወሽቆ አደፈጠ። መርከቢቱ ነፍሷ ወጣ። ቀለጠች። በስሜት ተፍነከነከች። ክንፍ አወጣች። በረረች። ከነፈች። ወደ ላይ ተምዘገዘገች፣ ተመጠቀች። ሰውዬው አንገቷ ስር ተለጥፎ ድምፁን አጥፍቶ ትንፋሹን ዋጥ አድርጎ ፀጥ ብሎ ማዳመጥ ይዟል። . . . እዚህ ምን እንዳመጣው ትንሽ አሰበ። . . . ማን አምጥቶ እዚህ ጣለው? . . . የምሽት ቆይታውን አሰላሰለ። አራት ኪሎና ካዛንቺስ ማምሸቱ ትዝ አለው።

በጊዜ ጀምሮ አረቄና ጂን መጎንጨቱ ታወሰው። ከምሽቱ አራት ሰዓት ገደማ "ውቢት ፍፍቴ" ጎራ ማለቱን አስታወሰ። የለምለም ኩርኩር መልክና ቁመና ከነባንኮኒዋ በዓይነ ሕሊናው ብቅ አሉበት። . . . ለምለም ኩርኩር ካሸር ባንኮኒው ውስጥ ገብታ ቂጥጥ ኩፍስ ብላ ዓይኖቿን ስታቁለጨልጭ ታየችው። . . . ሲላፋትና ሲጎነትላት በደንብ ታወሰው። . . . እንደነጎድጓድ ጆሮ ግንዱን አጨሆ የተመረገበት ጥፊና ቡጢ በሚገባ ትዝ አለው። . . . አሁን የት ነው ያለው ማለት ነው? . . . እዚህ አልጋ ላይ አብራው ያለችውስ ማናት? ለምለም ኩርኩር ትሆን? ለምለም ኩርኩር ይህን የመሰለ ሽቶና አልጋ ከየት ታመጣለች? . . . እንዴትስ ይህን ልታክል ትችላለች? . . . ሴት ልጅ አልጋ ላይ ስትደርስ ሚጢጢዋ ግዙፍ ትሆናለች የሚባለው እውነት ይሆን? . . . አንገቷ ስር ተወሽቆ ይህን እያሰላሰለ በእጆቹ ትምቡክ ትምቡክ የሚል ገላዋን እየደባበሰ፣ እየተሻሸ ትንሽ አዳመጠ። . . . ይህቺ ሰው ማን ልትሆን ትችላለች? . . . የሸንብራ አፍንጫ የምታክለዋን ለምለም ኩርኩርን ፍለጋ መጥቶ ቋጥኝ ከምታክል ከዚህች ሰው ዘንድ ምን አምጥቶ ጣለው? . . . የኮሎምቦስ ጉዞ አለ ለራሱ። . . . ኮሎምቦስ ህንድን ፍለጋ ጉዞ ጀመረ። ለወራት በውቅያኖስ ላይ ከረመ። ከብዙ እንግልት በኋላ ምድር አየ። ማን እንደሚባል አላወቀውም ነበር። ህንድን ያገኘ መስሎታል። ህንድን ሳይሆን ትልቂቱን ሀብታሚቱንና ሰፊዋን አሜሪካ አገኘ። . . . እርሱንስ እየነረተ አምጥቶ ከዚህ ምቹ አልጋ ላይ አንዳች ከምታክል ሴት ጎን ያደረሰው ጉዞው እንደኮሎምቦስ ጉዞ ይሆን? . . . ለምለም ኩርኩርን ፍለጋ ወጥቶ ወርቅና ብር ተንተርሟ በምታድር እመቤት ላይ ጥሎት ይሆን?

መርከቢቱ መቀጣጠል መንደድ ጀምራለች። እርሷ በተራዋ መወራጨት፣ መፈራገጥ ይዛለች። ሰውዬው አንገቷ ስር እንደተለጠፈ ማዳመጡን ቀጥሏል። መርከቢቱ ነፍሷን ስታ ከወዲያ ወዲህ ተወራጨች። ጉሮሮዋን ሰንጥቆ የወረደ በሚመስል አኳኋን ቆረር . . . ቆረረረረር . . . ቆረረረረር -ር አድርጋ ምራቋን ግርግጭ ግርግጭ አደረገችው። ፍም እሳት እንደነካው ቅቤ ቀለጠች። እርሷ በተራዋ አንገቱ ሥር ገብታ ተወሸቀች። ድንቢጥ አክላ አነሰች። ዝርግትግት ብላ ሁለመናዋን አስረከበች።

አድፍጦ የቆየው አውሬ ከመሸገበት ቀና አለ። ከሥፍራው ተስፈንጥሮ ተከተላት። አብሮአት ተምዘገዘገ። ደረሰባት ያዛት። ተፈናጠጠ። ተሳፈረባት። . . . እጥፍ ዘርጋ፣ ጎንብስ ቀና፣ እጥፍ ልምጥ፣ ጭብጥ ጭብጥብጥ ጭምቅ እያደረገ ወደ ሌላ ዓለም ይዟት ነጎደ። ዋጥ ስልቅጥ ጉርስ ሊያደርጋት ታገላት። እርሷም እህል አይቶ እንደማያውቅ ረሃብተኛ ልትውጠው ተስገበገበች። ተፍጨረጨረች። ልትውጠው ሞከረች። አልቻለችም። ደግማ ሞከረች አቃታት።

. .በመካከሉ ርችት ተተኮሰ። መርከቢቱን አገኛት። አልሳታትም። መሃል ግንባሩን በቀስት እንደተወጋ አውሬ ዘላ ፈረጠች። ተስፈነጠረች። በእርካታ ስቃይ አቃሰተች። ከሪችቱ ጋር ወደ ላይ ተምዘገዘገች። ሪችቱ ፈነዳ። አብራ ፈነዳች። ነፍሷን ሳተች። ነደደች። . . . ቀይ፣ ብጫ፣ ሃምራዊ፣ ሰማያዊ፣ አረንጓዴ፣ ቡናማ ቀለማት በዓይኖቿ ስር ፈሉባት፤ ሸፈኗት። የተለየ ጣዕም አፏን ሞላው። አጣጣመችው። ተስገብግባ ግርግጭ ግርግጭ አድርጋ ምራቋን ዋጠችው። . . . ከዚያም ቀስ ብላ በእርጋታ በእፎይታና በዝግታ ወርዳ ከባህሩ ላይ ብትንትን አለች። ጥልቅልቅ ብላ ተንሳፈፈች። እየቀዘቀዘች እየበረደች በላብ ተነክራ በዝምታ ተዋጠች። የምታሳዝን ትንሽዬ ፍጡር ሆና ዝርግትግት፣ ዝርክርክ ብላ አሽለበች። በዚያች አፍታ ድብን ያለ እንቅልፍ ጧ – ጭልጥ አድርጎ ወሰዳት።

ውቢት በሰውዬው እቅፍ ውስጥ እንዳለች ነቃች። እንደዕፍረትም አደረጋት። ቀስ ብላ ሰውዬውን ተመለከተችው። ደም የሸፈነው ፊቱና የተገሸለጠ ግንባሩ በደንብ ታያት። ቁስሉን ስታየው እርሷው እንደቆሰለች ያህል አመማት። ቆጠቆጣት።የደጉ ደንደሮ ቁመናና አካፋ እጁ ታሰባት። "በምኑ ቢመታው ነው እንዲህ ፊቱ የተገሸለጠው?" ስትል ራሷን ጠየቀች። ተስፈንጥራ ከአልጋዋ ላይ ወረደችና ወደ ቁምሳጥኗ አመራች።

ለትንሽ አፍታ በመስታወቱ ፊት ቆማ ፊት ለፊት የምታያትን ውቢት መንገሻን ትኩር ብላ አየቻት። እንደ ትላንት ማታው አታስጠላም። "ምጡን እርሺው ልጁን አንሺው" ስትል ለራሷ ነገረቻት። ከቁምሳጥኗ ውስጥ አልኮልና ባለመቶ ብር ኖቶች አወጣች። ደጉን አስጠራችው። በፍጥነት ሄዶ ደህና ጠቦት ገዝቶ እንዲመጣ እየነገረችው ድንገት ዓይኗ በቀኝ እጁ ጣት ላይ ባለው ትልቅ የመዳብ ቀለበት ላይ አረፈ። ኩስትርትር ብላ ገረመመችው። የሰውየውን ፊት ቀርድዶ የጣለው በዚህ ቀለበቱ መሆኑ ገባት።


"አውልቀህ ወዲህ በል አለችው" ፋታም ሳትሰጠው። አውልቆ ሰጣት። ማታ ይሞታል የተባለው ሰካራም ነፍሱ አድራ አባወራነት መሾሙን ደጉም ገብቶታል። መስኮቱን ከፍታ ቀለበቱን አሽቀንጥራ ወረወረችው። ደጉ ፊቱ ጠቆረ። ሳግ አነቀው፣ እልሁ መጣበት። ለምለም ኩርኩር "ውቢት ፍፍቴ" ቡና ቤት ስትቀጠር በመጀመሪያ ወር ደመወዟ የገዛችለት ስጦታ ነበረች።

ሰውዬው አሁን ተንጋሎ ተኝቷል። . . . የኮሎምቦስን ጉዞ እያሰላሰለ!

ተ ፈ ፀ መ

---------------------------------

የዚህ ልብወለድ ደራሲ አብዬ የብዕር ስማቸው ነው።



# ፓ ለ ቲ ካ ና ባ ላ ገ ር

ማዶ ለማዶ
ከሂርጳሳ አንዱዓለም (አ.አ)

ከአባይ ወዲያ ማዶ ወያኔ ተደላድላለች። ድፍን ትግራይን አስለቅቃ ተንሠራፍታበታለች። በደቡብ ጎንደር በነፋስ መውጫ በደብረ ታቦር በከምር ድንጋይ በወሎ እስከ ወልዲያ ደርሳ ትንሸራሸራለች። በእህል ከምር መሀል እንደገባች አይጥ ተመቻቺታል። ባላገሩን የኮር አባል፣ መንገድ መሪ ወንዝ አሻጋሪ ኮተቷን ተሸካሚ፣ አጋሰስ ነጂ አድርጋ መረማመጃ እንዲሆናት ላይ ታች ትላለች። ፀባይዋን አሳምራ ገራም መስላ ተለሳልሳለች። በሰሜን ሸዋ መሃል ሜዳ ድረስ ዘልቃ የመሃል ሜዳ ቆፈንና ብርድ ያንዘፈዝፋታል። መንግስት በጂት እንዳይፈልሳት ምሽግ ቆፍራ መሬት ውስጥ ፈልፍላ ገብታለች። ባላገር መስላ ተመሳስላ መንግሥት በገፍ የሚያደርገውን ምልመላ ትሰልላለች። ነጋዴ መስላ በየመንገዱና በየከተማው የሚደረገውን እንቅስቃሴ ታጠናለች። ኢንቬስተር መስላ የመንግሥት ባለስልጣኖችን፣ የጦር ጄኔራሎችንና አዣዦችን በውስኪ እየነከረች ታደነዝዛለች። ጮማ እያስቆረጠች፣ ጎድን እያስጠበሰች፣ ቡፌ እያስደገሰች፣ የመንግሥት ሹም ተሰብስቦ የሚያወራውን ታዳምጣለች። በኮክቴልና በራት ግብዣ ላይ ጥቂት መለኪያ ውስኪ ተይዞ የሚወራውን በአደባባይ ከሚወራው ጋር አንድ መሆኑን ትመዝናለች።

በእነዚህ አካባቢዎች በወያኔ ግዛት ስር ያለው ባላገር ደግሞ የወያኔ ነገር ምኑም አልጣመውም። የመንግሥት መ/ቤቶችንና ቢሮዎችን የምግብ ማብሰያ የአጋሰሷ ማጎሪያ አድርጋለች። የባለሥልጣን ቤት ሁሉ እሥር ቤት ሁኗል። ከአስተዳደርና ከዳኝነቱ የለችበትም። ባላገር ተበደልኩ እያለ ለሚያቀርበው አቤቱታና ክስ ራሱ ባላገሩ ተሰብስቦ ሕዝባዊ ፍርድ ይስጥ ባይ ናት። ይህ ዓይነቱ የሜዳ ላይ ፍርድ የማያዋጣ መሆኑን፣ ደም አቃብቶ በአገር እንደማያድኑር ዳፋው ለልጅ ልጅ እንደሚተርፍ ባላገር ያውቃል። ዳኛ በሌለበት፣ ምስክር በማይቆጠርበት ተከሳሽ መልስ በማይሰጥበት ሁኔታ ተበደልኩ ባይ ብቻ የሚደረድረውን የወንጀልና የስሞታ ዝርዝር ለመስማት በስብሰባ ላይ ተጎልቶ መዋሉም ለድሃ ጎጆው እንደማይረባው ይገባዋል።

ባላገር የወያኔ ስብሰቦሽና ሕዝባዊ ፍርድ ገና ከመነሻው ሰልችቶታል። ለአንድ ሰሞን ሆ ብሎ በደሉንና ስሞታውን ሲንዘራዘር የነበረ ባላገር ሁሉ ከጥዋት ጀምሮ ምሽት ድረስ ስብሰባ ላይ ተጥዶ መዋል ተረፈው። ሹም በነበሩ ግለሰቦች ላይ በኮሚቴ አባላት ላይ የሚሰማው ክስ ስፍር ቁጥር የለውም። የኮር ምልምል የሆነ አንዱ ኩታራ ሕዝቡን ሰብስቦ ሲፈርድና ሲያስፈርድ ይውላል።
ይህን ልብ ያለ ባላገርም:-

ኧረ ምን ይሉታል የኩታራ ውሎ፣
ይሽኛውን እሰሩት ይሽኛውን ስቀሉ፣
ይሽኛውን ፍቱት ይሽኛውን ግረፉት፣
ይኼኛውን ዕድሜ ልክ ያኛውን ሃያ ዓመት፣
የጀግኒትን ነገር ልብም አላላችሁት።
ወዩት አገር ታይቷል፣
ከማንስ ተወርሷል።
ዳኛ አሌለበቱ ከሳሽ እምንጓደድ፣
ያናኑረናል ወይ ይሄ የሜዳ ላይ ፍርድ።

እያለ ሕዝባዊ ፍርድ እየተባለ ባላገሩ በደሉኝ በሚላቸው ግለሰቦች ላይ የሚያሳልፈው ፍርድ ከዳኝነት ባህሉ ጋር ያልተለመደ ከአያት ከቅድመ አያት ያልተወረሰ መሆኑን በመንገር መተቸት ጀመረ።

ባላገር የሰለቸውና የጠላው ኮሚቴ ሲቀርለት በወያኔ የኮር አባላትና ምልምሎች መታመሱ ግን አልቀረለትም። እዚህ ግባ የማይባል ኩታራ ሁሉ የኮር አባል ሆኖ ትልቅ ሹም ሆኗል። በጭፍን ዳኝነት መስጠት፣ አፉን ሞልቶ መሳደብ፣ እንደልቡ ማሠር መፍታት ይዟል። በጣም በአጭር ጊዜያት ፈላጭ ቆራጭ አዣዥ ናዣዥ ወጥቶታል።
ባላገርም ይህን እየታዘበ:-

እስከዚያው ነው እንጂ እስከዚያው ድረስ፣
የበቅሎ ኮርቻ አይሆን ለፈረስ።

እያለ ያለ ቦታቸው የተቀመጡ፣ ያለ አቅማቸው የሚንጠራሩ መሆናቸውን በዘፈን መልክ በቀረርቶ በፉከራ ይነግራቸው ጀምሯል። የወያኔን ስብከት ሰምቶ ለወያኔ የሚያደዘድዙ ሥልጣን ፈላጊዎችና ታጣፊ ክላሽ ታጥቀው ቁንን ቁንን የሚሉ ነፍስ ያላወቁ ልጆች ባላገሩን ያምሱት ገቡ። ባላገርም አምና ካቻምና የሆነውን፣ ለወያኔ እዚህ መድረስም ቢሆን እርሱም መርዳቱን እያስታወሰ በጉልበታቸው እንዳይመኩ የወያኔ ጀሌዎችን መምከር ጀመረ። እየተዋጋች ከመጣችዋ ወያኔ ይልቅ ከድል በኋላ የተቀላቀሉት ጀሌዎች ባላገሩን አሳር አበሉት። ባላገርም:-

ኧረ ተዉ ግድ የለም፣ አንርሣ የአምናን፣
ኧረ ተዉ ግድ የለም፣ አንርሣ የአቻምናን፣
ኧረ ተዉ ግድ የለም፣ አንርሣ ትናንትን፣
አይጥና ድመት እንዳንሆን መልሰን።

እያለ ከራሱ መካከል የኮር አባልነት ተመልምለው የወያኔ ጀሌ ሆነው ያለ አቅማቸው ሥልጣን ላይ ቁብ ያሉትን ልጆቹን አስጠነቀቀ። ያገኙትም ድል ሆነ የያዙት መሣሪያ ቢሆን ትላንት ባለ ድልና ጉልበተኛ ከነበረው መንግሥት ዘንድ የነበረ ዛሬ ግን ሁኔታው ተገልብጦ በእነርሱ እጅ መግባቱን እንዲያውቁት "ድል የእግዚአብሔር ነው፣ ኃይል የመድሃኒአለም ነው" እያለ መከራቸው።
እንዲህ እያለ:-

ደርግም ይዞ ነበር ሰላሳ ጎራሽ፣
እየጣለው ሄደ እንጂ ለአንዳንድ ብጣሽ።
ጩኸኙ በጉልበት ይኮራ ነበረ፣
አምላክ ተቀየመው እጅ እግሩ ታሠረ።

ወያኔ እግዚአብሔርን አታውቅ፣ አምላክን አትፈራ፣ ሲነግሯት አትሰማ የባላገሩን ምክርና ተግሳጽ ከምንም አትቆጥር። ባላገሩን ሰብስባ ሕዝባዊ ፍርድ እያስፈረደች የምትፈልገውን አጋድማ አረደች። ገሚሱንም እያስገባች ከረቸመችበት። አኳኋኑ ያላማራትን፣ ያሳድማል ብላ የምትፈራውንም እያጋዘች ምድር ውስጥ ተቆፍረው በተዘጋጁ እሥር ቤቶች ውስጥ ዘጋችባቸው። እርስ በእርሱ ባላገሩን እያቆላለፈች አንዱን በአንዱ ላይ እያስፈረደች የበቀል ጥማቷን ተወጣች። ባላገሩ ነገሩ ገብቶት "እርስ በእርሱ ሥጋን በኩበት ጠበሱ" እያለ ይተርትባት ጀምሯል።

ይሁን እንጂ ለኮር ምልመላ፣ ለሕዝባዊ ፍርድ ለግምገማ ለምኑም ለምኑም ባላገሩን ስብሰባ እየጠራች እርሻ ቀርቶ፣ አዝመራ መሰብሰብ ቀርቶ፣ ልጅ አዋቂው ወንዱ ሴቱ ሥራ ፈቶ ውሎው አደባባይ ሆነ። በደቡብ ጎንደር ደብረ ታቦር አካባቢ በአንድ የገጠር ትምህርት ቤት ውስጥ የጎልማሶች ማሠልጠኛ ጣቢያ (ጎማጣ) ኃላፊ የነበረ አንድ የአንደኛ ደረጃ መምህር የቀረበበት ክስ ሶስት ቀን ሙሉ ሲሰማ ሰንብቶ የዕድሜ ልክ እስራት ተወስኖበት ነበር።

ባላገር ይህቺን ዓይነቷን ፍርድ አይወድም። ግራ ቀኝ የሚሰማ ዳኛ በሌለበት፣ ምስክር በማይሰማበት ከሳሽ ብቻ እንዳሻው ወንጀል ደርድሮ የልቡን ፍርድ የሚሰጥበት ሁኔታ እንደማያዛልቅ እንደማያዋጣ ያውቃል።

የማይመስል ነገር የማይመሳሰል፣
አቤት ብሎ እንጂ ድሃ መች ፈርዶ ያውቃል፣
ለብ የለው ውሻ ጣዲቅ ይቀላውጣል።

በማለት የወያኔ የዳኝነት ወግ የማያዋጣ መሆኑን ለባለጊዜ ለባለተራ ተናገረ። በዚህ ዓይነት በተሰጡ ሕዝባዊ ፍርዶች በርካታ ንጹህ ሰዎች የሞት ቅጣት ተፈጽሞባቸዋል።ታሥረዋል።ንብረታቸውን ተወርሰዋል።

ባላገር ሥራውን ትቶ ስብስቦሽ ላይ ተጥዶ ከአደባባይ መዋል አለሆነለትም። ለአንዲት ጀምበር ከቀዬው ከራቀ ከአዝመራው ከተስተጓጎለ ብዙ ነገር ይጠፋል። ከብት ከዱር ሊቀር ይችላል። ወይም የሰው እህል የሰው ንብረት ገብተው አፈላማ መግባት አለ። በደጅ የተከመረ እህል፣ ወይም ጭድ ዶሮ ጭሮ ይበትነዋል ወይ እልፍ ሂያጅ የከብት መንጋ ያጠፋዋል። የአንድ ሰሞን አዝመራ ከተስተጓጎለ ደግሞ ካለ ዓመት አይገኝም። ይህንን ብሶቱን እንዲህ ሲል በዜማ በግጥም ገልጾታል:-

ካቻምና ስብስቦሽ፣
ዘንድሮም ስብስቦሽ፣
የወጣ አይመለስ፣
የተበደለ አይካስ፣
ድሃ አይፈረድለት የተጣላ አይታረቅ፣
እንዲያው ምን ይሉታል የድሃን ዘጥዘጥ።
እኔስ የዘንድሮው ቅጥአንባሩ ጠፋኝ፣
ተበደልኩኝ ብል ፍረድበት አሉኝ።

በማለት እያማረረ ይልቁንም መሆን ያለበት የሚለውን ለወያኔ ሹሞችና ጀሌዎች እንዲህ ሲል ይነግሯቸው ጀመር:-

ጽድቁ በቀረና በወጉ በኮነነኝ፣
ዳኝነቱ ቀርቶ የሚሰማኝ ባገኝ አላቸው።

. . የስብሰባ ነገር ከተነሣ በአብዮቱ የመጀመሪያ ዓመታት ግድም ባላገር ተመሣሣይ ሁኔታ አጋጥሞት ነበር። ያኔ ወንዱ ሴቱ በፍርድ ሸንጎ፣ በአብዮት ጠባቂነት፣ በኪነት፣ በተለያዩ ኮሚቴዎች ተመርጦ ከስብሰባ ወደ ስብሰባ ሲሮጥ ባላገር ብዙ ኑሮው ተጎሳቁሎበታል። በዚያን ወቅት እንዲህ ሆኖል ይባላል። . . . ሚስቱ የኪነት አባል እርሱ ደግሞ የአብዮት ጥበቃ ተመራጭ የሆነ የጎንደር ባላገር ቀኑን ሙሉ ስብሰባ ውሎ ሲገባ ከደጁ የተከመረውን ገለባና ጭድ ዶሮ ጭሮ በትኖታል። ከብቱ እንደተሰማራ ከዱር ቀርቶበታል። ይህ ያበሳጨው አባወራ ሚስቱን ሊቆጣ ይቃጣዋል። ወ/ሮ ሚስትም ኪነት ውላ ደክሞአት ጋደም ብላለች። የባሏን ቁጣ ትሰማና ጋደም ካለችበት ቀና ብላ ቀን ስትሰበክ የዋለችውን የእኩልነትና የአብዮት ጣጣ ትንጣጣባታለች አሉ። ሆድ የባሰውም ባላገር:-

የከመርነው ፈርሶ ደጃችን መጥፋቱ፣
ከብታችን ዱር ውሎ ስብሳቢ ማጣቱ።
ካህን (ኪነት) መሆንሽ ነው
አንቺ የእኔ እህት ሴትቱ።
እንዴት እንዲህ ይሆናል ብዬ ብናገራት፣
የእስከዛሬው ይበቃሃል፣
እኩልነት መጥቷል
ብላ ብትመልስ፣

እቀጣለሁ ብዬ አለንጋ ባነሳ፣
ለሸንጎ ነግሬ አሳስርሃለሁ አልችኝ መልሳ።
ልሂደው ልሂደው ከአገሬ ልጥፋ፣
ሚስቴ ካህን (ኪነት) ሆና ቤታችን ከጠፋ።
የሴት ሊቀ መንበር፣ የሴት ፍርድ ሸንጎ፣
ሠላም እንገናኝ ድስትና ሞጎጎ።
ሲል ምሬቱን ገልጾ ነበር ይባላል።

ዘንድሮም አሁንም ባላገር ወያኔ ፍርድ ትሰጠኛለች። የተነጠቅሁትን ማሳዬን ታስመልስልኛለች። ለበደሌ ካሣ ታስከፍልልኛለች ብሎ ቀርቦ ቢያያት ስብስቦሽ አታከተው። እናም:-

ወንዱም አላረሰ፣ ሴቱም አልፈተለ፣
ብስቦሽ ግምገማ ተሰጥቶ እየዋለ።
በማለት ምሬቱንና ስሞታውን ተናገረ።

ወያኔ በያዘቻቸው አካባቢዎች የፕሬዚዳንት መንግሥቱ መንግሥት "የወደቀው መንግሥት" ይባል ጀምሯል። መንግሥትም ቢሆን ባላገሩ በወያኔ ላይ በአጭር ጊዜ ውስጥ የሚያሰማውን ስሞታ ሰምቶ ዝም አላለም። በአንዳንድ ታዋቂ የአካባቢው ተወላጆችና በአዲስ አበባ በንግድ ሥራ ላይ በተሰማሩ ሰዎች አማካይነት ውስጥ ውስጡን ባላገሩን በወያኔ ላይ ለማሳመጽ ሙከራ አደርጎ ነበር። ግን አልሰራም። ባላገር በመንግሥት ላይ የነበረውን ቂም በቀል አልረሳም። መንግሥት አሁን ውስጥ ውስጡን መላላኩ ለራሱ ጥቅም እንጂ ለባላገር እንደማይበጀው አውቋል።

እናም በሠርግ ላይ ሲገናኝ፣ ታቦት ሲያነግስ፣ በለቅሶ በሰንበቴ ሲገናኝ ምክክሩ በሀገር ሽማግሌዎች አማካይነት ይደረግ ጀምሯል። በአንዳንድ ቦታም ከምክክሩ በፊት በአመቺና በአሳቻ ሥፍራ ወያኔን እያነቁ ፀጥ ማድረግ ሲጀመር የአገር ሽማግሌዎች ቶሎ ብለው ተመካክረው ውሳኔ ላይ ደረሱ። ይህም በዘፈን እየተመሰለ ለየባላገሩ እንዲህ ሲል መልዕክት ተላለፈ:-

እኔ ከአባይ ማዶ አንተ ከአባይ ወዲህ፣
ይሻለኝ ነበረ ጥንቱንም ባላውቅህ፣
ወይ አንተ አትመጣ ወይ እኔን አትወስደኝ፣
የሩቅ ለሩቅ ፍቅር ዳሩ ምን ሊጠቅመኝ።

እያለ ባላገር በፍቅር እያስመሰለ፣ የመንግሥት ውስጥ ውስጡን መላላክ ምንም እንደማይጠቅመው እርስ በእርሱ በዘፈን ተነጋገረ።

ከዚህም ሌላ የመንግሥት አይሮፕላኖች አሳቻ ጊዜ ጠብቀው በወያኔ ይዞታ ላይ የሚጥሉአቸውም ቦንቦች ለባላገሩ ሌላው ፍዳ ነበር። ጄት ድንገት ይመጣና መሬቱን ፈነቃቅሎት፣ አርሶት ይሄዳል። የመንግሥት ጄቶች የሚጥሉት ቦንብ እንደፍልፈል መሬት ፈልፍላ የገባችውን ወያኔን ሳይሆን የባላገሩን አዝመራና ከብቶች እንዳልነበሩ አደረጋቸው። ባላገርም:-

መንግሥቱ ኃ/ማርያም ኸረ ቦንብ ጣለ፣
እናቱን ነው እንጂ ሌላም አልገደለ።

ሲል ምሬቱን ገለፀ። ባላገር ለመንግስቱ ኃ/ማርያም መንግሥት እናቱ ነበርኩ ባይ ነው። የሚጣለውም ቦንብ የባላገሩን እርሻና አዝመራ ከመጉዳቱ በቀር ወያኔን እንዳላገኛት ለማሳወቅ:-

የሚተኮሰው መድፍ የሚጣለው ፈንጂ፣
ወያኔን አልነካም መሬቷን ነው እንጂ።

በማለት የመንግሥት ጦር ከርቀትና በአየር የሚያደርገው ድብደባ ያደረሰበትን ጉዳት ተናገረ።

የሚሰማ አልነበረም። መንግሥት ይህን የሚሰማበት ጆሮ የለውም። ለወያኔ ደግሞ "ቅቤ በማንኪያ" ሆነላት። ባላገሩ እንዳይነሳባትና እንዳያምጽባት ለመከላከልና ከእርሷ ጎን እንዲቆምላት ለማድረግ ደህና ዕድል ሰጣት።

ይልቁንም ደግሞ ይህ የመንግሥት ድርጊት የመንግሥት ጦር በለስ ቀንቶት ወያኔን አሸንፎ አባይን ቢሻገር እንኳ ለወያኔ አብልተሃል፣ አጠጥተሃል፣ ወያኔን ደግፈሃል ተብሎ ሌላ መከራና ፍዳ ሊያመጣበት እንደሚችል ባላገር ጠረጠረ። መንግሥት ከባላገሩ ጋር ውስጥ ውስጡን የጀመረው የምስጢር ግንኙነትም ሳይጠብቅ ቀረ። እንዲያውም የመንግሥት ጦር ገፍቶ ሲመጣ ባላገር ቁርጡን አውቆ ጫካ እንዲገባ ተመከረ። በየአካባቢው ላለው ባላገርም እንዲህ እየተባለ መልዕክቱ ተዳረሰ:-

መንግሥቱ ኃ/ማርያም ታሞ ታሥሯል በመጫኛ፣
በጥሶ የመጣ ዕለት ወይ እኛ ወይ እኛ።
በጥሶ የመጣ ዕለት አይኑን አፍጥጦ፣
የመጠጊያ ያለህ ትንሽት ቁጥቋጦ።

በማለት ባላገር ከወዲሁ ቆርጦ ተዘጋጅቶ እንዲጠብቅ ተነገረው። ወዲህ ደግሞ ባላገር ከመሃል አገር ተቆራርጦ ሸቀጥ ማግኘት አልቻለም። የሚገኘውም ያሀል ዋጋው በእጥፍ እጥፍ ጨምሮበት አቅሙ አልቻለም። ጨው የለም። ላምባ የለም። አቡጀዲ ጨርቃ ጨርቅ አይገኝም። የባላገሩ ጎጆ በጨለማ ተዳፍና ማደር ጀመረች። ጨው የሌለው ሽሮ መብላት የተለመደ እየሆነ መጣ። እህል ወይም ከብት ተሽጦ ለመላ ቤተሰቡ የዓመት ልብስ ይበቃ የነበረው ገንዘብ አሁን ለአንድ ሰው እንኳ አልችል አለ። ባላገርም የተመኘው ቀርቶ ያላሰበው በመሆኑ:-

ቀን ይወጣል ብዬ ብጠብቅ ብጠብቅ፣
ፍርድ አገኝ እንደሁ ብዬ ብጠብቅ ብጠብቅ፣
ያልፍልኛል ብዬ ብጠብቅ ብጠብቅ፣
እንኳን ቀን ሊወጣ ጨለማ ነው ጥቅጥቅ።

በማለት ወደ ባሰና ወደ ከፋ ሁኔታ ውስጥ መግባቱን ተናገረ። ባላገር ምርጫ በሌለው ሁኔታ ውስጥ ገባ። ከመንግሥት ወገን ሊሆን አልተቻለውም። ያለፈ ቁስሉ ገና ያልሻረ ጠባሳው አለ። ከወያኔ ወገን መሆን አቅቶታል። መላ ያለው፣ ተስፋ የሚሰጥ፣ የሚያጓጓ እንዳችም ነገር አላገኘበትም። እናም ባላገሩ እንዲህ አለ:-

እምናንም አየሁት፣
ዘንድሮንም አየሁት፣
ከደገሙትማ የከርሞን አይቼ፣
ገዳም እገባለሁ ቆቤን አስፍቼ።
መውዜር እንደሁ የለኝ፣
ክላሽ እንደሁ የለኝ፣
ዱሩን አልሞከረው። በማለት ምርጫ ማጣቱንና ያደረበትንም ስሜት ይገልጽ ጀመረ።

ከአባይ ወዲህ ማዶ መንግሥት ነፍሱ ልትወጣ እንደሚያጣጥር በሽተኛ ይወራጫል። ባለ በሌለ ኃይሉ ቢያንስ ወያኔን ካለችበት ገድቦ ለመያዝ ወራወጥ ይዟል። "ሁሉም ነገር ወደ ጦር ግንባር" በሚል መፈክር ሥር አብዮታዊ የዘመቻ ማዕከል ከቤተመንግሥት ጀምሮ እስከታች መንደር ድረስ ተዘርግቶና ተዋቅሮ ሹሙ ሁሉ ይደክማል። የሠራዊት ምልመላ በገፍ በስፋት ተጧጡፏል።

አሁን የመንግሥት መቆናጠጫ ሰሜን ሸዋ፣ ደቡብ ወሎ፣ ጎጃምና ሰሜን ጎንደር ብቻ ናቸው። ወሎ፣ ሸዋና ጎንደር ወያኔ ከፊሉን ስለያዘችው ዋናው መቆናጠጫ ደግሞ እስካሁን ወያኔ ያልያዘችው ጎጃም መሆኑ ነው።

ወያኔ ጎጃም ከገባች ድፍን ጎንደር በቀላሉ በእጇ ሊገባ እንደሚችል ያውቀዋል። ጎጃም ተያዘ ማለት ባሕርዳር የሚገኘውን አለምአቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ማጣት ማለት ነው። እርሱን ማጣት ደግሞ ከዚህ የአውሮፕላን ማረፊያ እየተነሱ ለሰራዊቱ ድጋፍ የሚሰጡ ተዋጊ ጀቶችና ከምስራቅና ከመሃል አገር ሰራዊት የሚያመላልሱ የማመላለሻ አውሮፕላኖች ግዳጅ ሊቋረጥ ወይም አስቸጋሪ ሊሆን ነው። ወያኔ ጎጃምን ከያዘች በበነጋታው በቡሬ በኩል ወደ ሆሮ ጉድሩ ወደ ወለጋ ተሻግራ፣ በደጀን በኩል ወደ ጎሐጽዮን ገስግሳ ወደ መሃል ልትገባ የምትችልበት አደጋ ስላለው በተለይ ጎጃም ውስጥ ይደረግ የነበረው መሰናዶ ጠንከር ያለ ነበር። ኢትኖራ አምራቾች ስብሰባ ላይ ከጓድ ፕሬዚደንት አጠር ቆፍጠን ያለ መመሪያ የተቀበለው የጎጃም ሹማምንት ሁሉ በሰራዊት ምልመላ ደፋ ቀና ይላል። ወያኔን ካለችበት ገድቦ ለመያዝ የአገሩ ባላገር በገፍ እየተመለመለ ሥልጠናና ትጥቅ እየተሰጠው ለግዳጅ እንዲሰማራ ከማድረግ ሌላ ምርጫ እንደሌለው ጓድ ፕሬዚደንት በጥብቅ አስገንዝበውታል።

ባላገር ደግሞ ወያኔ ጎጃምን የረገጠች ጊዜ እንደክረምት ጎርፍ ክልብስ ብላ ከነኮተታኮተቷ፣ ከነቅማሏ፣ ከነቅማንጅሯ አጋሰሷን ነድታ ወደ ምዕራብና ወደ መሃል እንደምትዘልቅ አውቋል። ወያኔን ገድቦ ለመያዝ ብዙ ባላገሮች እንደሚያስፈልጉም ገብቶታል።

ይህቺን ያወቀ ባላገር በጎበዝ አለቃ ተደራጅቶ በአገር ሽማግሌዎች፣ በቄስ፣ በመነኩሴ ተማምሎ መውጫ መንገዱን ማምለጫ ዘዴውን ቀይሷል። በብዙ ቀበሌዎች ባላገር በድብቅ ተሰብስቦ የጎበዝ አለቃ መርጦ መክሮ ተማምሎ ጨርሷል። የቤተክርስቲያን መስቀል ወጥቶ፣ ጠመንጃ ተደርድሮ፣ እያንዳንዱ ሰው መስቀል ይዞ ምሏል። በተደረደሩት ጠመንጃዎች ላይ አንድ በአንድ እየተራመደ "ይኽ ቢያልፈኝ፣ ይሄ አይለፈኝ፣ ዘር አይውጣልኝ፣ የአገር ምስጢር ባወጣ ሚስቴ ጥቁር ውሻ ትውለድ" በማለት በአገሩ ታቦት ቃል ኪዳን ተገባብቷል።

ባላገር የሚይዘውን፣ የሚጨብጠውን ካጣ መንግሥት ጋር መፋጠጥ እንደማይቻለውም አውቋል። ሁኔታው አልለየለትም። ድንገት እንኳ መንግሥት በለስ ቀንቶት ዕድሜው ቢሰነብት የሚደርስበትን መከራና ፍዳ ገምቷል። ለዚህም እንደ ዋንኛ ዘዴ ተደርጎ የተወሰደው በተቻለ መጠን ሽማግሌዎችን፣ አካለ ጎዶሎና ደካማ ሰዎችን መልምሎ መስጠት ነው። በተለይም ሽማግሌዎች ከልጆቻችን በፊት ቀድመን እኛ እንሙት እያሉ አሻፈረኝ እንዲሉ ተመከረ። በምልመላው ውስጥ ገብተው የሚሰለጥኑ ጎልማሶች ሥልጠናውን ጨርሰው ለግዳጅ ከመሰማራታቸው በፊት መሣሪያ እጃቸው ሲገባ የጥበቃ ኬላውን ሰብረው ወደ ቀበሌያቸው እንዲመለሱ ድፍን ጎጃም ውስጥ ውስጡን ሲማማልና ሲመካከር ሰነበተ።

እንዲህም ሲል እርስ በእርሱ መልዕክት አስተላለፈ።

ዝመቱ ይሉናል ዝመቱ ታጠቁ፣
እነርሱ እንደሴት ወይዘሮ እያብረቀረቁ።
እንደራበኝ እንደሞረሞረኝ፣
ከበላ ሰው ጋር ልሞት ነው መሰለኝ።

በማለት መንግሥት ታጥቆ የተነሳለት ዘመቻ ለባላገሩ ምን ማለት እንደሆነ ተነጋገረ።

የመንግሥት ሹማምንት ለምልመላ በአጭር ታጥቀዋል። የገበሬ ማሕበራት ሊቀመንበሮችን፣ የፍርድ ሸንጎና የኮሚቴ አባሎችን አስጠርተው ጥብቅ መመሪያ ሰጥተዋል። እያንዳንዱ ቀበሌ ገበሬ ማኀበር ተሰብስቦ እንዲቆያቸው በወሰኑበት ዕለት የአውራጃ ሹማምንት በወታደር ታጅበው ከች እያለ ባላገሩን መመልመል ይዘዋል።

ባላገርም ተሰናድቶ ቆይቶአቸዋል። ሰሞኑን በየደብሩ ሲመክርና ሲማማልበት የከረመውን በልቡ ይዞ የመንግሥት ሹማምንት የሚሉትን ለመፈፀም የፈቀደ መስሎ ተሰብስቦ ጠብቋል። እረኞችና ሴቶች ግን መዝፈን ጀምረዋል። እንዲህ እያሉ:—

አጀብ ቡሬ ሸኩዳናና እንዴት ዘይደሃል፣
አጀብ ደጋ ዳሞት እንዴት ዘይደሃል፣
አጀብ ቆላ ዳሞት እንዴት ዘይደሃል፣
ገጉሣ ወንበርማ እንዴት ዘይደሃል፣
አገው ግምጃ ቤት እንዴት ዘይደሃል፣
አወይ ማቻከናን እንዴት ዘይደሃል፣
ሞጣና ብቸና እንዴት ዘይደሃል፣
እነሴና እነብሴ እንዴት ዘይደሃል፣
ደምበጫ አማኑኤል እንዴት ዘይደሃል፣
ቄስና አንድ አይና መገበር ይዘሃል።

በማለት ለግዳጅ የማይሆኑ ቄሳውስትና አካለ ጎዶሎዎችን ለመንግስት የሰራዊት ምልመላ እንዲገብር (እንዲያቀርብ) ይህም አጀብ የሚያሰኝ ዘዴ መሆኑን የጎጃም ባላገር እንዲያውቀው ተደረገ።

ሽማግሌ አዛውንት ያረጀ ያፈጀው፣
አንካሣ አንድ አይናው ኮሣሣ ኮሣሣው፣
ይሂድና ይሙት እዚህም ቀባሪ የለው።

በማለትም ሽማግሌዎች አዛውንቶችና ቄሳውስት እዚህ ቀርተው ቀባሪ ከሚያጡ ወደ ጦር ግንባር ዘምተው የሆኑትን እንዲሆኑ መልዕክቱ በመላው ጎጃም ተሰራጨ። መንግሥት አካለ ጎዶሎና አዛውንቶችን እንደማያዘምትም ባላገር ልቡናው ያውቃል።

ይህ የአገሬው ምክርና መሃላ ደግሞ ከመንግሥት ሹማምንት ጆሮ ገና አልገባም። መሃላውን ሰብሮ ይህን ምስጢር አውጥቶ የተገኘ ባላገር ከዕድር ከሰንበቴ ይወጣል። ሚስቱ፣ ልጆቹ፣ ከብቱ ከአገሬው ጋር አይቀላቀሉም። እሳት ከጎረቤት አይጭርም። ውኃ ከኩሬ አይቀዳም። በሬው በተገኘበት ታርዶ ይበላል። የባሰ ሁኔታ ከመጣም ቤቱ፣ ንብረቱ በሌሊት ተቃጥሎ ከአገር ይባረራል ወይም አንዱ ስርቻ ተገድሎ ይጣላል። መኃላ የአገር ምስጢር ጥብቅ ነው። ተመራጮችና የኮሚቴ አባላትም አቀፍቁሮ ከተነሣ ባላገር ጋር የበለጠ መቀያየም የማያዋጣቸው መሆኑን አውቀውት እጃቸውንና እንደበታቸውን ሰብስበው አርፈው ተቀምጠዋል። በዚያን ወቅት በጎጃም በአንደኛው አውራጃ ውስጥ የሆነውን ላጫውትዎ።

. . . የአውራጃው ሹም በስቴሽን ዋገን እየከነፈ በወታደሮች ታጅቦ በአንድ ቀበሌ ገበሬ ማኅበር ይደርሳል። የቀበሌው ባላገር ተሰብስቦ እንዲቆየው አስቀድሞ ቀጠሮ ተይዞ ስለነበር በቀበሌው ውስጥ ነፍስ የሚያውቀው ሁሉ ከደብር ተሰብስቧል። በርከት ያለ ባላገር ተሰብስቦ የቆየው ሹም ግዳጁ እንደሰመረለት እንደተሳካለት በመገመት ደስ ብሎታል።

የአውራጃው ሹም እንደደረሰ በአገሬው የአነጋገር ዘዬ ቅስቀሳ ይጀምራል። ስለ ሀገር ነፃነት፣ ስለ ባንዲራ፣ ስለ አገር አንድነት ብዙ ብዙ ይላል። ብዙ ባላገሮች ከሜዳው ላይ ፍስስ ብለው ያዳምጣሉ። ምልመላው ሲካሄድ ሕዝቡን እንዲያባብሉት ተሰሚነት ያላቸው የሀገር ሽማግሌዎችና ቀሳውስት አስተያየት እንዲሰጡ አገሬውን እንዲያግባቡ ማድረግ አንዱ በምልመላው ረገድ የተሰጠ መመሪያ ስለነበር የሐገር ሽማግሌዎች አስተያየታችሁን ስጡ ይላል። ሽማግሌዎችና ካህናት ተነስተው ለሀገር መሞት ከጥንትም ያለ ነው እያሉ አስተያየታቸውን ሰጡ። ልክ ጥቆማው ተጀምሮ የአንድ ሰው ስም ከመጠራቱ በፊት አንድ ኮሳሳ ሽማግሌ ተነስተው ይፎክሩ ጀመር።

ዘራፍ አካኪ ዘራፍ አካኪ ዘራፍ
አካኪ ዘራፍ ብሎ ሲነሣ፣
የሌሊት አውሬ የቀን ጃውሣ፣
ቁጭ ብሎ ተኳሽ አነጣጣሪ፣
የጠላቱን ቅልጥም ሰባሪ።
ዘሬፍ የኔሁን ረታ፣
አነጣጣሪ ግንባር የሚመታ፣

ዘራፍ ዘራፍ . . . እያሉ ኮተት ኮተት አሉ። ከወዲያ ወዲህ ተንቀራፈፉ። ተንጎራደዱ። ቅስማቸው አልሰበር ብሎ እንጂ አካላቸው ደክሞአል። እንኳን የጠላታቸውን ቅልጥም የሚሰብሩ ግንባር የሚመቱ ቀርቶ ውለው እንኳ የሚገቡ አይመስሉም። ድምፃቸው የፉከራ ሳይሆን የኑዛዜ ያህል ነው። ኮተት፣ ኮተት ቀርፈፍ ብለው ሰውን ሁሉ ገረመሙት። ፈንጠር ፈንጠር ቆነጥነጥ ማለታቸው ነው በእሳቸው ቤት። እሳቸውን ተከትለውም አንድ አራት ሽማግሌዎች ማቅራራት መፎከር ጀመሩ። ግራ የገባው የአውራጃ ሹም "ሥነ ሥርዓት፣ ሥነ ሥርዓት" እያለ ይጮሃል። ሽማግሌዎቹ እየተንቀራፈፉ ይፎክራሉ። ሌሎቹ ፀጥ ብለው ሲቀመጡ አንደኛው ግን አሻፈረኝ አሉ።

"ቆዩ አባቴ ፉከራውን ያቁሙልን" አለ አውራጃ ሹሙ

"የምናገረው አለኝ ጌታው!" አሉ ሽማግሌው በተራቸው።

"ይበሉ ይናገሩ" አለ ሹሙ ለእኚህ ኮሣሣ ሽማግሌ ጠመንጃ ሰጥቶ የሚያዘምታቸው ስራ የፈታ ማን ይኖራል? በሚል አስተያየት ሽማግሌውን እየተመለከታቸው።

"ምነው ሐገሬ ምን አልኩህ? እንዴት እኔ አባቱ እያለሁ ልጄ ቀድሞኝ ይዘምታል? እኔ እያለሁ እንዴት ልጄ ቀድሞኝ ይደፋል? ባይሆን እኔ አባቱ ሄጄ ስሞት አባቴ! አባቴ! ብሎ ደሜን ያውጣ እንጂ እንዴት እኔ ቁጭ ብዬ ልጄ ይዘምታል?" አሉ ሽማግሌው ወደ ባላገሩ ዞረው።

"ምንድነው የሚሉት?" አላቸው ሹሙ ግራ በተጋባ መንፈስ!

"ልናገር ጌታው! ተናገሩ ካላችሁን እናገራለሁ። መቼም መዝመት ጥንትም ያለ ነው። ከአያት ከቅድመ አያት ጀምሮ ያለ ነው። የምናውቀው አባት ሲዘምት ልጅ ይከተላል። ዛዲያ ሐገሬ ምን በደልኩህ እኔ እያለሁ ልጄን ለዘመቻ የምትልከው?" አሉና ባላገሩን ከፍ ዝቅ አድርገው ገረመሙት። ሌሎቹ ሽማግሌዎች ደግሞ ተነስተው መፎከር ጀመሩ። አስተያየት ሲሰጡ የነበሩትም እዛውንት:-

"ዘራፍ አካኪ ዘራፍ አካኪ ዘራፍ
ዘራፍ የኔሁን ረታ
አነጣጥሮ ራስ የሚመታ . . ." አሉና

ዝም አሉ። ፉከራው ጠፋባቸው።

"እኔ እኮ እግር አልመታም፣ ግንባር ነው የምመታው፣

ዘራፍ አካኪ ዘራፍ አካኪ ዘራፍ
ዘራፍ ብሎ ሲነሣ፣
የለሊት አውሬ የቀን ጃውሳ፣
ሲያዩት አልባሌ ልቡ የአንበሣ"

እያሉ ፎከሩ።

"ስምዎ ማነው አባቴ" አላቸው ሹሙ።

"የኔሁን ረታ"

"የትኛው ነው ልጅዎ?"

"ይህኛው" አሉ ወደ አንድ ጠይም ባላገር እያመለከቱ።

"ተነሥ እስቲ አንተ ወንድሜ ማነው ስምህ?" አለው ሹሙ ወደ ባላገሩ ዞሮ

"እይሸሹህም ስሜነህ" አለ ባላገሩ

"ታዲያ ለምንድነው ልጄ ነው የሚሉት?" አለ አውራጃ ሹሙ፣ የአባትና የልጁ ስም አልገጣጠም ስላለው ወደ ሽማግሌው እያመለከተ

"ልጄ ነው" አሉ ሽማግሌው ተንፈራጠው እንደፎካሪ ለመቆም እየቃጣቸው።

"ማ ቢወልድ ማ? አላቸው ሹሙ መልሶ።

"የወንድሜ ልጅ ነው። የወንድም ልጅ ባይወልዱትም ልጅ ነው።" አሉና ሳይጨርሱ

ዘራፍ አካኪ ዘራፍ
አካኪ ዘራፍ
እንኳን ለሀገሬ እንኳን ለባንዲራ" . . .

ዝም አሉ። አሁንም ግጥሙ ጠፋባቸው።

"እባክዎ አንቱ ሰውዬ ዝም ይበሉ" አለ የአውራጃው ሹም እንደመበሳጨት ብሎ።

"እንግዲያውስ እከሌ ይዝመት" አለ አንዱ ባላገር ከወዳያ ጥግ።

"ማነው እከሌ ማለት እስቲ ብድግ በል" አለ ሹሙ። ጥምጥም የጠመጠሙ አንድ ኮሣሣ ቄስ እየተንኳተቱ ብድግ አሉ።

"እኚህማ ቄስ ናቸው። በዚህ ላይ አንድ ዓይና" አለ ሹሙ።

"ቢሆንም ለሀገሬ እሞታለሁ" አሉ ቄሱ እንደቅድሙ ሽማግሌ እየተንኳተቱ። "እንዲያውም አንድ ዓይና መሆኔ ለማነጣጠር ያመቸኛል።" አሉና የተሰበሰበውን ባላገር ሁሉ አሳቁት። አውራጃ ሹሙ ግን አልሳቀም። በመካከሉ ሌላ አንድ ሽማግሌ ብድግ አሉና።

"እኔም ለሀገሬ ሟች ነኝ። . . . እንዲህ እንደሚያዩኝ ደካማ ሽማግሌ አልምሰልዎ ጌታው። የማሳፍር አይደለሁም።" እያሉ ቦተት ቦተት፣ ቀርፈፍ ቀርፈፍ ብለው ማቅራራት ያዙ። ሹሙ አንዳች ነገር ጠርጥሯል።

"እሺ አባቴ እርስዎ ሲፈለጉ ይመጣሉ። አሁን ይቀመጡ" አላቸው በብስጭት።
ጥቆማው ቀጠለና አንድ ሰው ብድግ አለ። ቀጭን ረዥም እግሩን ዝሆኔ ያሳበጠው ጠይም ባላገር ነው።

"ማነው ወንድሜ ስምህ?" አለ የአውራጃው ሹም።

"ሰውነት መልካሙ" ሲል መለሰ ባላገሩ።

እስቲ ወደዚህ ወጣ በል።" ባላገሩ እየተንቀራፈፈ ወደፊት መጣ። ሰውዬው እግረ በሽተኛ ነው። አሁን ሹሙ የባለገሩ ተንኮል በደንብ ገብቶታል። የተመደበለትን የአውራጃውን ኮታ ባያቀርብ ደግሞ የሚደርስበትን ያውቃል። ግራ በተጋባ ስሜት ለራሱ ያዘነ መሰለ።

"ጎበዝ የያዝነው የአገር ጉዳይ መስሎኝ። ውርድ ከራስ! ነገ ሁላችንም ነን የምንጠየቀው አንዴ አንድ ዓይና ቄስ፣ ሌላ ጊዜ እግረ በሽተኛ ሰው ለግዳጅ ስታቀርቡ ምን ማለታችሁ እንደሆነ እንዲገባችሁ እፈልጋለሁ። እዚህ የተኮለኮለው ጎረምሣ ሁሉ ለሀገሩ የማይዘምት ሆኖ ነው ወይስ .

. . ?" ሲል ደነፋ። የአውራጃው ሹሙ። ትንሽ በባለሥልጣንነት ዓይነት ድምፅ!

"የለም ጌታው እናንተ መሣሪያውን ስጡኝ እንጂ እንኳን በጥይት በዚህ እግሬ ብረግጥ የሀገሬን ጠላት እምገድል ነኝ" አለ እግረ-አባጣው ባላገር። የአውራጃው ሹም ባላገር ተመካክሮና ተማምሎ የቆየው መሆኑን አሁን በሚገባ ተረድቷል። ገብቶታል። ።

አንድ ሰው በተጠቆመ ቁጥር ሊሞቱ የደረሱ ሽማግሌዎች እየተነሱ የመፎከራቸው ምስጢር በደንብ ታይቷቸዋል ቀኑን ሙሉ በዚህ ዓይነት ባላገርና የመንግሥት ሹም ሲተናነቅ ድብብቆሽ ሲጫወት ውሎ ቀኑ መሸ። የአውራጃው ሹም ሌላ ቀጠሮ ይዞ መኪናውን አስነስቶ ተፈተለከ።

የተመለመሉት ጥቂት ሽማግሌዎች አካለ ጎዶሎና ቄሶች ነበሩ። ባላገር ዘዴው እንደሰራለት አወቀ። ጥንቱኑ እንዲህ ተመካክሮ ምስጢሩን ጠብቆ በሆነ አሰኘው። ይህንንም እንዲህ ሲል ላልሰማው የጎጃም ባላገር ሁሉ አዳረሰ:-

አላውቅበት ብለህ ከአገር መኖሩን፣
አላውቅበት ብለህ ቀድሞውኑ ጥንቱን፣
ተመዞ ተመዞ ቤትህ ያፈሳል፣
አንድ ሲል አንድ ሲል ገበያ እንኳን ያልቃል፣
ዛሬ ግን ከደብርህ የቀናህ መስሎኛል።

ሲል ከደብር ላይ የተማከረውና የተማማለው እንደጠቀመው ተነጋገረ። እንዲህም ከሆነ ባላገር ሚስጢሩን ጠበቅ አድርጎ እርስ በእርሱ መስማማት የሚያዋጣው መሆኑን:-

እንቆቆው ጎጃሜ እንዲህ ከተማረ፣
ደህና አድርጎ መክደኑ ዛሬስ መች ቸገረ።
በማለት የተገባባውን ቃል ኪዳን ለማጥበቅ ተስማማ።

(ይቀጥላል)

---

ሂርጳሳ አንዱዓለም የአዲስ አበባ ነዋሪ ናቸው።

---


## ማስታወቂያ

የላንዳፍታን መጽሄት በምትኖሩበት አካባቢ ለማከፋፈል የምትፈልጉ በአድራሻችን ደውሉልን።

ለአከፋፋዮች ጥሩ ኮሚሽን እንከፍላለን። በዚያውም በአገራችን ቋንቋ ለሚጻፍ መጽሄት ዕድገት አስተዋጽዖ እናደርጋለን። አድራሻችን

LANDAFTA
P.O.Box 49301
Atlanta, GA 30359
ስልክ (404) 728-9122

# Addisu Gebeya አዲሱ ገበያ

## We Carry Large Selection Of Ethiopian Foods & Spices

*We have everthing you need to prepare an Ethiopian Feast !*

| DESCRIPTION | QTY(lb) | Price |
|---|---|---|
| 1. Berbere | 1/2 | 3.99 |
| 2. Miten Shiro | 1/2 | 3.50 |
| 3. Aja | 1/2 | 3.50 |
| 4. Mitmita | 1/2 | 3.50 |
| 5. Awaze | 1/2 | 3.99 |
| 6. Butter Maker | 1 | 13.99 |
| 7. Tef | 1 | |
| 8. Mekelesha | 1 | 13.50 |
| 9. Kik | 1 | 0.49 |
| 10. Bakela | 1 | 1.79 |
| 11. Miser | 1 | 0.89 |
| 12. Kinche | 1 | 0.39 |
| 13. Telba | 1 | 1.25 |

NAME ______
ADDRESS ______
______
CITY ______
STATE ______ ZIP ______
Tel. ( ) ______

**WE DO MAIL ORDER**

Please Include $5.50 For Shipping And Make Your Check Or Money Order Payable To: Addisu Gebeya

- JEWELRY
- VIDEOS
- CASSETTES
- REKEBOTE (ረከቦት)
- COFFEE
- ETHIOPIAN ARTS
- ETHIOPIAN DRESS

AND MUCH MORE

2202 18th St. N.W.,
Washington, DC 20009
202 •986 •6013 / 23

# ኢትዮወርድ EthioWord

የተሟሉና የማይቀጠሉ የሞዴት ፊደላት፣ አጸጻፎችና አቀራረቦች ቡታዎቻቸውን እንደጠበቁ ብዙ የዊንደውስ ፕሮግራሞች ውስጥ በቀጥታ በግዕዝ ለመጻፍ ● ወደ እና ፕሮሜክሮ ለማዛወርና እዚያም ለማረም ● ለገቢ ወጪ፣ ለደረሰኝ፣ ለፎርሞች... ● ኢትዮዊን ከፊደል መለጠፊያና ኢትዮዎርድ ጋር

● Type *Ethiopic* in dozens of *Windows* applications with our complete (world font) characters and alphabets with pop-up on-screen keyboard. ● Import/export and edit in *Microsoft Word.*

**ሞዴት ModEth $400.00**
The scientific *Ethiopic* publisher for DOS

$280.00 ብቻ

FAST • EASY TO USE • PERFECT AND



**የኢትዮጵያ ኮምፒዩተሮችና ሶፍትዌር**
**Ethiopian Computers and Software**
9781 W. Fremont Pl., Littleton, CO 80123, USA
Tel.: (303) 972-2186 ● Fax: (303) 973-4342

*The pioneers of Ethiopic (Geèz) computing since 1982.*

ModEth, EthioScaler, EthioWin and EthioWord are trademarks of ABSHA Ltd

# ? ያለፈው ሰንጠረዥ መልስ

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| መ | ብ | ሳ | ት | ■ | ባ | ለ | አ | ን | ድ |
| ን | ቃ | ት | ■ | አ | ዳ | ም | ን | ■ | ን |
| ግ | ት | ር | ነ | ት | ■ | ■ | ተ | ላ | ክ |
| ስ | ■ | ቅ | ስ | ቀ | ሳ | ■ | ዋ | ና | ■ |
| ት | ል | ■ | ን | ባ | ብ | ይ | ወ | ዳ | ል |
| ■ | ስ | ት | ስ | ም | ■ | ሙ | ቀ | ት | ■ |
| ማ | ል | ን | ■ | ■ | በ | ላ | ው | ■ | በ |
| ■ | ስ | ግ | ደ | ት | ■ | | ■ | ወ | ጣ |
| አ | ያ | ር | ስ | ■ | አ | ት | መ | ጣ | ም |
| ማ | ለ | ት | ■ | ግ | ፍ | ■ | ጣ | ት | ■ |

## ሰንጠረዥ ጨዋታ

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 2 | 3 | 4 | ■ 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 |
| 11 | ■ 12 | 13 | 14 | 15 | 16 | ■ 17 | 18 | 19 | 20 |
| 21 | 22 | 23 | ■ 24 | 25 | 26 | 27 | 28 | ■ 29 | 30 |
| 31 | 32 | ■ 33 | 34 | 35 | 36 | ■ 37 | 38 | 39 | 40 |
| ■ 41 | 42 | 43 | 44 | 45 | 46 | 47 | ■ 48 | 49 | ■ 50 |
| 51 | 52 | 53 | ■ 54 | 55 | ■ 56 | ■ 57 | 58 | 59 | 60 |
| 61 | ■ 62 | 63 | 64 | 65 | 66 | 67 | 68 | ■ 69 | 70 |
| 71 | ■ 72 | 73 | 74 | 75 | ■ 76 | 77 | 78 | 79 | 80 |
| 81 | 82 | ■ 83 | 84 | ■ 85 | 86 | 87 | 88 | ■ 89 | 90 |
| 91 | 92 | 93 | 94 | 95 | 96 | 97 | ■ 98 | 99 | 100 |

### ወደ ጎን
1. bottle
6. he made him weep
13. not to strike (ዱላ)
18. it became beautiful
25. ትካዜ
31. bee
34. she sent
38. potatoe
42. without investigating
51. Eth. traditional dress (for cold)
58. የአልጋ ቅመም
63. ከአባት ከልጅ
73. insect
77. great ones
81. fresh
86. he kissed her
91. you are sleepy
99. left

### ወደ ታች
1. light
3. vocabulary
4. quarrel
6. she does't give comfort
8. for one
9. he snatched
10. she stole
15. she witnessed against me
22. chairperson
34. ደቀቀ
39. eagle
42. vomit (noun)
51. የሀረርጌ አውራጃ
58. renovation
60. good job
64. bedshhet
67. when she gossips about you
82. የጠላ መጥመቂያ
86. he coughed

መልሶቻችሁን ላኩልን።

# የላንዳፍታ መጽሔት ደምበኛ ይሁኑ

| | | | |
|---|---|---|---|
| ለ6 ተከታታይ እትሞች | U.S. | $16.00 | (including postage & handling) |
| | Canada | $22.00 | (including postage & handling) |
| | Europe & Asia | $30.00 | (including postage & handling) |

የሚላክሎት በመጀመሪያ ደረጃ ፓስታ አገልግሎት ነው።
በአካባቢዎ ገበያ ላይ ከመዋሉ በፊት ይደርስዎታል።

## የላንዳፍታ መጽሔት የደምበኝነት ቅጽ LANDAFTA SUBSCRIPTION FORM

NAME ______________________________

ADDRESS ______________________________

CITY ______________ STATE ________ ZIP ________

PHONE ( _______ ) ______________

<u>ያለፉትን እትሞች</u> ማዘዝ ከፈለጉ ይህንኑ ይጥቀሱ
ክፍያው ከነመላኪያው ለእያንዳንዱ እትም $ 2.50 ነው።

ለጓደኛዎ በሽልማት መልክ ለመላክ ከፈለጉ ከዚህ በታች ያለውን ይሙሉ።
Please, send my gift subscription to the following person.

NAME ______________________________

ADDRESS ______________________________

CITY ______________ STATE ________ ZIP ________


PHONE ( _______ ) ______________

እባክዎን ክፍያዎን በመኒ ኦርደር ወይም በቸክ በአድራሻችን ይላኩ።
*Please, send money order or check payable to LANDAFTA.*

LANDAFTA
P.O.BOX 49301
ATLANTA, GA 30359,

# ADVERTISE ON LANDAFTA

# በላንዳፍታ ላይ ድርጅቶን ያስተዋውቁ




**ADVERTISMENT ORDER FORM**

I would like to place an advertisment on LANDAFTA.

Name: ____________________

Address: ____________________

City: ____________________

St. ___ Zip: ____________

Phone: ____________________

PLEASE, MARK THE SPACE BELOW TO INDICATE YOUR CHIOCE LIKE THIS (X)

## SINGLE ISSUE RATES

| | |
|---|---|
| ◯ BACK COVER | $200.00 |
| FULL PAGE | |
| ◯ INSIDE COVERS | $175.00 |
| ◯ INSIDE PAGES | $140.00 |
| ◯ HALF PAGE | $90.00 |
| ◯ 1/4 PAGE | $65.00 |
| ◯ 1/8 PAGE | $50.00 |

## TWO CONSECUTIVE ISSUES RATE

| | |
|---|---|
| ◯ BACK COVER | $350.00 |
| FULL PAGE | |
| ◯ INSIDE COVERS | $300.00 |
| ◯ INSIDE PAGES | $250.00 |
| ◯ HALF PAGE | $150.00 |
| ◯ 1/4 PAGE | $110.00 |
| ◯ 1/8 PAGE | $90.00 |

ላ
ን
ዳ
ፍ
ታ

Enclosed, please find: 1. A copy of the advertisment to be placed.
2. A check for the amount marked above.

Please, send a copy of the proof before printing. ☐

I Want my ad Translated in Amharic ☐
(no extra fee - please indicate words or phrases to be translated)

For Information, Please Call Advertisment Department:
Publisher at: Phone/Fax (404)728-9122

Please, Send check or money order payable to LANDAFTA along with your order.
LANDAFTA, P.O.Box 49301, Atlanta GA 30359



# MRA'G TRAVEL
## ሚራዥ የጉዞ ወኪል

*International - Business - Leisure - Cruise*


ለአለም አቀፍና
ለአገር ወሰጥ ጉዞዎ አለንልዎ!

ገነት ፈቀደ
ፕሬዚዳንት
Genet Fekede
*President*

እስ·ተማማኝ ጉዞ ወደ

አዲስ አበባ
አስመራ
ጆሀንስ በርግ
ቴላቪ·ቭ
ኢየሩሳሌም
ፍራንክፈርት
ለንደን

Excellent Service!
Special Fare!
Group Fare!



92 Piedmont Ave N.E
Atlanta, GA. 30303
(404)577-4404 Fax (404)222-9305



## ካሊፎርኒያ ማርት በአትላንታ
## CALIFORNIA MART IN ATLANTA

2080 CHESHIRE BRIDGE ROAD
ATLANTA, GA 30324
(404)320-6747 - (404)320-9082

ቁርስ — ፉል፤ ግንፍልፍል፤ ያበሻ ዳቦ፤ አምባሻ

ምሳና እራት — ክትፎ፤ ጥብስ፤ ጎረድ ጎረድ፤ የጥብስ ፍርፍር፤ የበግ አልጫ ፍትፍት

በተጨማሪ እንጀራና ሥጋ እንሸጣለን።

ORDER FOOD TO GO!!

የተለያዩ የምግብ ሸቀጦች መደብር

ESPRESSO
CAPPUCCINO

| | |
|---|---|
| በርበሬ | እጣን |
| ሚጥሚጣ | የተነጠረ ቅቤ |
| ሽሮ | አዋዜ |
| ቅንጩ | ጌሾ |
| ምስር | የወጥ መከለሻ |
| ጤፍ | ቡላ ዱቄት |
| ቡና | ልዩ ልዩ ቅመማ ቅመሞች |

ይደውሉልን ወይም ይጎብኙን!!

Mail Order Available
Please, call for Arrangements